የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት

# ብሔራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ

## 2011-2020 ዓ.ም

መስከረም 2011
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ምስጋና | i |
| መግቢያ | iii |
| መልዕክት ከኢፌዲሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚንስትር | v |
| መልዕክት ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር | vii |
| ክፍል አንድ: - የስትራቴጂው መነሻዎችና አስፈላጊነት | 1 |
| 1.1. የስትራቴጂው መነሻዎች | 1 |
| 1.1.1. የሀገራችንን ልማት ለመደገፍ | 1 |
| 1.1.2. ሀገራዊ ወጪን ለመቆጣጠርና ብክነትን ለማስቀረት | 2 |
| 1.1.3. የሎጅስቲክስ ችግር አፈታት ሥርዓት ተኮር እንዲሆን ማድረግ | 3 |
| 1.1.4. ዘርፉን በግልጽ ራዕይና አቅጣጫ ለመምራት | 4 |
| 1.2. ስትራቴጂው ከአገራዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ጋር ያለው ትስስር | 5 |
| 1.2.1. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ እና የትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ትስስር | 6 |
| 1.2.2. የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጅዎቻችንና የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው ትስስር | 6 |
| 1.2.3. የከተማ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች | 6 |

| | |
|---|---|
| 1.2.4. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅንነት ፖሊሲ ግቦች እና ብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ትስስር | 8 |
| 1.2.5. የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ትስስር | 9 |
| 1.3. የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ አዘገጃጀት | 12 |
| **ክፍል ሁለት፡- የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም** | 15 |
| 2.1. የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች አንጻር፤ | 25 |
| 2.1.1. በዓለም ባንክ የሚዘጋጀው የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያ (LPI) | 15 |
| 2.1.2. የዓለም የወደብ አልባ ሀገሮች የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ግምገማዊ ሪፖርት | 19 |
| 2.1.3. የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም (World Economic forum) | 19 |
| 2.1.4. የዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ማጠቃለያ | 20 |
| 2.2. የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ ወጪና ጊዜ ትንታኔ፤ | 20 |
| 2.2.1. የሎጅስቲክስ ጊዜ (Logistics Time) | 21 |
| 2.2.2. የሎጂስቲክስ ወጪ (Rates and Cost Indicators) | 26 |
| 2.3. የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ ግምገማና የችግሮች ትንታኔ ግኝቶች | 32 |
| 2.3.1. የንግድና የፋይናንስ ሥርዓት | 32 |
| 2.3.2. ያልተቀላጠፈ ያልተቀናጀ የትራንዚትና የጉምሩክ አሠራር | 33 |
| 2.3.3. የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ብቃትና አቅም ዝቅተኛ መሆን | 34 |

| | |
|---|---|
| 2.3.4. በሎጅስቲክስ የአገልግሎት ዘርፍ የሞኖፖሊ አሠራር ችግር | 34 |
| 2.3.5. በቂ የሎጅስቲክስ መሠረት ልማት አለመኖርና የማኔጅመንት ችግር | 35 |
| 2.3.6. በሎጅስቲክስ ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪዎችም ሆነ በተቆጣጣሪ ተቋማት ያለው የአደራጀጀት፣ የአቅም፣ የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት | 35 |
| **ክፍል ሶስት፡- የሎጅስቲክስ ዘርፍ ራዕይ፣ የስትራቴጂው ዓላማና ግቦች** | 37 |
| 3.1 ዓላማና ግቦች | 37 |
| 3.1.1 አጠቃላይ ዓላማ | 37 |
| 3.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች | 37 |
| 3.1.3 የስትራቴጂው ግቦች | 37 |
| 3.2 የሎጅስቲክስ ዘርፍ ስትራቴጂዎች | 38 |
| ስትራቴጂ 1 የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አሠራርና የኦፕሬተሮች ብቃት ትራንስፎርም ማድረግ፡፡ | 39 |
| ስትራቴጂ 2 የሎጅስቲክስ ዘርፍ የፖሊሲና የህግ ዕቀፍ ማጠናከር | 51 |
| ስትራቴጂ 3 የተሳለጠና አስተማማኝ የጉምሩክና የትራንዚት ሥርዓት መዘርጋት | 55 |
| ስትራቴጂ 4 አስተማማኝ የንግድና የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት በሎጅስቲክስ የማሳለጥ ሚናውን ማጉልበት | 62 |
| ስትራቴጂ - 5 የሎጅስቲክስ መሠረተ - ልማት መገንባት | 66 |
| ስትራቴጂ - 6 የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተቋማዊ አቅምና የዘርፉ የሰው ኃይል መገንባት እና ውጤታማ አደረጃጀት መፍጠር | 70 |

| | |
|---|---|
| **ክፍል አራት፡- ስትራቴጂውን በመፈጸም ረገድ ከመንግስት የሚጠበቁ እርምጃዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚና የክትትልና ግምገማ ስርዓት** | 75 |
| 4.1 ከመንግስት የሚጠበቁ እርምጃዎች | 75 |
| 4.2 የባለድርሻ አካላት ሚና | 75 |
| 4.3 የስትራቴጅው አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ አቅጣጫ | 81 |

# ምስጋና

የብሔራዊ ሎጅስቲክ ስትራቴጂ ትግበራ የሀገሪቱን የንግድ ሎጅስቲክስ ዘርፍ በመሰረታዊነት በመለውጥ እና የውጭ ንግድ ተወዳዳሪነትን በማሻሻል ረገድ ጉልህ ሚና ይኖረዋል፡፡ የኢትዮጵያ የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ይህንን ስትራተጂ ሰነድ በማዘጋጀት ሂደት ዋና ኃላፊነት ወስዷል፡፡ የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ዋና ዳይሮክተር የሆኑት አቶ መኮንን አቶ አበራ፤ ይህን ስትራቴጂ ዝግጅት ከጅማሬ ጀምሮ እስከ ፋጻሜ ድረስ በማስተባበር እና በመከታተል ላበረከቱት አስተዋጽኦ ላቅ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

እንዲሁም በብሔራዊ ሎጅስቲክ ስትራቴጂ ዝግጅት ወቅት የተለያየ ድጋፍ ላደረጉ ተቋማት በተለይም፡-

- የትራንስፖርት ሚኒስቴር
- የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም
- የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርትና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት
- የገቢዎች ሚኒስቴር
- የጂቡቲ ወደብ ባለስልጣን
- አስመጪዎች፤ ላኪዎች፤ የመርከብ ወኪሎች፤ ዕቃ አጓጓዦች እና የዕቃ አስተላላፊዎች
- የመንግስት እና የግል ባንኮች፤

ከፍ ያለ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መረጃ በማስባሰብ እና የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ተሳትፎ ላደረጉ ለመላው የማሪታይ ጉዳዮች ባለስልጣ ሰራተኞች መ/ቤቱ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

# መግቢያ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ መንግስት ግቦች በሀገራችን ፈጣን ልማትን ማረጋገጥና ከልማቱም ህዝቡ በየደረጃው ተጠቃሚ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መነሻነት ላለፉት አሥራ ሁለት ተከታታይ ዓመታት የተመዘገበው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገትን ተከትሎ የውጭ ንግድ ዕቃዎችና የሀገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ በመጠንና በዓይነት በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የሀገራችንን የውጭ ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት ውስጥ ዋናው ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት ነው፡፡ በሌላ በኩል የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ውጤታማነት መለኪያ በሆኑት ከሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ አንጻር ሲመዘን በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ ሎጅስቲክሱ በትራንዚት ጊዜ፣ በዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ፣ በመርከቦች የወደብ ላይ ቆይታ፣ ጭነት ከወደብ የማንሳት አቅምና በመሰል የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከመሆኑም ባሻገር ዘርፈ-ብዙ ጉዳት እያስከተለ ነው፡፡

ስለሆነም ይህን የሎጅስቲክስ ሥርዓትን ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስችል ጥናት እና ትንታኔ ላይ የተመሠረተ ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና በተቀናጀ መልኩ መተግበር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡ በዚሁም መሠረት ይህ ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ተዘጋጅቷል፡፡

## የስትራቴጂ ሰነዱ በአራት ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን

**ክፍል አንድ** የስትራቴጂው መነሻዎችና አስፈላጊነት፣ ከሌሎች የሀገሪቱ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ጋር ያለው ትስስር እና ስትራቴጂው የተዘጋጀበትን ሂደት ያሳያል፡፡

**ክፍል ሁለት** ከሎጅስቲክስ መሠረታዊ የአፈጻጸም መለኪያዎች በመነሳት በሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት በተጨባጭ ያሉት ክፍተቶችና ችግሮች እንደዚሁም የችግሮቹ ዋና ዋና መንስኤዎች ተዳሰውበታል፡፡

**ክፍል ሶስት** የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ራዕይ፣ ዓላማና ግቦች፣ እንደዚሁም ዓላማና ግቦቹን ለማሳካት የሚያስችሉና በሥርዓቱ ዙሪያ የተዳሰሱትን መሠረታዊ ክፍተቶች ለማስተካከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎች፣ ንዑሳን ስትራቴጂዎችና የማስፈጸሚያ ሀሳቦች (Interventions) የቀረበበት ነው፡፡

**ክፍል አራት** ከመንግስት የሚጠበቁ እርምጃዎች፤ የባለድርሻ አካላት ሚና እና የክትትልና ግምገማ ስልቶችን አካቶ ቀርቧል፡፡

# መልዕክት

## ከኢፌዴሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚንስትር



ክብርት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ
የኢፌዴሪ ትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚንስትር

ሎጅስቲክስ የአንድን ሀገር የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ነባራዊ ሁኔታን ከተቀረው ዓለም ጋር ለሚያስተሳስረው የንግድ እንቅስቃሴ የጀርባ አጥንት ነው፡፡ የዓለም ዓቀፍ የንግድ መጠን እና እንቅስቃሴ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ1968 በባህር የሚጓጓዘው የዓለም የንግድ መጠን 2.6 ቢሊዮን ሜ/ቶን የነበረ ሲሆን ከ50 ዓመታት በኋላ በ2018 ይህ መጠን ወደ 10.7 ቢሊዮን ሜ/ቶን ደርሷል፡፡

ይህንን ጭነት በማንቀሳቀስ ከመነሻ ወደ መዳረሻ ቦታው በማድረስ ሂደት ትራንስፖርት እና በአጠቃላይም ሎጅስቲክስ ቁልፍ ሚና ይጫወታል፡፡ ሎጅስቲክስ በተደራጀ እቅድ፣ በተሟላ መሰረተ ልማት፣ በነጠረ እና በታቀለለ የህግ ማዕቀፍ እና አሰራር፣በሰለጠነ የሰው ሀይል እና በቴክኖሎጂ ተደግፎ ካልተመራ የኢኮኖሚ እድገትን ከሚያቀጭጩ ችግሮች አንዱ ይሆናል፡፡

በዓለም ላይ እንደሚስተዋለው የንግድ እንቅስቃሴ እድገት ሁሉ የሀገራችን የንግድ መጠንም ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል፡፡ እ.ኤ.አ በ1991 የኢትዮጵያ የዓለም አቀፍ ንግድ መጠን 1.3 ሚሊዮን ሜ/ቶን የነበረ ሲሆን ይህ መጠን በ2018 ወደ 12.5 ሚሊዮን ቶን ደርሷል፡፡ ሆኖም ይህንን ለማስተናገድ ያለው የሀገራችን ሎጅስቲክስ እድገት ከመንገድ አቅርቦት፣ ከትራንስፖርት አቅርቦት፣ ከፋይናንስ አቅርቦት፣ከወደብ እና ኮሪደር አጠቃቀም፣ ከጉምሩክ አሰራር እና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል ከማሰማራት አንጻር ሲታይ ከዓለም አቀፍ አሰራር ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ ወደ ኋላ የቀረ እንደሆነ በብዙ ማስረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ስለሆነም ዘርፉን በሚገባ በተደራጀ ስትራቴጂ መምራት ለመንግስት ቅድሚያ ትኩረት የተሰጠው ተግባር በመሆኑ በዘርፉ የተሰማራችሁ የመንግስት፣ የግልና ዓለም አቀፍ ደጋፊ አካላት ስትራቴጂውን በመተግበር ሂደት የማይተካ ሚናችሁን እንደምትወጡ እምነቴ የጸና ነው፡፡ የትራንስፖርት ሚኒስቴር ይህንን ስትራቴጂ በማስፈጸም ረገድ የአንበሳውን ድርሻ በመውሰድ የማይቋረጥ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

አመሰግናሁ!
ስትራቴጂውን በተሟላ መልኩ ለመተግበር ሁላችንም እንትጋ!.

# መልዕክት

## ከማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር




አቶ መኮንን አበራ
የማሪታይም ጉዳይ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር

የሎጂስቲክስ ዘርፉን በጠራ ራዕይ፣ ዓላማና አቅጣጫ ለመምራት የሚያስችል ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድ መዘጋጀቱና በመንግስት መጽደቁ ትክክለኛ እርምጃና ትልቅ ስኬት ነው፡፡

በሎጅስቲክስ አገልግሎትና ሎጅስቲክስ ነክ ጉዳዮች ዙሪያ በተደጋጋሚ፣ ለተራዘሙ ጊዜያቶች በችግርና በችግር ትንታኔ ላይ ከመወያየት አዙሪት ወጥቶ፣ በዘርፉ ያሉት በርካታ ማነቆዎችን ለመፍታት በሚያስችሉ የመፍትሄ ሃሳቦችንና ኘሮግራሞችን ወደ መተግበር አጀንዳ መሸጋገር እንደ ሀገር ትልቅ እመርታ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በሌላ በኩል በመንግሥት የጸደቀው ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ሰነድ በራሱ ግብ አይደለም፡፡ የሎጀስቲክስ ሥርዓታችንን ትራንስፎርም ለማድረግም ዋስትና አይሆንም፡፡ ትራንስፎርሜሽን የትግበራ ውጤት ነው፡፡ በመሆኑም

ትልቁ ጉዳይ በዘርፉ ያሉት በርካታ ማነቆዎች ለመፍታት የሚያስችሉ ኘሮግራሞችን በመተግበር ውጤት ማስመዝገብ ነው፡፡ የትግበራ ሂደት ሃሣብን የሚያስታውሰኝ አንድ ጥሩ አባባል አለ፤ “ዋናው ነገር፣ ዋናውን ነገር ዋና ማድረግ ነዉ”፡፡

የሀገራችን የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ የትግበራ ምዕራፍ ዋናው ነገርም የስትራቴጂውን ትግበራ ሊሸከም የሚችል አደረጃጀት መፍጠር ነው፡፡

በዚህ ረገድ በዘርፉ ቁልፍና የማይተካ ሚና ያላቸው ሚ/ር መ/ቤቶችና ተቋማት ከስትራቴጂው በልካቸው የድርሻቸውን ቆርሰው በመወሰድ፣ በጥብቅ ዲሲኘሊን እንዲተገበሩ አስተሳስሮና አቀናጅቶ የሚመራ አደረጃጀት መፍጠር ሲሆን፣ በዚህም የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው ትግበራ በበላይነት አመራር የሚሰጥ የቅንጅት መድረክ መፍጠር አንዱ ነው፣ ሁለተኛው በስትራቴጂው የተዘረዘሩት የመፍትሄ ሃሣቦችን ለቅሞ ወደ ኘሮግራምና ኘሮጀክት ለመለወጥ በመረጃ ትንታኔ ላይ ተመስርቶ ትግበራውን በባለቤትነት የሚፈጽም የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ ማቋቋም ነው፡፡

ስለሆነም የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (አካዳሚ) በሎጅስቲክስ ዘርፍ የተሟላ የትምህርት ዝግጅት ያላቸው፣ ከኢንዱስትሪው ደግሞ ረጅም የሥራ ልምድ፣ ብቃትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች በማሰባሰብ ጠንካራ የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ በማቋቋም ይህን ስትራቴጂ ለመፈጸም የበኩሉን ሚናና ኃላፊነት የሚወጣ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

# ክፍል አንድ፡

## የስትራቴጂው መነሻዎችና አስፈላጊነት

በዚህ ክፍል የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ (National Logistics Strategy /NLS) ዝግጅት መነሻዎችና የስትራቴጂው አስፈላጊነት እንዲሁም ስትራቴጂው ከአገራዊ እና የሴክተር ፖሊሲዎች ጋር ያለው ትስስር ቀርቧል፡፡

### 1.1. የስትራቴጂው መነሻዎች

ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂን ለማዘጋጀት በዋናነት አራት ጉዳዮች እንደመነሻ ተወስደዋል፡፡ እነርሱም፡-

#### 1.1.1. የሀገራችንን ልማት ለመደገፍ

በሀገራችን እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ ዕድገት ፈጣን ነው፡፡ ፈጣን ብቻ ሳይሆን ቀጣይነትም ያለው ነው፡፡ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥ ደግሞ ሎጅስቲክስ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ሀገራችን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማስቀጠል ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴ እያደረገች ሲሆን፣ በዚህም ኢንቨስትመንትን ለመሳብ የሚያስችሉ በርካታ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ ይሁን እና በልዩ ልዩ ድጋፎች መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለሀብቶች ሎጅስቲክስ አሁንም ስጋታቸው ነው፡፡ በዚህም ሎጅስቲክስ የልማት ማነቆ የመሆን ዕድሉ ሰፊ እየሆነ ነው፡፡

ስለሆነም የሎጅስቲክስ ሥርዓታችን መገለጫ የሆኑትና በማንኛውም መስፈርት ተቀባይነት የሌላቸው ዝቀተኛ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር የሎጅስቲክስ ሥርዓታችን ከልማት ማነቆነት ተላቆ ሀገራችን ለኢንቨስትመንት ተመራጭ እንድትሆን ከሚያደርጉት ሁኔታዎች (enabling factor) አንዱ እንዲሆን የማድረግ ተግባር ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

የሀገራችን የሎጅስቲክስ ችግር መገለጫዎች ከሆኑት መካከል የዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ከፍተኛ መሆን አንዱ ነው፡፡ የውጭ ንግዳችን የሚያጓጉዙ መርከቦች ሳያራግፉ በባህር ላይ ቆመው የሚያሳልፉት ጊዜ (Anchorage time) ለማራገፍ ከሚወስድባቸው ጊዜ ጋር ተዳምሮ

ከ2-3 ወራት መድረሱ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ እንዲንር አድርጓል፡፡ ተወዳዳሪ አይደለም ከሚል አልፎ ጉዳቱ ከንግድ አጋሮቻችን (ከአቅራቢዎችና፣ የመርከብ፣ ባለቤቶች) ጋር ያለን የንግድ ግንኙነት ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር ጀምሯል፡፡

በመሆኑም ይህ አሳሳቢ ጉዳይ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂን ለማዘጋጀት አንዱ መነሻ ነው፡፡

## 1.1.2. ሀገራዊ ወጪን ለመቆጣጠርና ብክነትን ለማስቀረት

የሀገራችንን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ ከውጭ የሚገቡ የኢንቨስትመንት፣ የንግድ የፕሮጀክትና መሰል ዕቃ መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ነው፡፡ የሀገር ውስጥ ንግድም እንደዚሁ እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚያው ልክ የሎጅስቲክስ ወጪውም በእጅጉ እያደገ ነው፡፡ ከሀገራችን የሎጅስቲክስ ወጪ ውስጥ አላግባብ የሚወጣና ብክነትን እያስከተለ ያለው መጠንም በዚያው ልክ እያደገ ነው፡፡

ለማሳያ ያህል በመንግስት አስመጪዎች ብቻ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ደረቅ ብትን ጭነት (ማዳበሪያ፣ እህል፣ ከሰልና ስኳር) በዓመት በአማካይ ከ2.5 — 4ሚሊዮን ቶን ይሆናል፡፡ ለዚህ ጭነት ለትራንስፖርት ብቻ (የባህር፣ የወደብ አገልግሎትና የመንገድ) በዓመት በአማካይ ከ6 ቢሊዮን ብር በላይ ያህል ወጪ ይደረጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ጭነቶች ለማቅረብ በጨረታ የሚሳተፉ አቅራቢዎች በሚያቀርቡት ዋጋ ላይ ለመርከብ ዲመሬጅ ብቻ በአንድ ቶን 10 የአሜሪካን ደላር ተጨማሪ ወጪ ጨምረው ያቀርባሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በሀገራችን ያለው የተወሳሰበ የሎጅሰቲክስ ሥርዓት ነዉ፡፡ በማሳያነት የተጠቀሰው አላስፈላጊ ወጪ የመርከቦች የባህር ወደብ ላይ ቆይታ ከፍተኛ በመሆኑ የሚከፈል አላስፈላጊ ወጪ ነው፡፡

በአጠቃላይ የትራንስፖርት ወጪ፣ የወደብ፣ የመጋዘን ኪራይ፣ ለኮንቴይነር ዲመሬጅ፣ ለትራንዛክሽን ወጪ፣ ለኢንቨንተሪ ወጪና ሌሎች የሎጅስቲክስ ወጪዎች ከፍተኛ ናቸው፡፡

በመሠረቱ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ሊወገዱ የሚችሉ አላሰፈላጊ ወጪዎችን የተሸከመ ነው፡፡ ዓለም አቀፍ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የሎጅስቲክስ ወጪ ከአገር አገር የሚለያይ ቢሆንም በአማካይ የ "GDP" ከ14% - 35% እንደሚሆን ይገመታል፡፡

በመሆኑም የሎጅስቲክስ ወጪ አንዱ ሀገራዊ ወጪ ነው፡፡ ሀብትን ከብክነት ለማዳን ደግሞ ወጪን በሥርዓት መምራትን ይጠይቃል፡፡ በኩባንያ/ተቋም ደረጃ እንኳ ወጪን የሚቆጣጠር አካል (Cost Manager) በማቋቋም የወጪ መቀነሻ ዘዴን በመቀየስና ወጪን በአግባቡ የመምራት ሥራ ይሰራል፡፡ ይልቁንም በሀገር ደረጃ ከፍተኛ የሆነው የሎጅስቲክስ ወጪን መምራት የግድ ይላል፡፡ ለዚህም የሎጅስቲክስ ወጪን በአግባቡ መለየትን፣ የተበታተነ መረጃ ማሰባሰብን፣ መተንተንና ከፍተኛ የሆነ የሀገር ሀብትን ከብክነት ለማዳን የሚያስችል ሥርዓት የመዘርጋት አስፈላጊነት ለሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ዝግጅት ሌላው መነሻ ነዉ፡፡

### 1.1.3. የሎጅስቲክስ ችግር አፈታት ሥርዓት ተኮር እንዲሆን ማድረግ

በሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ዙሪያ እያጋጠሙ ያሉት ችግሮች፣ የችግሮቹ መገለጫዎች፣ የችግሮቹ መንስኤዎችና እያስከተሉት ያለው ጉዳት ከሎጅስቲክስ ሥርዓታችን የመነጩ ናቸው፡፡ የሎጅስቲክስ ሥርዓታችንን የገነቡት ደግሞ በርካታ ተዋናዮች አሉ፡፡ የበርካታ ጉዳዮች ስብስብና ትስስር ነው፡፡ በሎጅስቲክስ ሥርዓታችን ውስጥ ዘርፉ የሚመራበት ህግና ፖሊሲ፣ የተዘረጋው መሠረተ ልማት፣ ዘርፉን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ ተቋማት አሠራር፣ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች፣ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብቃት፣ ዓቅምና መሰል በርካታ ሁኔታዎች ከፍተኛ ድርሻ አላቸው፡፡ ለሎጅስቲክስ አገልግሎትና የአፈጻጸም ደረጃ ዝቅተኛነት በሥርዓቱ ውስጥ ያሉት ተዋናዮችና በርካታ የተንዛዙ አሠራሮች ድርሻ አላቸው፡፡ ለመፍትሄውም በዚያው ልክ በልካቸው ድርሻ አላቸው፡፡ የሀገራችን ሎጅስቲክስ ልማታችንን ሊደገፍ በሚችል ቁመና እንዲገኝ ለማድረግ የሚወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች የተናጠል መሆን የለባቸውም፡፡ የተናበበ፣ የተቀናጀና ትስስር ያለው የመፍትሄ አሰጣጥ አካሄድ መከተል ይኖርበታል፡፡ የሎጅስቲክስ ችግርን ለመፍታት ስትራቴጅክ ጉዳዮችን በመዘንጋት በኦፐሬሽናል የመፍትሄ ጉዮች ላይ ብቻ ማተኮር በቂ አይደለም፡፡ የሎጅስቲክስ ችግሮችን ከመሰረቱ ለመፍታት ትራንስፎርም ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ስለሆነም የሀገራችንን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርም ለማድረግ ከኦፐሬሽናል መፍትሄ (Operational Solution) ባለፈ ሥርዓት ተኮር (Systemic) የማድረግ አስፈላጊነት ሌላው የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው አንዱ መነሻ ነው፡፡

### 1.1.4. ዘርፉን በግልጽ ራዕይና አቅጣጫ ለመምራት

ሎጅስቲክስ ጭነቶችን፣ መሠረተ-ልማቶችን፣ በዘርፉ ያለውን አሠራርና የሰው ኃይልን አስተሳስሮና አቀናጅቶ የመምራት ተግባርን ያካትታል፡፡ በመሆኑም ሎጅስቲክስ በርካታ አካላትንና አሠራሮችን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማቀናጀት የሚያስችል ስልትን ይሻል፡፡ ሎጅስቲክስ ጠንካራ የመረጃና የክትትል አሠራርም ይፈልጋል፡፡ የሀገራችን ሎጅስቲክስ በትክክለኛ መረጃና ትንታኔ ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ አውድን ተረድቶ በመምራት ረገድ ክፍተት አለ፡፡ በዘርፉ ችግሮች ዙሪያ ሁሉም በመሰለው "ትንታኔ" የሚያቀርብበት ነው፡፡ በመሆኑም ትክክለኛ የዘርፉ ወሰንና ድንበር ተበጅቶለት በዚሁ ልክ የባለቤትነትና የኃላፊነት መስመርም ተለይቶ በመምራት በኩል ክፍተት አለ፡፡

በዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ሚና ያላቸው ጉዳዮች ለምሳሌ የወደብ አጠቃቀም፣ ዘርፉ የሚመራበት ፖሊሲና በመሰል አቅጣጫዎች የጠራ ራዕይና ስትራቴጂ ነድፎ በመንቀሳቀስ በኩልም ክፍተት አለ፡፡ ስለሆነም እነዚህና መሰል ክፍተቶች በሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ላይ የሚኖራቸው ድርሻና ተጽዕኖ ግምት ውስጥ በማስገባት ክፍተቶቹን ለመድፈን የሚያስችል ስትራቴጂ የመንደፉ አስፈላጊነትም ሌላው መነሻ ነው፡፡

## 1.2. ስትራቴጂው ከአገራዊ ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎች ጋር ያለው ትስስር

የሀገራችንን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ለማምጣት በየደረጃው የሕዝቡን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እና የዲሞክራሲ ሥርዓታችንን ለመገንባት በሚገባ የተዘረዘሩ አገራዊ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተው በመተግበር ላይ ናቸው፡፡ እነዚህ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ረጅም ዘመን ተሻጋሪ እንደመሆናቸው በርካታ ጉዳዮችን ጠቅልለው የያዙ ቢሆንም በተለይም የትራንስፖርት ሎጅስቲክስ በፖሊሲዎች አፈጻጸም ያለውን ሚና በሚገባ መገንዘብና መተንተን፤ የፖሊሲዎችን አቅጣጫ በመከተል እነሱን ከማሳካት አንጻር መቃኘት ተገቢ ይሆናል፡፡ በመሆኑም የሎጅስቲክስ ስትራቴጅው አገራዊ ፖሊሲዎችን ከማሳካት አንጻር ያለው ድርሻ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### 1.2.1. የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ እና የትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ትስስር

በ1994 ዓ.ም ጸድቆ በስራ ላይ ያለው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅ መነሻ መርሆዎች የኢንዱሰትሪ ልማት ስትራቴጅው ሞተር የግል ባለሀብቱ መሆኑን አምኖ መቀበል፤ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፤ ኤክስፖርት መር የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫን መከተል፤ ጉልበትን በሰፊው በሚጠቀሙ ኢንዱስትሪዎች ላይ ያተኮረ የልማት አቅጣጫን መከተል፤ የአገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብትን አቀናጅቶ የመጠቀም አቅጣጫን መከተል፤ የመንግስት ጠንካራ የአመራር ሚና የሚጫወትበትን አቅጣጫ መከተል፤ መላው ህብረተሰብ ለኢንዱስትሪ ልማት በጋራ የሚሰለፍበትን አቅጣጫ መከተል እና ለኢንዱስትሪ ልማትና ለልማታዊ ባለሀብት የተመቻቸ ሁኔታን መፍጠር (የጥገኝነት አረንቋን ማድረቅ፤ የተረጋጋና ለልማት የሚያመች የማክሮ ኢኮኖሚ ሁኔታን መፍጠር፤ ዘመናዊና ለልማት የተመቻቸ የፋይናንስ ስርዓት መፍጠር) እንደሆኑ ተጠቅሰዋል፡፡

በዋናነት ግን አስተማማኝ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ማቅረብ (የመንገድ እና መንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት፤ የባቡርና የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት፤ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት፤ የቴሌኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት፤ የኤሌክትሪክ አገልግሎት፤ የውሃ እና የመሬት አቅርቦት) ለልማታዊ ባለሀብቱ ቀጥተኛ ድጋፍና አመራር መስጠት በትራንስፖርት ሎጅስቲክስ እና መሰል አገልግሎት ተቋማት የሚፈጸሙ አቅጣጫዎች ተጠቅሰዋል፡፡ ስለሆነም የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጅው የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅውን ከማሳካት አንጻር እና በመስኩ ለሚሰማራ የግል ባለሀብት የሚሰጠው ጠቀሜታ እጅግ የጎላ ነው፡፡ በኢንዱስትሪው ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በተለይም በአሁኑ ወቅት እየተገነቡ ላሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ቀጥተኛ የሆነ የሎጅስቲክስ ድጋፍ ከሌላቸው እና ጥሬ እቃ ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ በወቅቱ እና በተመጣጣኝ የሎጅስቲክስ ወጪ ካልቀረበላቸው እና ምርቶቻቸው ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ ለዓለም ገበያ ማቅረብ ካልቻሉ ኢንዱስትሪዎች በትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ብቃት ማነስ ምክንያት ሊመክኑ ይችላሉ፡፡ በሀገራችን የሚገነቡ ትላልቅ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች እንደ የማዳበሪያ እና የስኳር ፋብሪካዎች፤ የኃይል አቅርቦት ፕሮጀክቶች እና ሌሎችም የግብርና ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራሞችን በታለመላቸው ጊዜ እና ወጪ ለማሳካት የተሳለጠ የባህር ትራንስፖርት እና የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል፡፡ በመሆኑም የሎጅስቲክስ በስትራቴጅ አለመመራት ሀገራችን ወደ ኢንዱስትሪ ለመሸጋገር የምታደርገውን ጉዞ በእጅጉ የሚያጓትት ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር ይህ ስትራቴጅ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በዓለም ገበያ ተወዳዳሪ በማድረግ ረገድ የማይተካ ሚና አለው ተብሎ ይታመናል፡፡

## 1.2.2. የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲዎቻችንና ስትራቴጅዎቻችን እና የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው ትስስር

በሀገራችን ገጠራማ አካባቢዎች ዕምርታዊ የግብርና ምርት እድገት እና ሁለንተናዊ የገጠር ትራንስፎርሜሽን በማስመዝገብ ላይ የሚገኘው የኢፌዴሪ መንግስት የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲ ስትራቴጅ ዋናው የእድገታችን ቁልፍ ሲሆን ይህ ፖሊሲ በዋናነት የሚያተኩርባቸው ዘርፎችም በገበያ የሚመራ የግብርና ልማት እንዲኖር ማድረግ፤ የገጠር ፋይናንስ ስርዓት ማሻሻል፤ የግል ባለሀብቶች በግብርና ልማት ዘርፍ በሰፊው እንዲሳተፉ ማበረታታት እና ሌሎችም ሲሆኑ ፖሊሲውን ይበልጥ ወደ መሬት ከማውረድ አንጻር የትራንስፖርት ሎጅስቲክሱን ማሻሻል እና የግብርና ግብዓቶችን በወቀቱ ማቅረብ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር የጭነት ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ስትራቴጂው የገጠርና ግብርና ልማት ፖሊሲን ከማሳካት አኳያ የራሱ የማይተካ ሚና ይኖረዋል ተብሎ ይታመናል፡፡ በተለይም በአርሶ አደሩ የሚመረቱ ለፋብሪካ የሚሆኑ የግብርና ጥሬ እቃዎችን በወቅቱ እና በተመጣጣኝ የሎጅስቲክስ ወጪ ለኢንዱስትሪዎች ማቅረብ፤ ከፋብሪካዎች የሚመረቱ የግብርና ግብዓቶችን ደግሞ ለአርሶ አደሩ በውቅቱ እና በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ ካልተቻለ የግብርና ልማት እና የኢንዱስትሪ ልማት ትስስር እጅግ በጣም የላላ እና የሀገራችንን እድገት በእጅጉ የሚጎዳ ይሆናል፡፡ ስለሆነም የትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ስትራቴጅን በሚገባ ቀምሮ ተግባራዊ ማድረግ አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ ለሀገራችን የምርጫ ጉዳይ አይደለም፡፡

## 1.2.3. የከተማ ልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች

በከተማ ልማት እና ቤቶች ሚኒስቴር አማካኝነት ተዘጋጅተው በመንግስት የጸደቁ በርካታ ፖሊሲዎች ያሉ ሲሆን እነዚህ ፖሊሲዎች መሰረት የሚያደርጉት በከተሞች የሚኖረውን ህዝብ ኑሮ ማሻሻል እና ከተሞች ውብ እና ጽዱ ሆነው በቂ የትራንስፖርት እና ሌሎች መሰረተልማት እንዲሚሉላቸው አቅጣጫ የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከጭነት ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ስትራቴጅው ጋር ይበልጥ ቁርኝት ያላቸውን የከተማ ፖሊሲዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### የከተማ ቤት አቅርቦት የስትሬቴጂ ማዕቀፍ

የከተሞች እድገት እየተስፋፋ የመምጣት እና የተጨማሪ ከተሞች መቆርቆር ወይም የገጠር አካባቢዎች ወደ ከተማነት መቀየር ክስተት ከተሞቻችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች የሚስተዋሉባቸውና ለነዋሪዎቻቸው በቂ

አገልግሎት መስጠት የተሳናቸው በመሆናቸው እነዚህን ችግሮች ማቃለል ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ሆኗል፡፡ በከተሞች ከሚታዩ ችግሮች መካከል ደግሞ የመኖሪያ ቤቶች እጥረት ዋነኛው ነው፡፡

የመኖሪያ ቤት ከሰው ልጅ መሰረታዊ ፍላጎቶች/መብቶች መካከል የሚመደብ ሲሆን የመጠለያ እጦትም የድህነት አንዱ መገለጫ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ በከተሞች ያለውን ችግር ለመፍታት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ አስተዳደሮች የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስዱ ቆይተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት በአዲስ አበባ ከተማ ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ እና በክልል ከተሞች ደግሞ ከ1999/2000 ዓ.ም ተግባራዊ በተደረገው የተቀናጀ የቤቶች ልማት ፕሮግራም ተከናውኗል፡፡ ሆኖም የቤቶች ግንባታው በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም፤ በፍላጐትና አቅርቦት መካከል ሰፊ ክፍተት አለ፡፡ ለዚህ ክፍተት የሚጠቀሱ ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም በዋናነት የግንባታ ግብአቶች አቅርቦት እጥረት እና የኮንስትራክሽን አቅም አናሳ መሆን አንዱ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሎጅስቲክስ ሂደቱ ቀልጣፋ አለመሆን የትራንስፖርት አቅርቦት በአይነትም በመጠንም ከገቢ እቃዎች ጋር የተጣጣመ አለመሆን ነው፡፡ ስለሆነም የከተማ ልማት የቤቶች አቅርቦት ፖሊሲ ዘመናዊ የሎጅስቲክስ ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት ያሰቀምጣል፡፡ ከዚህ አንጻር የፍሬት ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ስትራቴጅዉ እነዚህን ቁልፍ የሀገራችን ፖሊሲዎች ከማሳካት አንጻር ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የከተማ ሎጅስቲክስ /City Logistics/ ለሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እያቆጠቆጠ ያለ ሳይንስ /Emerging science/ በመሆኑ ለዚህ ዘርፍ ልዩ ትኩረት በመስጠት በከተሞች ውስጥ ያለው የጭነት ሎጅስቲክስ ፍሰት በትራፊክ ፍሰት ላይ ያለውን ጫና በሚያቃልል እና የከተሞችን እንቅስቃሴ /Mobility/ ቀልጣፋ በሚያደርግ መልኩ መምራት ወቅቱ የሚጠይቀው ጉዳይ ነው፡፡

## የከተማ ፕላን ዝግጅትና ትግበራ ስትራቴጂ

ከተሞች ልማትን ከማፋጠን አኳያ ከህዝብ ቀጥሎ ያላቸው አንዱና ትልቁ አቅም በከተሞች ውስጥ ያለው መሬት ነው፡፡ የከተማ ኘላን መሬትን በአግባቡ ለመጠቀም የማህበራዊ-ኢኮኖሚ ልማት ዕቅድን፣ የሀገር፣ የክልል፣ የንግድ ኮሪደሮችንና ማዕከሎችን ልማትና ዕቅዶችን መነሻ የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡ የከተማ ኘላን ሥራ የገጠር-ከተማና የከተማ-ከተማ ትስስርን በማጠናከር ለዘላቂ ልማት ጠቀሜታው የላቀ ነዉ፡፡ የከተማ ነዋሪው ህዝብ በከተማ ኘላን ዝግጅትና ትግበራ ሂደት ንቁ ተሳታፊ እና ባለቤት መሆኑንም የሚያረጋግጥ ሥርዓት መገንባት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ መሬትን በአግባቡ ለማስተዳደር መጀመሪያ የከተማውን

ወሰን ማወቅና አጠቃቀሙን በኘላን መወሰን ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም የከተማ ፕላን ሲዘጋጅ ምጣኔን ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚገባ በመርህነት ከተጠቀሱ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ ይህም ማለት 30% ለአረንጓዴና ለህዝብ የጋራ አገልግሎት የሚውል፤ 30% ለመንገድ፤ ተርሚናሎችና ሌሎች መሰረተ ልማቶች፤ 40% ለህንጻ ግንባታ (የመኖሪያ፣ የመስሪያ፣ የማምለኪያ፣ ወዘተ) የሚመለከት ነው፡፡ ይህን ፖሊሲ ከመተግበር አንጻር ከተጠቀሱ ችግሮች መካከል የከተማ-ከተማ ትስስር በንግድ፣ በትራንስፖርት፤ በጋራ ጉዳዮችና ተዛማጅ በሆኑ ኢንዱስትሪዎች እና ሎጅስቲክስ ማዕከላት ገና ብዙ ያላደገና ሊሰራበት የሚገባዉ ጉዳይ መሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም ጭነትፍሬት ትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ስትራቴጅው የሚተገበረው በመሬት ላይ በመሆኑ የከተሞችን የፕላን መዋቅር በሚገባ በመገንዘብ የሚገነቡ የሎጅስቲክስ ማዕከላት ይህንን የከተሞች የዞን አደረጃጀት እና የከተሞችን ደረጃ መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፡፡

### 1.2.4. የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅንነት ፖሊሲ ግቦች እና ብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ትስስር

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደኅነነት መነሻም መዳረሻም የኢኮኖሚ ልማትና ዴሞክራሲን እውን ማድረግ ነው፡፡ የኢኮኖሚ ዲኘሎማሲያችን ከሚያተኩርባቸው መስኮች አንዱ ለሀገራችን የገቢና ወጪ ንግድ ቀልጣፋ እና አስተማማኝ የትራንዚት እና ትራንስፖርት ኮሪደር እንዲኖር ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ከአፍሪካ ቀንድ አገሮች ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ስናነሳ ጎረቤቶቻችን ከሆኑት ስለ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፤ ኬንያ እና ደቡብ ሱዳን ማለታችን ነው፡፡

እነዚህ አገሮች የቅርብ ጎረቤቶቻችን እንደመሆናቸው መጠን ከአገራችን ጋር የቋንቋ፣ የባሕል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮ ሀብት ወዘተ…ግንኙነት አላቸው፡፡ በአገራችን የሚካሄደው ለውጥ እነሱን በቀጥታ ይነካል፣ በነሱ ውስጥ የሚከናወኑ ሁኔታዎችም እኛን በቀጥታ ይመለከታሉ፡፡ አገራችን በአሁኑ ወቅት ወደብ አልባ ስትሆን ከደቡብ ሱዳን በስተቀር ሁሉም ጐረቤቶቻችን ወደብ ያላቸውና የወደብ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ናቸው፡፡ ከዚህ በመነሳት ከጎረቤት አገሮች ጋር ጥብቅ ትስስር እንዳለን ተገንዝበን ከነዚህ አገሮች ጋር የሚያገናኘንን ትክክለኛ ፖሊሲ መቀየስ ይገባናል በማለት የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን ይተነትናል፡፡ በመሆኑም ጎረቤቶቻችን ባለወደብ፤ እኛ ወደብ አልባ በመሆናችን በኢኮኖሚ እየለማን ስንሄድ በዚያው መጠን ብቃት ያለው የወደብ አገልግሎት የሚያስፈልገን

መሆኑ ሌላው ጉዳይ ነው፡፡ አገሮቹ የወደብ አገልግሎት ለኢትዮጵያ ቢሰጡ ተጠቃሚ የምትሆነው ኢትዮጵያ ብቻ ሳትሆን እነሱም ናቸው፡፡ ይልቁንም አንዳንዶቹ ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት ባይሰጡ በኢኮኖሚያቸው ላይ በቀላሉ የማይገመት ችግር የሚፈጠርባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ከኢኮኖሚና ከጋራ ጥቅም አኳያ ከታየ የወደብ አገልግሎቱ በአስተማማኝ ሁኔታ ሊቀርብ የሚችልና የሚገባው ነው፡፡

በጥቅሉ ሲታይ አገሮቹ በኢኮኖሚያዊ እድገታችን ላይ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው በጎም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ ያላቸው አይደሉም፡፡ በዚህ ረገድ ክብደት የሚሰጠው ጉዳይ ቢኖር የወደብ አገልግሎት ሲሆን አደጋው ሁሉም ተባብረው ለኢትዮጵያ የወደብ አገልግሎት የከለከሉ እንደሆነ ወይም አገልግሎቱ በተለያየ ምክንያት ቀልጣፋ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡  እንደዚህ አይነቱ አደጋ ሊከሰት የሚችለውም በኢኮኖሚያዊ አዋጭነት መርህ ሳይሆን በፖለቲካ ግጭቶችና ቅራኔዎች ምክንያት ነው፡፡ ይህ የአሁኑን ነባራዊ ሁኔታ የሚገልጽ ሲሆን ከረጅም ጊዜ አኳያና ጎረቤት አገሮች በልማት እየገሰገሱ ሲሄዱ ግን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ገበያ ሊፈጥሩ ይችላሉ በማለት ስለ ወደብ አገልግሎት አቅርቦት ፖሊሲው አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው የተጨማሪ ኮሪደሮችን አጠቃቀም በተመለከተ ከረጅም እና ከአጭር ጊዜ አኳያ ልንተገብራቸው የሚገቡ በርካታ እርምጃዎችን (Interventions) በማካተት ቀርቧል፡፡

### 1.2.5. የ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ትስስር

የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ በመሰረታዊነት የመጀመሪያውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መነሻዎች፣ ዓላማዎችና የትኩረት አቅጣጫዎች የሚያስቀጥል ሆኖ ለየት የሚያደርጉት የራሱ ባህሪያት አሉት፡፡ እነሱም፡-

- ግብርና በዚህ ዕቅድ ዘመንም የልማታችንና ፈጣን ዕድገታችን የማይተካ አስተዋፅኦ የሚያደርግና የዘመናዊ አምራች ዘርፍ ዕድገት ዋና ምንጭ ሆኖ የሚቀጥል መሆኑ፤
- የግብርናው ዘርፍ ለውጥ ማምጣት የጀመሩትን የስትራቴጂክ የምግብ ሰብሎች ምርታማነትና ጥራት የበለጠ ከማሳደግ ባሻገር የላቀ ዋጋ የሚያወጡ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችና የኤክስፖርት ምርቶች ላይ የልማት ቀጠናን ማዕከል ያደረገ ርብርብ በማድረግ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፤

- የመስኖ ግብርና፣ የአበባ፣ የአትክልትና ፍራፍሬ እንዲሁም የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሥራን በከፍተኛ ደረጃ ማስፋፋት ላይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ፤

- የኢኮኖሚው የማምረት አቅም ላይ ለመድረስ ቅልጥፍና መጨመርና በአምራች ዘርፎች በሚመረቱ ምርቶች ለጥራት፣ ለምርታማነት እና ተወዳዳሪነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራና የተጀመረው ካይዘን በስፋትና በጥልቀት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል፣ የቤንች ማርኪንግ እንቅስቃሴም እንደሚስፋፋ ግልፅ ግቦች መቀመጣቸው፤

- በጠቅላላ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ለሚታየው መዛባት ልዩ ትኩረት መሰጠቱና ፈጣን እድገት የማስመዝገብ ግብም ይህን የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት ከማስተካከል አኳያ እንዲቃኝ ለማድረግ ልዩ ትኩረት መሰጠቱ፤

- ይህ መዛባት ሁለት መልክ ያለው ሲሆን በቁጠባና በኢንቨስትመንት መካከል ያለው ክፍተትና በወጪና በገቢ ንግድ መካከል ያለው ክፍተት እየሰፋ መሄዱ፤

- ይህን መዛባት ለማስተካከል የግልና የመንግስት ቁጠባን የማስፋፋትና የወጪ ንግድ ምርቶችን ምርታማነት ጥራትና ተወዳዳሪነት የማሣደግ እንቅስቃሴ ከመቸውም ጊዜ የላቀ ጥረት እንደሚጠይቅና ይህንንም ለማሳካት ግልፅ ግቦች መቀመጣቸው፤ ናቸው፡፡

ከዚህ አኳያ የሁለተኛው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሎጅስቲክሱን ከማሻሻል አንጻር የሚከተለውን የትኩረት አቅጣጫ አስቀምጧል፡፡

ይኸውም የተቀናጀ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ አገልግሎትን ማረጋገጥ ሲሆን ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ለትራንስፖርት ልማት በተሰጠው ትኩረት በመንገድ፣ በአቪየሽንና አየር ትራንስፖርት፣ በባህር ትራንስፖርትና ማሪታይም አገልግሎት፣ በቅርቡ ደግሞ በባቡር ትራንስፖርት ከፍተኛ ኢንቨስትመንት ተካሂዷል፡፡ በዚህም የአገራችን የትራንስፖርት ዘርፍ ጉልህ ዕድገት አስመዝግቧል፡፡ በቀጣዩ የዕቅድ ዘመን የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ዘርፉ ከዚህም በላይ መሠረታዊ ለውጥ እንዲያሳይ ለማድረግ ታቅዷል፡፡ ዘርፉ ከሚጠይቀው ከፍተኛ ሁለንተናዊ አቅም አንጻር ግልፅ በሆነ ራዕይና የተቀናጀ የትራንስፖርት ስትራቴጂ ወይም ማስተር ፕላን መመራት ይኖርበታል፡፡ ስለሆነም በቅድሚያ የእስካሁኑ አፈፃፀም፣ የቀጣዩ ጊዜ የልማት ራዕይ እና የዓለም ምርጥ ልምድን መሠረት በማድረግ

ወቅታዊ የሆነ የተቀናጀ አገራዊ የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ስትራቴጂ/ማስተር ፕላን መቀረፅ ይገባል፡፡ በዚህም መሰረት የትራንስፖርት አገልግሎት ቅልጥፍናን በማሳደግና የተቀናጀ የቅብብሎሽ ሥርዓት በመፍጠር የትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ እንዲሁም በትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት የግል ባለሃብቱን አቅም በመገንባት ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ይደረጋል፡፡ በገጠር እያደገ የመጣውን ምርት ከዋና ዋና የገበያ ማዕከላት ጋር የሚኖራቸውን ቁርኝት የማረጋገጥ፣ የግብርናና የገጠር ኢኮኖሚ መሠረቱ የሠፋና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ጥሬ ዕቃ ማቅረብ እንዲችል ከከተሞች ጋር የማስተሳሰር፣ የገጠር ቀበሌዎችንና ወረዳዎችን ከገበያ ማዕከላት ጋር እንዲመጋገቡ የሚያስችል የገጠር ትራንስፖርት ተደራሽነትን የማስፋፋት ተግባራት ትኩረት ተሰጥቷቸው ይከናወናሉ፡፡

በአገር ውስጥ የተገነቡት የደረቅ ወደብ አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ጥራት፣ ቅልጥፍናና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፣ ለገቢና ወጪ ምርቶች የምንጠቀምባቸውን የትራንስፖርት ኮሪደሮች በቂ አቅም እንዲኖራቸው ደረጃቸውን ማሻሻል፣ ማስፋፋትና ማሳደግ፣ የአገሪቱ አሉታዊ መገለጫ የሆነውን የመንገድ ትራፊክ ደህንነት ችግር መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ማድረግ በዚህ ረገድ የመንገዶች ዲዛይን የትራፊክ ደህንነትን ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፣ የትራንስፖርት ማኔጅመንት ሥርዓቱን በማሻሻል ቀልጣፋ የአገር አቋራጭ፣ የክልላዊና የከተማ ትራንስፖርትን በጥራትና በስፋት እንዲቀርብ ማድረግ፣ የመንገድ፣ የባቡር፣ የባህርና የአየር ትራንስፖርት ሥርዓትን በተቀናጀ ሁኔታ ማስፋፋት፣ የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት ግንባታና አገልግሎት ማስፋፋት የባለ ብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን (Cross cutting issues) ያገናዘበ እንዲሆን ማድረግ ከትኩረት አቅጣጫዎቹ በዋናነት የሚጠቀሱት ናቸው፡፡ የባህር ትራንስፖርትና ሎጀስቲክስ አገልግሎት አገሪቱ ለነደፈችው የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ትራንስፎርሜሽንና የኤክስፖርት ልማት መስፋፋት ከሚጫወተው ቁልፍ ሚና አኳያ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን የባህር ትራንስፖርት ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እውን ለማድረግ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የሚከናወኑ የሺፒንግ፣ ሎጂስቲክስና ድጋፍ ሰጪ ዋና ዋና ተግባራትን በተቀናጀ ሁኔታ ለአገልግሎት ሰጪና ለተገልጋይ አካላት የተሟላ፣ ወጥነት ያለው፣ ወቅታዊና /Real Time/ ተደራሽ የሆነ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት እንደሚዘረጋ በእቅዱ ተካቷል፡፡

ስለሆነም የሎጅስቲክስ ስትራቴጅው ሁለተኛውን አገራዊ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን አቅድን ከማሳካት አንጻር በተለይም ደግሞ ለኤክስፖርት

አምራች ኢንዱስትሪው ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ የሎጅስቲክስ ስርዓት ከመዘርጋት አንጻር፤ ለግብርና ልማት ስራችን ወቅቱን የጠበቀ እና በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ የግብርና ግብዓት ከማቅረብ አንፃር፤ በዘርፉ የሚታየውን የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር በአሰራር ከማስወገድ አንጻር ከፍተኛ ድርሻ እንደሚኖረው ታምኖበታል።

## 1.3. የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂ አዘገጃጀት

የሎጅስቲክስ ስትራቴጂው በመነሻነት ከተባበሩት መንግስታት የልማት ኘሮግራም (UNDP) በተደረገ የፋይናንስ ድጋፍ ናታን (NATHAN Asocciates Inc.) በተባለ ዓለም አቀፍ የጥናት ኩባንያ የቀረበ መነሻ ጥናት ነበር። ይህን ጥናት መነሻ በማድረግ የሚዘጋጀውን የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ከኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ ተጨባጭ ሁኔታ ይበልጥ ለማጣጣምና በዋናነት ደግሞ በትክክለኛ የመረጃ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ የችግሮች ትንታኔ (Comprehensive Diagnosis) ላይ እንዲመሰረት ለማድረግ የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን የሎጅስቲክስ ባለሙያዎችን ያሰባሰበ የጥናት ቡድን በማቋቋም ሰፊ ጥናት አካሂዷል። ጥናቱ የተሟላና በሰፊ ትንታኔ ላይ የተመሰረተ ለማድረግ ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን የሎጅስቲክስ ሂደት በዋና ዋና ሂደቶች በመከፋፈል ለመለየት ጥረት ተደርጓል። በዚህም መሰረት የገቢና የወጪ ዕቃዎች በአምስት ዋና ዋና የሥራ ሂደቶች ከታች በሠንጠረዥ 1 በተመለከተው መንገድ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 1- የገቢና ወጪ እቃዎች ዋና ዋና ሂደቶች




በመሆኑም በእያንዳንዱ ሂደት ከሚመለከታቸው አካላት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን፡-

- በዘርፉ ከሚገኙ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ተቆጣጣሪ ተቋማት እና ተጠቃሚዎች መረጃ የማሰባሰብና የትንታኔ ሥራ ተካሂዷል።

- በበርካታ ተቋማት ሪፖርት ላይ የተመሠረተ ግምገማ ተካሂዷል፡፡
- በዓለም ዓቀፍ ተቋማትና በልዩ ልዩ የመንግሥት መ/ቤቶች በሎጅስቲክስ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡
- በሎጅስቲክስ የዓለም ዓቀፍ ተሞክሮዎች ተወስደዋል፡፡

በዚህ ሂደት በተዘጋጁ ረቂቅ ሰነዶች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር አራት የምክክር መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ በሂደት ሰነዱን የማዳበር ሥራ ተሰርቷል፡፡

በአጠቃላይ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ሰነዱ ይህን ሂደት በመከተል የተዘጋጀና በሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ላሉት በርካታ ማነቆዎች የመፍትሄ ፖኬጅ ሊሆን በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ነው፡፡ ስትራቴጂው በኢንዱስትሪው የሚገኙ ባለድርሻዎች የተወያዩበትና ያመኑበት ነው፡፡ የልማት አጋሮቻችን አስተያየትም የተካተተበትና በመጨረሻም ለትራንስፖርት ሚ/ር ቀርቦ አቅጣጫ በተሰጠው መሠረት ተስተካክሎ የተዘጋጀና በሚ/ር መ/ቤቱ የታመነበት ሰነድ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት:

## የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም

የሀገራችን የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ ግምገማ በሁለት መንገድ ታይቷል፡፡ እነርሱም፡-

1ኛ/ በዓለምአቀፍ ተቋማት ስለ ኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም የሚወጡ ሪፖርቶች እና፣

2ኛ/ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ መረጃን መሠረት ያደረገ ትንታኔ ናቸው፡፡


### 2.1. የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ ከዓለም አቀፍ ተቋማት ሪፖርቶች አንጻር፤

በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገሮች የሎጅስቲክስ ሥርዓታቸው ያለበት ሁኔታን የሚዳሰሱ የተለያዩ ጥናቶችና ሪፖርቶች በየጊዜው የሚዘጋጁ ሲሆን፣ በዚህ ረገድ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ያለበት ደረጃን ለመገንዘብ እንዲቻል የሚከተሉት ሶስት ዓለምአቀፍ ሪፖርቶች ታይተዋል፡፡ እነርሱም፡-

#### 2.1.1. በዓለም ባንክ የሚዘጋጀው የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያ (LPI)

በርካታ ሀገሮች የሎጅስቲክስ አፈጻጸምን ለማሻሻል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችና ስልቶችን ለመቀየስ በመነሻነት የሚጠቀሙት ጥናትና ሪፖርት በየሁለት ዓመቱ በዓለም ባንክ የሚዘጋጀው የሎጅስቲክስ አፈጻጸም መለኪያ ሪፖርት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ሪፖርት መሰረት የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም (LPI) ደረጃ በተመለከተ በሎጅስቲክስ አፈጻጸም ኢንዴክስ (LPI) በዓለም ቀዳሚ ከሆነው ሀገር ጀርመንና በጣም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ ጥቂት ወደብ አልባ ሀገሮች ጋር በማነጻጸር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ስዕል 2- የዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያ




የመረጃ ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ሪፖርቶች (እ.ኤ.አ ከ2010 - 2016)

እ.ኤ.አ የ2016 የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም በ6ቱ መለኪያዎች ከሌሎች ሀገሮች ጋር በማነጻጸር በሠንጠረዥ 2.1 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2.1- የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ አፈፃፀም ንፅፅር በ6ቱ ዋና መለኪያዎች

| ሀገራት | LPI ደረጃ (/160) | LPI ነጥብ (5) | 6 ዋና መለኪያዎች (2016) | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ጉምሩክ | መሰረተ ልማት | ዓለማቀፍ ጭነት | የሎጂስቲክ ብቃት | ክትትል (Tracking & tracing) | ጭነትን በወቅቱ ማድረስ |
| ጀርመን | 1 | 4.24 | 4.12 | 4.44 | 3.86 | 4.28 | 4.27 | 4.45 |
| ሉክሰምበርግ | 2 | 4.22 | 3.90 | 4.24 | 4.24 | 4.01 | 4.12 | 4.80 |
| ኡጋንዳ | 58 | 3.04 | 2.97 | 2.74 | 2.88 | 2.93 | 3.01 | 3.70 |
| ኬንያ | 42 | 3.33 | 3.17 | 3.21 | 3.24 | 3.24 | 3.42 | 3.70 |
| ታንዛንያ | 61 | 2.99 | 2.78 | 2.81 | 2.98 | 2.92 | 2.98 | 3.44 |
| ሩዋንዳ | 62 | 2.98 | 2.93 | 2.62 | 3.05 | 2.87 | 3.04 | 3.35 |
| ቡርኪናፋሶ | 81 | 2.73 | 2.55 | 2.67 | 2.73 | 2.78 | 2.49 | 3.13 |
| ሱዳን | 103 | 2.52 | 2.23 | 2.20 | 2.57 | 2.36 | 2.49 | 3.28 |
| ቡሩንዲ | 107 | 2.50 | 2.02 | 1.98 | 2.42 | 2.46 | 2.6883 | 3.45 |
| ዛምቢያ | 114 | 2.42 | 2.25 | 2.26 | 2.51 | 2.42 | 2.36 | 2.74 |
| ኢትዮጵያ | 126 | 2.37 | 2.60 | 2.12 | 2.56 | 2.37 | 2.18 | 2.37 |

የመረጃ ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ሪፖርቶች (እ.ኤ.አ 2016)

የኢትዮጵያ LPI በቀላል ማኑፋክቸሪንግ የሀገራችን ተወዳዳሪ ከሆኑ አምስት ሀገራት LPI ጋር በማነጻጸር ደግሞ በሠንጠረዥ 2.2 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2.2- የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ አፈፃፀም በቀላል ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ተወዳዳሪ ከሆኑ ሀገሮች (LPI) ንጽጽር

| ሀገራት | 2016 | | 2014 | |
|---|---|---|---|---|
| | LPI ደረጃ (160) | LPI ነጥብ (5) | LPI ደረጃ (160) | LPI ነጥብ (5) |
| ቻይና | 27 | 3.66 | 28 | 3.53 |
| ቦትስዋና | 57 | 3.05 | 120 | 2.49 |
| ቬትናም | 64 | 2.98 | 48 | 3.15 |
| ካምቦዲያ | 73 | 2.80 | 83 | 2.74 |
| ባንግላዴሽ | 87 | 2.66 | 108 | 2.56 |
| ኢትዮጵያ | 126 | 2.37 | 104 | 2.59 |

የመረጃ ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ሪፖርቶች (እ.ኤ.አ 2016)

ከስዕሉም ሆነ ከሁለቱ ሠንጠረዦች ለመገንዘብ የሚቻለው፡-

1. የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ፣ (ከ160 ሀገራት 126ኛ ላይ መሆኑ)፤
2. በሎጅስቲክስ አፈጻጸም አብዛኛው ሀገሮች ደረጃቸው እየተሻሻለ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ ግን በተቃራኒ እያሽቆለቆለ መሆኑ፤
3. የሀገራችን የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ በቀላል ማኑፊክቸሪንግ ዘርፍ ከሀገራችን ተወዳዳሪ ከሆኑት ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር የመጨረሻ መሆን ብቻ ሳይሆን በብዙ ርቀት ወደ ኋላ የቀረ መሆኑ፤
4. በቅርቡ በወጣው የ2018 ሪፖርት የኢትዮጵያ ደረጃ ፈጽሞ ያልተገለጸ ሲሆን ከ2012 - 2018 (Agreggeted LPI) ሪፖርት ላይ የኢትዮጵያ ደረጃ ከ126ኛ ወደ 131ኛ ዝቅ ያለ መሆኑ ታይቷል፡፡

### 2.1.2. የዓለም የወደብ አልባ ሀገሮች የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ግምገማዊ ሪፖርት

በዓለም ላይ 42 ሀገራት ወደብ አልባ ሲሆኑ፣ ይህን ልዩ ሁኔታ ያገናዘበ የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓታቸውን ለመደገፍ የተነደፈ ኘሮግራም አለ፡፡ ባሁኑ ወቅት VPOA (Viena Program of Action) በሚል ስያሜ የተዘጋጀው ኘሮግራም በትግበራ ላይ ሲሆን፣ ይህን ዓለም አቀፍ ኘሮግራም የሚከታተለው አካል የየሀገራቱ የትራንዚት ትራንስፖርት አሠራር ግምገማዊ ሪፖርት አውጥቷል፡፡ በዚህ ሪፖርት የኢትዮጵያ የትራንዚት ትራንስፖርት ሥርዓትን በሚመለከት የመንገድ፣ የመሠረተ-ልማትና ሌሎች የሎጅስቲክስ ፋሲሊቲዎች መገንባቱን፣ ከጐረቤት ሀገሮች የወደብ አጠቃቀም ስምምነቶች መደረጋቸውና ጥሩ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ የተሻለ መሆኑን ጠቅሶ መሠል ጥረቶች በመንግስት በኩል የተደረገ ቢሆንም ከሚጠበቀው ውጤት አንጻር ሲታይ ሰፊ ክፍተት መኖሩ ግምገማዊ ሪፖርቱ አመልክቷል፡፡

### 2.1.3. የዓለም ኢኮኖሚክ ፎረም (World Economic forum)

የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም በሚያወጣው ባለ አራት ነጥብ ኢንዴክስ መሰረት የሀገራችን ደረጃ ዝቅተኛ እንደሆነ ያሳያል፡፡ የሚከተለው ሰንጠረዥ ይህንኑ እውነታ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 2.3 - የኢትዮጵያ የዓለም ኢኮኖሚ ኢንዴክስእ.ኤ.አ (2014-15)

| አመላካቾች | ደረጃ ከ 144 ሀገራት | ውጤት (1-7) |
|---|---|---|
| ፈጻሚ ተቋማት | 96 | 3.5 |
| መሰረተ ልማት | 125 | 3.5 |
| የቴክኖሎጅ ዝግጅት | 133 | 2.5 |
| ማክሮ ኢኮኖሚክ ኢንቫይሮመንት | 95 | 4.4 |

የመረጃ ምንጭ፡- የዓለም ባንክ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ሪፖርቶች (እ.ኤ.አ 2016)

### 2.1.4. የዓለም አቀፍ ሪፖርቶች ማጠቃለያ

ከላይ ከተመለከቱት ዓለም አቀፍ የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ መለኪያዎችና ሪፖርቶች አኳያ የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ደረጃ በሁሉም መስፈርቶች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ መሆኑ ታይቷል፡፡

## 2.2. የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ ወጪና ጊዜ ትንታኔ

የሎጅስቲክስ ሥርዓት ሶስቱ ቁልፍ መለኪያዎች ወጪ፣ ጊዜና የአገልግሎቱ አስተማማኝነት ናቸው፡፡ የሀገራችንን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ለመፈተሽና የአፈጻጸም ደረጃውንም በተሟላ መልኩ ለመገንዘብ እንዲቻል የገቢና የወጪ ዕቃዎች የንግድ ሂደትን በአምስት ዋና ዋና ሂደቶች በመከፋፈል እና ከሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ አንጻር በእያንዳንዱ የሥራ ሂደት ሥርዓቱ ያሉበት ችግሮች፣ የችግሮቹ መገለጫዎችና መንስኤዎቹን በዝርዝር የመተንተን ሥራ ተሰርቷል፡፡ ከዝርዝር ትንታኔና የአፈጻጸም ግምገማው በመነሳት ግኝቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

#### የገቢና የወጪ ዕቃዎች መጠን

ባሁኑ ወቅት የሀገራችን የገቢ ዕቃዎች ዓመታዊ መጠን 14 ሚሊዮን ቶን የደረሰ ሲሆን፣ በዋና ዋና የጭነት ዓይነት ሲከፋፈሉ የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

- የኮንቴይነር መጠን 3.2 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ሲሆን ይህም 23% ድርሻ አለው፤
- የደረቅ ብትን ጭነት 4 ሚሊዮን ቶን ሲሆን 28% ድርሻ አለው፤
- የነዳጅ ጭነት 4.1 ሚሊዮን ቶን ሲሆን ይህም 29% ድርሻ አለው፤
- የብረት ጭነትና ሌሎች ጀነራል ዕቃዎች 2.9 ሚሊዮን ቶን ሲሆን 20% ድርሻ አለው፡፡

የወጪ ዕቃዎችም በዓመት 2 ሚሊዮን ቶን የደረሰ ሲሆን፣ በጅቡቲ በኩል ወደ ዓለም ዓቀፍ ገበያ የሚላከው መጠን ዓመታዊ ግምቱ 65,000 ኮንቴይነር ወይም 1.3 ሚሊዮን ቶን ደርሷል፡፡

የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪን ከመተንተን አኳያ የገቢ ዕቃዎች በአንጻራዊ የኮንቴይነር ጭነትን ዘርዘር ባለመልኩ ሌሎቹ ደግሞ የኦፐሬሽን ባህሪያቸው

በተወሰነ መልኩ የሚለያይ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ጭነት አጠር ያለ የመረጃ ትንታኔ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## 2.2.1. የሎጅስቲክስ ጊዜ (Logistics Time)

የሎጅስቲክስ ጊዜን የሚወስኑ በርካታ ሁኔታዎች (factors) ያሉ ሲሆን፣ ከነዚህም መካከል የማጓጓዣ ዓይነት፣ የትራንስፖርት ሥርዓት፣ የጭነት መነሻና የጭነት መድረሻ ቦታዎች ይገኙበታል፡፡ የሎጅስቲክስ ጊዜ በዕቃዎቹ ፍሰት ወይም የማጓጓዝ ሂደት ውስጥ ያሉት በርካታ ተግባራትን ለማከናወን የሚወሰደው አማካይ ጊዜ ነው፡፡ ለዚህ ትንታኔ የገቢ ዕቃዎች በአስመጪው የዕቃ ትዕዛዝ (order) ከመጠየቅ ጀምሮ ጭነቱ እስከመረከብ ያለው ተወስዷል፡፡ የወጪ ዕቃዎች ደግሞ በላኪው የወጪ ምርቱን ለመላክ ዝግጁ ከማድረግ ጀምሮ ጭነቱን መድረሻ ባህር ወደብ ለማድረስ የሚወስደው አማካይ ጊዜ /በቀናት/ ተወስዷል፡፡ ይህን የበርካታ ሀገሮች የሎጅስቲክስ ጊዜ የአፈጻጸም መለኪያ መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ ጊዜን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ በዚሁ መሠረት ከታች እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

### *2.2.1.1. የገቢ እቃዎች (Import)*

#### የኮንቴይነር ጭነት

ሀ) ጭነት ከማዘዝ እስከ መረከብ የሚወስደው ጊዜ (Lead Time)

የገቢ እቃን ለማስመጣት ከባንክ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ጥያቄ ጀምሮ ኤል ሲ ከፍቶ ለሻጭ መላክን ከዚያም ሻጭ እቃውን አዘጋጅቶ መነሻ ወደብ በማድረስ በመርከብ ላይ መጫንን ጨምሮ በመድረሻ ወደብ የሚከናወኑ ተግባራትንና ወደ ሀገር ውስጥ በየብስ ማጓጓዝን፣ የጉምሩክ ስነስርአትን አጠናቆ አስመጪው እስኪረከብ ድረስ ያለውን ጊዜ በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ “Lead time” የዕቃው አቅራቢ ምርቱን ለማዘጋጀት መጫኛ ወደብ ድረስ ማጓጓዝን የሚያካትት ቢሆንም ይህ ሂደት ለሁሉም ሀገሮች ተመሳሳይ በመሆኑ በዚህ ሂደት ውስጥ አልተካተተም፡፡ በመሆኑም የሀገራችንን ‘’Lead Time’’ ለማስላት የሚከተሉት ታሳቢዎች ተወስደዋል፡፡ እነርሱም፡-

- የጭነቱ መነሻ ሻንጋሀይ/ቻይና
- ማራገፊያ ባህር ወደብ ጅቡቲ
- አንድ ባለ20 ጫማ የኮንቴይነር ጭነት

- ዕቃው አደገኛ ዕቃ ያልሆነ (Non-Dangereous Cargo)
- የጭነቱ መድረሻ ቦታ አዲስ አበባ ሲሆን

በዚሁም መሠረት ጭነቱ በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓትና በዩኒ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት በመለየት ከታች በሠንጠረዥ 2.4 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2.4፡- የገቢ ዕቃዎች አጠቃላይ የሎጅስቲክስ ጊዜ በሥራ ሂደት የተከፋፈለ መረጃ

| የሚከናወኑ ተግባራት | ዩኒ ሞዳል | | የመልቲ ሞዳል | |
|---|---|---|---|---|
| | ጊዜ በቀናት | በ% | ጊዜ በቀናት | በ% |
| በባንክ የውጭ ምንዛሪ መጠየቅና ኤልሲ መክፈት | 45 | 37 | 45 | 40 |
| በመጫኛ ወደብ ላይ መርከብ መጠበቅ | 10 | 8 | 10 | 9 |
| በባህር ላይ በመርከብ ማጓጓዝ | 25 | 20 | 25 | 23 |
| በመድረሻ የባህር ወደብ የቆይታ ጊዜ | 37 | 30 | 6 | 5 |
| በየብስ ወደ ሀገር ውስጥ ማጓጓዝ | 3 | 2 | 3 | 2 |
| በደረቅ ወደብ የቆይታ ጊዜ * | - | - | 19 | 17 |
| የጉምሩክ ስነስርአት ማጠናቀቅና እቃ መረከብ | 3 | 3 | 4 | 4 |
| ድምር | 123 | 100 | 112 | 100 |

የመረጃ ምንጭ፡- ማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ከተጠቃሚዎች የተጠናቀረ ሪፖርት

*በደረቅ ወደቡ ውስጥ የቆይታ ጊዜያቸው ከ60 ቀናት በላይ የሆኑ ኮንቴይነሮችን አይጨምርም፡፡ እነዚህን ያካተተ ሲሆን በአማካይ 59 ቀናትነው፡፡

ከሠንጠረዡ ለመገንዘብ የሚቻለው በሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ጭነት ለመረከብ በአማካይ አራት ወራት እንደሚያስፈልግ ያመለክታል፡፡ ይህ ከዓለም አቀፍ አሠራር አኳያ ሲታይ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገሮች አማካይም የሀገራችን በእጥፍ ከፍ ይላል፡፡ በዚህ ሂደት

ከፍተኛውን ድርሻ (65%) የያዘው በባንክ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድና የዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ነው፡፡

ከዚህ አኳያ ጭነቱ በመጫኛ ወደብ (Port of Loading) ለመርከብ ጭነት ዝግጁ ከሆነበት ቀን እስከ መረከብ ድረስ የሚወስደው ጊዜ በአማካይ 78 ቀናት ሆኗል፡፡ እንዲሁም ጭነቱ በመድረሻ የባህር ወደብ ላይ (Port of Destination) ከመርከብ ከተራገፈበት ቀን እስከ መረከብ የሚወስደው ጊዜ በአማካይ 42 ቀናት ሆኗል፡፡ ከመርከብ ከተራገፈበት እስከ መረከብ ያለው የትራንዚት ጊዜ የሚያካትተው ጭነቱን ከባህር ወደብ/ጅቡቲ/ ለማንሳት አስመጪው እንቅስቃሴ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እስከ መረከብ ድረስ የሚወስደው ጊዜ ነው፡፡ በዩኒሞዳል የባህር ወደብ ፎርማሊቲዎችን አጠናቆ በየብስ አጓጉዞ የጉምሩክ ስነ ስርአትን በማጠናቀቅ እቃው መረከብን የሚያካትት ነው፡፡ በመልቲሞዳል ደግሞ የባህር ወደብ ፎርማሊቲን አጓጓዙ አጠናቆ በየብስ አጓጉዞ ደረቅ ወደብ ማድረስንና ባለእቃው ደግሞ የደረቅ ወደብና የጉምሩክ ስነስርአትን አጠናቆ እቃውን እስከ መረከብ ድረስ ያለውን ጊዜ ያካተተ ነው፡፡ መረጃው በሠንጠረዥ 2.5 ተመልክቷል፡፡

ሠንጠረዥ 2.5 - የትራንዚት ጊዜ

| የሚከናወኑተግባራት | የሚወስደው ጊዜ በቀናት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ዩኒሞዳል | | | መልቲሞዳል | |
| | ጥቅል እቃ | ኮንቴነር | ተሽከርካሪ | ኮንቴነር | ተሽከርካሪ |
| ከኢትዮጵያ ጉምሩክ የትራንዚት ፍቃድ ማግኘት | 2 | 2 | 2 | --- | --- |
| በጂቡቲ የጉምሩክ ስነስርዓት ማጠናቀቅ | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 |
| በጂቡቲ ከመርከብ ወኪል የእቃ መልቀቂያ ማግኘት | 1 | 1 | 3 | 1 | 3 |
| በወደብ እቃ ርክክብ ማጠናቀቅ | 1 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| የጭነት ማጓጓዣ መመደብና የወደብ መግቢያ መቀበል | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| እቃ መጫንና የየብስ የጉዞ ሰነድ ማዘጋጀት | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 |
| ጭነቱን ወደ ሀገር ውስጥ ማጓጓዝ | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| በመድረሻ ስፍራ የጉምሩክ ስነስርዓት አጠናቆ እቃ መረከብ | 2 | 1 | 2 | 4 | 4 |
| ድምር | 14 | 12 | 17 | 12 | 15 |

የመረጃ ምንጭ፡- ማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ከተጠቃሚዎች የተጠናቀረ ሪፖርት

በአጠቃላይ የኮንቴነር ጭነት ሲታይ የወደብ ላይ ቆይታ በጅቡቲ 37 ቀናት፣ በሞጆ 59 ቀናት ሆኗል፡፡

## ደረቅ ብትን ጭነት

የብትን ጭነት ማዳበሪያ፣ የግዥ ስንዴ፣ የእርዳታ እህል፣ ከሰልና ስኳርን የሚያካትት ሲሆን፣ ዓመታዊ ግምቱ 4 ሚሊዮን ቶን ደርሷል፡፡ ይህም ከውጭ ንግዳችን የ28% ድርሻ አለው፡፡

ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ደረቅ የብትን ጭነት ውስጥ ከ80% በላይ የመንግስት ግዥ ነው፡፡ የመንግስት የብትን ጭነት የሚመራበት አሠራር በሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው፡፡ የዚህ ጭነት አጠቃላይ ዋጋ በተደረገ ግምገማ (Assessment) ብር 6 ቢሊዮን እንደሚሆን ይገመታል፡፡ የሎጅስቲክስ ወጪ አማካይ በቶን 103 የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፣

- $30/ton (29%) ለባህር ማጓጓዣ፣
- $21/ton (20%) ለወደብ አገልግሎት፣
- $52/ton (51%) ለመንገድ ትራንስፖርት ነው፡፡

ስለሆነም የመንግስት የደረቅ ብትን ጭነት የሎጅስቲክስ ወጪ ዓመታዊ አማካኝ 257.5 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ወይም 5.6 ቢሊዮን ብር ነው፡፡ ይህ የእቃው ዋጋንና ሌሎች የሎጅስቲክስ ወጭዎችን ሳይጨምር ነው፡፡ የመርከቦች የባህር ላይ የቆይታ ጊዜ በአማካይ 15 ቀናት ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ከ2--3 ወራት በላይ በባህር የመቆየት ሁኔታም ይከሰታል፡፡

የዚህ ጭነት “Lead time” ወጥነት የጐደለው ብቻ ሳይሆን አንዳንዴ ከ6 ወራት በላይ ይወስዳል፡፡ ከ “Lead time” ፣ ከመርከብ የባህር እና የወደብ ላይ ቆይታና ከመሰል የብትን ጭነት የሎጅስቲክስ አፈጻጸም መለኪያ የሀገራችን ለንጽጽር እስከማይመች ድረስ በአጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ዋናው መንስኤ የገንዘብ፣ የመረጃ፣ የዕቃ ፍሰቱን በተቀናጀና በተናበበ መልኩ በብሄራዊ ደረጃ በትክክለኛ ዕቅድ ያለመምራት ነው፡፡

## የነደጅ ጭነት

የነዳጅ ጭነት በጅቡቲ ወደብ በኩል የሚገባው በዓመት 4.1 ሚሊዮን ቶን የደረሰ ሲሆን፣ በዚህ ጭነት ኦፐሬሽን ላይ ያሉት ዋና ዋና ችግሮች፡-

- የጅቡቲ ወደብ የማስተናገድ ዓቅም ማነስ
- የጅቡቲ ወደብ ዋጋ ውድነት
- ስርቆትና የመርከብ ዲመሬጅ ሲሆን፣ ለዚህም ከጭነቱ ባህሪይና ውድ ከመሆን አኳያ በባህር ማጓጓዝ ከወደብ የማስተናገድ ዓቅምና በማጓጓዝ አሠራሩ ላይ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችን የሚፈታ የፋሲሊቲና ደህንነቱ የተጠበቀ የማጓጓዝ ሥርዓት መዘርጋት የግድ የሚል ነው፡፡

## የብረትና ሌሎች ጀነራል ዕቃዎች

የብረትና ሌሎች የጀነራል ዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ከ30 ቀናት በላይ ነው፡፡ ይህም ለተለያዩ ወጪዎች የሚዳርግ ብቻ ሳይሆን በዕቃ ጥራትም በተለይም በብረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው፡፡

ለዚህ መንስኤው ከሆኑት ውስጥ፡-

- የአስመጪዎቹ የገንዘብ እጥረት
- ዕቃ ወደብ ከደረሰ በኋላ የገበያ ፍለጋ ሥራና
- የክትትል ማነስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለ) የጭነት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች በአመት የሚሸፍኑት ርቀት (truck millage)

የጭነት ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎች በአመት የሚሸፍኑት ርቀት በጨመረ ቁጥር ከወደብ እቃን በፍጥነት የማንሳት አቅም ይጨምራል፡፡ የሀገራችን የጭነት ተሽከርካሪዎች በአመት የሚሸፍኑት ርቀት በአማካይ 60,000 — 80,000 ኪሎ ሜትር ብቻ በመሆኑ ከወደብ እቃን በሚፈለገው ፍጥነት ማንሳት አዳጋች ሆኗል፡፡

### *2.2.1.2. የወጪ ዕቃዎች (Export)*

የወጪ ዕቃዎች የሎጅስቲክስ ጊዜ መረጃ ከታች በሠንጠረዥ 2.6 የተመለከተ ሲሆን፣ ሠንጠረዡን ለማዘጋጀት የሚከተሉት ታሳቢዎች ተወስደዋል፡፡ እነርሱም፡-

- አንድ ባለ 20 ጫማ ኮንቴይነር
- ክብደቱ ከ20 ቶን ያልበለጠ
- የቡና ጭነት
- በጅቡቲ ወደብ ላይ ዕቃው በኮንቴይነር ታሽጐ የተላከ
- መነሻ ቦታ አዲስ አበባ
- መድረሻ ቦታ ሀምበርግ/ጀርመን

ሠንጠረዥ 2.6 - የወጪ እቃዎች የሎጅስቲክስ ጊዜ

| ወጪ እቃን በመላክ ሂደት ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት | የሚወስደው ጊዜ /በቀናት/ |
|---|---|
| የባንክ ፈቃድ ማግኘት | 2 |
| የጉምሩክ ፈቃድ ማግኘትና በየብስ ማጓጓዣ መጫን | 1 |
| ወደ ጂቡቲ በየብስ ማጓጓዝ | 3 |
| የጂቡቲ ጉምሩክና የወደብ ፎርማሊቲ አጠናቆ በኮንቴነር ማሸግ | 2 |
| መርከብ መጠበቅና መጫን | 5 |
| በባህር ወደ ሀምበርግ ወደብ (ጀርመን ) ማድረስ | 23 |
| ድምር | 36 |

የመረጃ ምንጭ፡- በማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን ከተጠቃሚዎች የተጠናቀረ ሪፖርት

## 2.2.2. የሎጂስቲክስ ወጪ (Rates and Cost Indicators)

የገቢና ወጪ ዕቃዎች የሎጂስቲክስ ወጪ የተተነተነው የሎጂስቲክስ ወጪ ሞዴል በማዘጋጀት ሲሆን ሞዴሉ የተዘጋጀው በተለያዩ አገሮች የሎጂስቲክስ ወጪዎች ሞዴል ላይ በመመስረት ነው፡፡ እነዚህም አገሮች ደቡብ አፍሪካ፣ ደቡብ ኮሪያ፣ አሜሪካና ኢንዶኔዥያ ናቸው፡፡

### 2.2.2.1. ገቢ ዕቃዎች (Import)

#### አጠቃላይ ወጪ

የገቢ እቃን ለማስመጣት ከባንክ የውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ጥያቄ ጀምሮ ኤል ሲ ከፍቶ ገዢ እቃውን እስኪረከብ ድረስ ያለውን አጠቃላይ ወጪ በዩኒሞዳልና መልቲ ሞዳል ተለይቶ በሠንጠረዥ 2.7 እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡የገቢ እቃን አጠቃላይ የሎጂስቲክስ ወጪ ለማስላት የሚከተሉት ታሳቢዎች ተወስደዋል፡፡

እቃው የተገዛበት ዋጋ 40,000 የአሜሪካን ዶላር፣ በአንድ ባለ 20 ጫማ ኮንቴነር የታሸገ ክብደቱ ከ20 ቶን ያልበለጠ፣ አደገኛ ኬሚካል ያልሆነ፣ የእቃው መነሻ ወደብ ሻንጋይ (ቻይና)፡፡

#### የማጓጓዣ ወጪ

የማጓጓዣ ወጪ እቃው ለአስመጪው እስኪደርስ ድረስ በባህርና በየብስ ለማጓጓዝ እንዲሁም በየመሀሉ ለባህርና ለደረቅ ወደቦች የሚወጣውን ወጪ ያካተተ ነው፡፡ የዚህ ወጪ ዝርዝር በሠንጠረዥ 2.7 ከዚህ በታች ተጠቃሎ ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2.7 - የማጓጓዣ ወጪ በአሜሪካን ዶላር

| የወጪ ዝርዝር | በዩኒሞዳል | | በመልቲሞዳል | |
|---|---|---|---|---|
| | | መቶኛ | | መቶኛ |
| የባህር ላይ ማጓጓዣ | 725 | 28 | 725 | 30 |
| የጁቡቲ ወደብ አገልግሎት | 650 | 25 | 600 | 25 |
| ወደ ሀገር ውስጥ የየብስ ማጓጓዣ ወጪ | 1127 | 43 | 1000 | 41 |
| የደረቅ ወደብ የሀገር ውስጥ የአገልግሎት ክፍያዎች | 100 | 4 | 113 | 4 |
| ድምር | 2602 | 100 | 2438 | 100 |

የመረጃ ምንጭ፡- ከማ.ጉ.ባ የሎጅስቲክስ ችግሮች ትንታኔ ሰነድ የተወሰደ

ከላይ የተመከተው የትራንስፖርት /የወደብ ሀንድሊንግን ጨምሮ/ ወጪ ሲሆን፣ የሎጅስቲክስ ወጪው ማለትም፡-

- ከላይ የተመለከተው የትራንስፖርት ወጪ
- የL/C ክፍያ
- የኢንሹራንስ ክፍያ
- ለኮንቴይነር የመጋዘንና የዲመሬጅ ወጪ እና

ሌሎች የአስተዳደር ወጪዎችን ያካተተ ለአንድ ባለ 20 ጫማ ኮንቴይነር በአማካይ 4500 የአሜሪካን ዶላር ወጪ ይደረጋል።

## የወደብ አገልግሎት ወጪ

የወደብ አገልግሎት ወጪዎች የሚከፈሉት ወደቡ ለሚሰጠው አገልግሎት ሲሆን፣ እነዚህም ክፍያዎች ከአንዱ ወደብ ወደሌላ ወደብ ይለያያሉ። ከዚህ አኳያ የጂቡቲ ወደብ በውድነቱ ይታወቃል። ለንጽጽር ያህል የጂቡቲና የአካባቢው ወደቦች የታሪፍ መረጃ ከዚህ በታች በሠንጠረዥ 2.8፣ 2.9 እና 2.10 ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 2.8- ለገቢ ዕቃዎች የስቴቬዶሪንግ /የማራገፍ/ አገልግሎት ክፍያ ሲነጻጸር

| የኮንቴይነር ዓይነት | በየወደቡ የሚከፈል የስቴቬዶሪንግ ወጪ በአሜሪካን ዶላር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሞምባሣ | ዳሬሰላም | ፖርት ሱዳን | አማካይ | ጅቡቲ | ጅቡቲ ከአማካይ ጋር ሲነጻጸር በ% |
| ባለ 20 ጫማ | 99 | 80 | 110 | 96 | 133 | +39% |
| ባለ 40 ጫማ | 125 | 120 | 220 | 155 | 166 | +7% |

ምንጭ፡- ማገባ የትንታኔ ሰነዶች

ሠንጠረዥ 2.9 - ለገቢ ዕቃዎች የሾር ሀንድሊንግ አገልግሎት ክፍያ ንጽጽር

| የኮንቴይነር ዓይነት | በየወደቡ የሚከፈል የሾር ሀንድሊንግ ወጪ በአሜሪካን ዶላር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሞምባሣ | ዳሬሰላም | ፖርት ሱዳን | አማካይ | ጅቡቲ | ጅቡቲ ከአማካይ ጋር ሲነጻጸር በ% |
| ባለ 20 ጫማ | 85 | 70 | 40 | 65 | 272 | +318% |
| ባለ 40 ጫማ | 85 | 95 | 80 | 87 | 544 | +525% |

ምንጭ፡- ማገባ የትንታኔ ሰነዶች

ሠንጠረዥ 2.10- ለወጪ ዕቃዎች የስቴቬዶሪንግ /የማራገፍ እና ሾር ሀንድሊንግ / አገልግሎት ክፍያ ንጽጽር

| የኮንቴይነር ዓይነት | በየወደቡ የሚከፈል የስቴቬዶሪንግ እና ሾር ሀንድሊንግ ወጪ በአሜሪካን ዶላር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሞምባሣ | ዳሬሰላም | ፖርት ሱዳን | አማካይ | ጅቡቲ | ጅቡቲ ከአማካይ ጋር ሲነጻጸር በ% |
| ባለ 20 ጫማ | 184 | 230 | 110 | 175 | 249 | +42% |
| ባለ 40 ጫማ | 273 | 330 | 220 | 274 | 398 | +45% |

ምንጭ፡- ማገባ የትንታኔ ሰነዶች

## የየብስ ማጓጓዣ ወጪ

የየብስ ማጓጓዣ ወጪ ከጂቡቲ ወደብ አንስቶ በዩኒሞዳል አስመጪው እስከጠየቀበት መድረሻ፣ በመልቲሞዳል ደግሞ እስከ ደረቅ ወደብ ድረስ በየብስ የጭነት ማመላለሻ ጭነት ለማጓጓዝ የሚከፈል ክፍያ ሲሆን በሠንጠረዥ 2.11 ከሌሎች የአካባቢው አገሮች ጋር ተነጻጽሮ የቀረበው

አንድ 30 ቶን የያዘ ባለ 40 ጫማ ኮንቴነር እስከ አዲስ አበባ የሚጓጓዝበትን የዩኒሞዳል አማካይ ዋጋ ነው፡፡

ሠንጠረዥ 2.11- የየብስ ማጓጓዣ ወጪ (በአሜሪካን ዶላር) ማነጻጸሪያ

| የጭነቱ መነሻ | የጭነቱ መድረሻ | ርቀት በኪሎ ሜትር | ዋጋ በ20 ጫማ ኮንቴነር | ለ1 ኪ.ሜትር የሚከፈል | ለ1 ቶን የሚከፈል | 1ቶን 1ኪ.ሜ. ማጓጓዣ ወጪ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሞምባሳ | ናይሮቢ | 483 | 1045 | 2.16 | 34.83 | 0.072 |
| | ካምፓላ | 1137 | 3700 | 3.25 | 123.33 | 0.108 |
| | ኪጋሊ | 1439 | 4800 | 3.34 | 160.00 | 0.111 |
| ዳርሳላም | ካምፓላ | 1571 | 4600 | 2.93 | 153.33 | 0.098 |
| | ኪጋሊ | 1475 | 4300 | 2.92 | 143.33 | 0.097 |
| ጂቡቲ | አዲስ አበባ | 925 | 2050 | 2.22 | 68.33 | 0.074 |

የመረጃ ምንጭ፡- እ.ኤ.አ የ2014 የምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች የሎጅስቲክስ አፈጻጸም ሪፖርት

### *1.4.2.2. የወጪ ዕቃዎች (EXPORT)*

ጠቅላላ የወጪ ዕቃዎች የሎጂስቲክስ ወጪ ለማስላት ወካይ እቃዎች በመውሰድ የሚከተለው ትንታኔ ቀርቧል፡፡

ለዚህ ትንታኔ አንድ ባለ 40 ጫማ ጨርቃጨርቅ የያዘ ኮንቴነር ከጂቡቲ ወደብ ወደ ኢስታንቡል (ቱርክ) ወደብ እንደሚጓጓዝና እንዲሁም አንድ ባለ 20 ጫማ ቡና የያዘ ኮንቴነር ወደ ሀምበርግ(ጀርመን) ወደብ እንደሚጓጓዝ ታሳቢ ተደርጓል፡፡ ትንታኔውም በሠንጠረዥ 2.12 እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሠንጠረዥ 2.12 የወጪ እቃ የሎጂስቲክስ የዩኒሞዳል ወጪ

| የወጪ ዝርዝር | የባለ 20ጫማ ኮንቴነር ወጪ (USD) | ከጠቅላላወጪ ድረሻ በመቶኛ | የባለ 40ጫማ ኮንቴነር ወጪ (USD) | ከጠቅላላወጪ ድረሻ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| የየብስ ማጓጓዣ ወጪ ከአዲስ አበባ ጂቡቲ | 510 | 26 | 1020 | 32 |
| የጂቡቲ ወደብ ወጪ | 450 | 23 | 660 | 21 |
| የባህር ማጓጓዣ ወጪ | 950 | 49 | 1400 | 44 |
| ኮሚሽንና ሌሎች ወጪዎች | 40 | 2 | 80 | 3 |
| ጠቅላላ ድምር | 1950 | 100 | 3160 | 100 |

የመረጃ ምንጭ:- ከሎጅስቲክስ የችግርች ትንተና ሰነድ የተወሰደ /ማ.ጉ.ባ/

የኤክስፖርት ሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ በተለይም የኤክስፖርት ምርቶችና ለማኑፋክቸሪንግ ግብዓት የሚገባው ጭነትን አጣመሮ ሲታይ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ወጪም ሆነ ጊዜ ከተወዳዳሪ ሀገሮች ጋር ሲነጻጸር በክንውን ከዛ በላይ ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህም ምክንያት በዋናነት ሶስት ጉዳዮች ናቸው። እነርሱም:-

- የጭነት መጠን (Economy of scale) ይህም የኤክስፖርት ጭነት መጠን ጥቂት እና የተበታተነ መሆኑ፤
- ርቀትና
- የሎጅስቲክስ አሠራራችን ድክመት ናቸው።

ይህ አሁን ያለው የኤክስፖርት መጠንና ዓይነትን መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ የቁም እንስሳት፣ የሚበላሹ ዕቃዎች (Perishable Goods) በተመለከተ የሎጅስቲክስ መሠረት ልማትና አሠራር በአጅጉ ዝቅተኛ ወይም የለም በሚባል ደረጃ ላይ ነው። ቢኖርም የሚወስደው ጊዜና ወጪው እንደሀገር ተወዳዳሪ ለመሆን አያስችልም። ከዚህ በተጨማሪ የአክስፖርት ምርትን በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጐ በመላክ ረገድ አሁን የተደረሰበት

የአፈጻጸም ደረጃ 33% ሲሆን፣ ይህም ሀገሪቱን ለውጭ ምንዛሪ ወጪ የሚዳርግና አሠራሩም የተቀላጠፈ እንዳይሆን አድርጐታል፡፡

## 2.3. የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ ግምገማና የችግሮች ትንታኔ ግኝቶች

ቀደምሲል በተመለከተው ክፍል የሀገራችን የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም ደረጃ በዋናነት የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪን ማዕከል በማድረግ የመረጃ ትንታኔ ተደርጓል፡፡ ይህ ከሎጅስቲክስ ዘርፍ የችግሮች ትንታኔ (Diagnosis Report) ዝርዝር የጥናት ሰነድ ውስጥ አመላካች እንዲሆን የተወሰደ መረጃ ነው፡፡ የችግሮች ትንታኔ በተካሄደበት የጥናቱ ምዕራፍ ውስጥ ለእያንዳንዱ የሥራ ሂደት የሚወስደው ጊዜ፣ የሚደረግ ወጪ፣ ከዓለምአቀፍና በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች ጋር በማነጻጸር ተተንትኗል፡፡ በእያንዳንዱ የሥራ ሂደትም ችግሮቹ እና የችግሮቹ መገለጫዎች፣ መንስኤዎችና ያስከተሉት ጉዳት ተተንትኗል፡፡ በአጠቃላይ የሀገራችን የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ ከዓለምአቀፍ ስታንዳርድ ጋር ሲነጻጸር በእጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መረጃው አመልክቷል፡፡ በምሥራቅ አፍሪካ ከሚገኙ ሀገሮች የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም አማካይ ውጤት ጋር ሲነጻጸርም የሀገራችን በአብዛኛዎቹ መለኪያዎች ከእጥፍ በላይ ይበልጣል፡፡

ለዚህ ዝቅተኛ የሎጅስቲክስ አፈጻጸም በምክንያት የሚጠቀሱ በርካታ ችግሮች ለመለየት ተችሏል፡፡ ከዚህ የችግሮች ትንታኔ በመነሳት የዘርፉን ራዕይና ዓላማ ከማሳካት አንጻርና የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ተወዳዳሪነትን ከማሻሻል አኳያ መሠረታዊ የሆኑና ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ብሎም ልዩ ትኩረት የሚሹ ቁልፍ ችግሮች የሚከተሉት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

### 2.3.1. የንግድና የፋይናንስ ሥርዓት

በትራንዚት ጊዜና ወጪ ትንታኔ ላይ እንደተመለከተው የገቢ ዕቃዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ሂደት ከባንክ ፈቃድ ማግኘት ጀምሮ ዕቃውን እስከ መረከብ ድረስ ከሚወስደው አጠቃላይ ጊዜና ወጪ ውስጥ የፋይናንስና የንግድ ሥርዓቱ ድርሻ 65% ያህል ነው፡፡ ከዕቃዎቹ የወደብ ላይ ቆይታ አንጻር ሲታይም የሀገራችን ከዓለም አቀፍ ስታንደርድ /አማካይ 3 ቀናት/ ከ10 እጥፍ በላይ ነው፡፡ ለዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ መራዘም በርካታ ምክንያቶችና ችግሮች ቢኖሩም ዋናውን ቁልፍ ችግር ግን የንግድና የፋይናንስ ሥርዓቱ ነው፡፡

ለምሣሌ የብትን ጭነት አገባብ ስርዓታችን መርከብን እንደ መጋዘን የመጠቀም ያህል ነው፡፡ ለዚህም ከዋና ዋና መንስዔዎች ውስጥ የጭነት አስመጪዎቹ የተበታተኑ እና አሠራራቸውም የተበጣጠሰ በመሆኑ በጋራ የማቀድ ችግር እና የገንዘብ አቅርቦቱ በተለይም የውጭ ምንዛሪ ችግር ነው፡፡ የዕቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ በተመለከተም ቢሆን ለዕቃዎች በባህር ወደብም ሆነ በደረቅ ወደብ ቆይታ ኮንቴይነርን እንደ መጋዘን የመጠቀም አሠራር በዋናነት ከትራንስፖርት ሎጅስቲክሱ በላይ የንግድ አሠራሩና የፋይናንስ ዘርፍ ንግድን በማሳለጥ ረገድ ያለው ክፍተት ነው፡፡ ለምሣሌ ሞጆ ደረቅ ወደብ ላይ ያሉት በየጊዜው ለረጅም ጊዜ የሚከማቹ ኮንቴይነሮች ጥሩ መገለጫ ናቸው፡፡

የንግድና የፋይናንስ ሥርዓቱ በሎጅስቲክስ አፈጻጸም ላይ ያለው አሉታዊ ተጽዕኖ ከላይ ከተጠቀሱት ባለፈ የገቢ ንግድ የሚመራበት አሠራር የተንዛዛና በርካታ አላስፈላጊ እጆች የበዙበት ነው፡፡ ስለሆነም ውጤታማና ፈጣን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ከመዘርጋት አኳያ የንግድና የፋይናንስ ሥርዓቱ ያለው ድርሻ ከፍተኛና አንዱ ቁልፍ ችግር መሆኑ ታይቷል፡፡

### 2.3.2. ያልተቀላጠፈ ያልተቀናጀ የትራንዚትና የጉምሩክ አሠራር

የገቢና የወጪ ዕቃዎች ከመነሻ ጀምሮ እስከ መድረሻ ባለው ሂደት ውስጥ በርካታ ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪ አካላት አሉ፡፡ እነዚህም፣ የዕቃ አቅራቢዎች፣ የባህር አጓጓዦች፣ ወደቦች፣ የኢትዮጵያና የባለወደብ ሀገሮች የጉምሩክ መ/ቤቶች፣ ትራንስፖርተሮች፣ የድንበር እና መሰል በርካታ ተቆጣጣሪ ተቋማት ናቸው፡፡ በእነዚህ አካላት የሚጠየቁ በርካታ የሰነዶች፣ የመረጃና የክፍያ ብዛት፣ የሥራ ሂደቱ የሚወስደው ጊዜ የተንዛዛ መሆን፣ ሥራው በሚጠይቀው ልክ በፋሲሊቲ፣ በመሣሪያና በሰው ኃይል የተሟላ ሆኖ አለመገኘት፣ በዋናነት ደግሞ በእነዚህ የሎጅስቲክስ ዘርፍ ተዋናዮች መካከል የተቀናጀ አሠራር አለመኖር አንዱና ከፍተኛ ማነቆ መሆኑ ታይቷል፡፡

እቃውን ከባህር ወደብ ለማውጣት የሚፈጸሙ ስነስርዓቶች፤በመንገድ ለማጓጓዝ፤እና በሀገር ውስጥ የጉምሩክ ስነስርዓት ፈጽሞ እቃውን ለማውጣት የሚወስደው ጊዜ በወረቀት ሲታይ እጅግ አነስተኛ ቢመስልም በተግባር ግን ውስብስብ የሆኑ ሂደቶችን የሚያልፍ በመሆኑ ከጉምሩክ አሰራር ጋር በተያያዘ በሚፈጠሩ የሲስተም እና ሌሎች ጉዳዮች የተነሳ የእቃዎች የትራንዚት ሂደት ረጅም ሆኖ ተገኝቷል፡፡

### 2.3.3. የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ብቃትና አቅም ዝቅተኛ መሆን

የሎጅስቲክስ ዘርፉን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ የመንግስት ልዩ ልዩ ተቋማት በዕውቀትና በብቃት ከመምራት አኳያ የተቋማት የማስፈጸም አቅም ማነስ አንዱ ማነቆ ሲሆን፣ እንዲሁም በመንግስትም ሆነ በግል ዘርፍ፣ በሀገር ውስጥም ሆነ በባህር ወደቦች የሎጅስቲክስ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች የዘርፉ ዕውቀትና ክህሎት ያለዉ የባለሙያ ክፍተት ሌላው ማነቆ መሆኑ ታይቷል፡፡

ከዚህ አኳያ የጉምሩክ አስተላላፊዎች፣ የእቃ አስተላላፊዎች፣ የመርከብ ወኪሎች፣ የጅቡቲ ትራንዚተሮች እና የጅቡቲ መርከብ ወኪሎች ተናቦ የመስራት፣ የስልጠና እና የብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥ ስርዓት ሀገራችን ከምትፈልገው የንግድ ሎጅስቲክስ አሰራር እና ፍላጎት አንጻር ያልተቀናጀ እና ያልተጣጣመ በመሆኑ በተለያዩ ተቆጣጣሪ አካላት በተበጣጠሰ መልኩ የሚሰጡ ብቃት የማረጋገጥ እና ኦፕሬተሮችን የማብቃት ስራ ተፈላጊውን ውጤት እያመጣ እንዳልሆነ ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በተለይ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች የሚሰጠው ስልጠና ወቅቱን በጠበቀ ሁኔታ በቋሚነት የማይሰጥ ከመሆኑ አንጻር ጥቂት የጉምሩክ አስተላላፊዎች በከፍተኛ ዋጋ ለመስራት የሚችሉበት እድልን በመፍጠር የባለሙያ እጥረት የሚያስከትል መሆኑ ታይቷል፡፡ በዋናነት የሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለውን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሳይበጣጠስ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት በመስጠት ረገድ ዘርፉ ከሚጠይቀው ብቃት፣ የፋሲሊቲና የማስተናገድ ዓቅም አንጻር ክፍተቱ ጉልህ መሆኑ ታይቷል፡፡

### 2.3.4. በሎጅስቲክስ የአገልግሎት ዘርፍ የሞኖፖሊ አሠራር ችግር

በሎጅስቲክስ የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ በሞኖፖሊና በብቸኛ የአገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (Exclusive Service Providers) የሚከናወኑ የአገልገሎት መስኮች ብዙ ናቸው፡፡ እነርሱም በጅቡቲ ወደብ የ”SGTD” የኮንቴይነር ተርሚናል፣ የብትን ጭነት ተርሚናል (SDTV)፣ የነዳጅ ተርሚናል (Horizon)፣ እንደዚሁም ለገቢ ዕቃዎች የባህር ትራንስፖርት፣ (ሁሉንም የገቢ ጭነት አይመለከትም) የመልቲ ሞዳል ኦፐሬሽንና የደረቅ ወደብ አገልግሎት ናቸው፡፡

እነዚህ የአገልግሎት መስኮች ለገበያ ክፍት አለመሆናቸው ብቻ ሳይሆን የአገልግሎት አሰጣጡን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራር ባለመዘርጋቱም ጭምር ለተንዛዛ አሠራርና ለአገልግሎት ዋጋ መናር መነሻ ምክንያት ነው፡፡

ስለሆነም የሎጅስቲክስ የአገልግሎት መስኮች ላይ ተገቢ ቁጥጥርና በዘርፉም የውድድር መንፈስ ዝቅተኛ መሆን በሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ላይ የማይናቅና ጉልህ ችግር መሆኑ ታይቷል፡፡

## 2.3.5. በቂ የሎጅስቲክስ መሠረተ ልማት አለመኖርና የማኔጅመንት ችግር

ውጤታማ እና የተቀላጠፈ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ከሚፈለገው ግብዓት አንዱ የመሠረተ - ልማት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከትንታኔው ከታዩ በርካታ ግኝቶች ውስጥ፤

- የትራንስፖርት አቅርቦትና የትራንስፖርት ማኔጅመንት ችግር፤
- የመንገድ ሁኔታ፤
- የጭነት ማዕከላት ሁኔታ፤
- የወደብ ፋሲሊቲ፤ የመርከብ ማሸጊያዎች፤ የወደብ ዕቃ መገልገያ መሣሪያዎችና
- የዘመናዊ የመረጃ ቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በመሰል የሎጅስቲክስ የመሠረተ-ልማት ግንባታ ላይ ክፍተት ታይቷል፡፡

## 2.3.6. በሎጅስቲክስ ዘርፍ በአገልግሎት ሰጪዎችም ሆነ በተቆጣጣሪ ተቋማት ያለው የአደራጀጀት፤ የአቅም፤ የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት

የሎጅስቲክስ ዘርፉን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ የመንግስት ልዩ ልዩ ተቋማት በዕውቀትና በብቃት ከመምራት አኳያ የተቋማት የአደረጃጀት እና አጠቃላይ የማስፈጸም አቅም ማነስ አንዱ ማነቆ ነው፡፡ እንዲሁም አንዱ ተቋም ከሌላው ጋር ተቀናጅቶ እና ተናቦ የሚሰራበት ህጋዊ የሆነ የጎንዮሽ የጋራ አሰራር “Horizontal coordination” የለም፡፡ በመንግስትም ሆነ በግል ዘርፍ፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በባህር ወደቦች የሎጅስቲክስ አገልግሎት የሚሰጡ ኩባንያዎች የዘርፉ ዕውቀትና ክህሎት ያለዉ የባለሙያ ክፍተት ሌላው ማነቆ መሆኑ ታይቷል፡፡

# ክፍል ሶስት:

## የሎጅስቲክስ ዘርፍ ራዕይ፣ የስትራቴጂው ዓላማና ግቦች

**ራዕይ**

በ2020 ዓ.ም መጨረሻ የሎጅስቲክስ ሥርዓታችን የሀገራችንን የንግድና የኢንቨስትመንት ዕድገት በማሳለጥ ከአፍሪካ ቀዳሚ ሆኖ ማየት::

## 3.1 ዓላማና ግቦች

### 3.1.1 አጠቃላይ ዓላማ

የሎጅስቲክስ ሥርዓቱን በቀጣይ አሥር ዓመታት ውስጥ ትራንስፎርም ማድረግ ነው::

### 3.1.2 ዝርዝር ዓላማዎች

- የሀገሪቱን የንግድና የፋይናንስ አሰራር በማሻሻል የሎጅስቲክስ አገልግሎትን ማሳደግ
- የተቀናጀና የተናበበ የትራንዚት እና የጉምሩክ አሰራር መዘርጋት
- የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን ብቃት ማሳደግ
- በሎጅስቲክስ ዘርፍ ያለውን የሞኖፖሊ አሰራር ማሻሻል
- የሎጅስቲክስ መሰረተ - ልማትን ማሳደግ
- የሎጅስቲክስ ዘርፍ የማስፈጸም አቅም መገንባት

### 3.1.3 የስትራቴጂው ግቦች

የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጅ ግቦች የሎጅስቲክስ አፈጻጸም መለኪያን፣ በአፈጻጸም መለኪያ መሠረት አሁን ያለበት ደረጃ እንዲሁም በቀጣይ

አሥር ዓመታት ውስጥ የሚደርስበትን ደረጃ በማካተት የተቀረጸ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ግብ 1. ጭነትን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የባንክ ፈቃድ ከመጠየቅ ጀምሮ ዕቃው በአገር ውስጥ እስከ መረከብ የሚወስደውን ጊዜ (lead time) ከ123 ቀናት ወደ 40 ቀናት መቀነስ፣

ግብ 2. ገቢ ዕቃዎች (import cargo) ከመርከብ ከተራገፈበት ቀን ጀምሮ በአገር ውስጥ ለመረከብ የሚወስደውን ጊዜ ከ46 ቀናት ወደ 7 ቀናት መቀነስ፣

ግብ 3. ወጪ ዕቃዎች (export cargo) ከአገር ውስጥ ከባንክ ፈቃድ ጀምሮ ጭነቱ መርከብ ላይ እስኪጫን የሚወስደውን ጊዜ ከ36 ቀናት ወደ 7 ቀናት መቀነስ፣

ግብ 4. ወደ አገር ውስጥ የሚጓጓዘውን የብትን ጭነት ያለምንም የመርከብ ዲመሬጅ ክፍያ ወደ አገር ውስጥ ማጓጓዝ፣

ግብ 5. የገቢ ዕቃዎችን የወደብ ላይ ቆይታ (port Dwell time) ከ40 ቀናት ወደ 3 ቀናት መቀነስ፣

ግብ 6. ወጪ ዕቃዎችን በአገር ውስጥ በኮንቴነር አሽጐ የመላክ አፈፃፀምን ከደረሠበት 33% ወደ 90% ማሳደግ፣

ግብ 7. የብትን ጭነት አጓጓዥ መርከቦች በወደብ የባህር ላይ ቆይታን ከ35 ቀናት ወደ 2 ቀናት መቀንስ፣

ግብ 8. የብሬክ በልክ አጓጓዥ መርከቦች በወደብ የባህር ላይ ቆይታን ከ15 ቀናት ወደ 2 ቀናት መቀነስ፣

ግብ 9. የጭነት መኪኖች አመታዊ የጉዞ ሽፋን "Truck Milage" ኪ.ሜ ከ70ሺ.ህ ወደ 120 ሺ.ህ ማሳደግ፤

## 3.2 የሎጅስቲክስ ዘርፍ ስትራቴጂዎች

የሀገራችን የሎጅስቲክስ ዘርፍ ራዕይና ዓላማውን ከማሳካት አኳያ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያላቸው ቁልፍ የሆኑ ማነቆዎች (challenges) በትንታኔ ላይ በተመሰረተ ጥናት ተለይተዋል፡፡ ስለሆነም የሎጅስቲክስ ሥርዓትን ትራንስፎርም የማድረግ ዓላማን ለማሳካትና ቁልፍ ማነቆዎችን ለመፍታት የሚያስችሉ ስድስት ዋና ዋና ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ስትራቴጂ - 1 | የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ አሠራርና የኦፐሬተሮች ብቃት ትራንስፎርም ማድረግ፣ |
| ስትራቴጂ - 2 | የሎጅስቲክስ ዘርፍ ፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማጠናከር፣ |
| ስትራቴጂ - 3 | የተሳለጠና አስተማማኝ የጉምሩክና የትራንዚት ሥርዓት መዘርጋት፣ |
| ስትራቴጂ - 4 | አስተማማኝ የንግድና የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት፤ ሎጅስቲክስ የማሰለጥ ሚናውን ማጉልበት፣ |
| ስትራቴጂ - 5 | የሎጅስቲክስ መሠረተ - ልማት መገንባት፣ |
| ስትራቴጂ - 6 | የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተቋማዊ አቅም፣ የዘርፉ የሰው ኃይል ብቃት መገንባት እና ውጤታማ አደረጃጀት መፍጠር፣ |

ለእያንዳንዱ ዋና ስትራቴጂ ንዑሳን ስትራቴጂዎችና የማስፈጸሚያ ስልቶች (Interventions) በማካተት እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ ንዑስ ስትራቴጂዎች የዋና ስትራቴጂዎች አካል ሲሆኑ የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Interventions) ደግሞ ስትራቴጂውን ወደተግባር ለመለወጥ የሚያስችሉ እርምጃዎች ናቸው፡፡ በመሆኑም የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Interventions) በቀጣይ ወደ ኘሮግራም የመለወጥ ሥራ የሚጠይቅ ነው፡፡

## ስትራቴጂ 1 የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አሠራርና የኦኘሬተሮች ብቃት ትራንስፎርም ማድረግ፡፡

*የስትራቴጂው መግለጫ*

ይህ ስትራቴጂ የሀገራችንን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርም በማድረግ ሂደት ቁልፍ ጉዳይ የሆነው የሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥና አሠራር ውጤታማ በሆነ መልኩ በመለወጥ የተቀላጠፈ ውጤታማና የተቀናጀ እንዲሆን ማድረግ፤ እንደዚሁም የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ለላኪዎችና ለአስመጪዎች የተሟላና የተቀናጀ አገልግሎት ለመስጠት ወደ ሚያስችል የላቀ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው፡፡

ይህን ስትራቴጅ ለመተግበር የሚከተሉት ንዑሳን ስትራተጂዎች ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ንዑስ ስትራቴጂ 1.1 | ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 1.2 | የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጅስቲክስ አገልግሎት ድርጅት የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አሰራርና አደረጃጀትን ትራንስፎርም ማድረግ፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 1.3 | የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን ማጠናከር፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 1.4 | የትራንስፖርት አቅምን ማሳደግ (Enhance Transport Capacity) |

እያንዳንዱ ንዑሳን ስትራቴጂዎች ከማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 1.1 - ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሥርዓት መዘርጋት

የዚህ ንዑስ ስትራቴጂ የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Intervention) ከአጭር መግለጫ ጋር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 1. የደረቅ ብትን ጭነት በብሄራዊ ደረጃ ለማቀናጀት የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፡፡

በመንግስት እና በተለያዩ አካላት በእርዳታ እና በግዢ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባውን ደረቅ ብትን ጭነት ከግዢ ጀምሮ በማቀድ፤ የፋይናንስ አቅርቦት፤የባህር ትራንስፖርት፤ የወደብ አገልግሎት፤ የመንገድ/የባቡር ትራንስፖርት እና በሀገር ውስጥ የመጋዝን አቅርቦትን በተቀናጀ መልኩ ለመምራት የሚያስችል አደራጃጀትና እና የህግ ማዕቀፍ በማዘጋጀት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 2. የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ሎጅስቲክስ ስርዓት መዘርጋት

የቁም እንስሳት ኤክስፖርት ለማሳደግ በሀገር ውስጥ ዋና ዋና ቀጠናዎች የእንስሳት ማቆያ ማዕከላት ከበቂ ፋሲሊቲ ጋር መገንባት፤ እንስሳትን

ከሀገር ውስጥ ማቆያ ስፍራ ወደ ባህር ወደብ ለማጓጓዝ የሚያስችሉ የእንስሳት ማጓጓዣ ማሟላት፣ የድጋፍ እና ማበረታቻ ስርዓት መዘርጋት፤ የእንስሳት ኤክስፖርት ሎጅስቲክስ አገልግሎት ሲጪ ኩባንያዎች እንዲፈጠሩ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤ በባህር ወደብ አካባቢ የተሟላ የቁም እንስሳት ማቆያ ስፍራ መገንባት እና በአጠቃላይ የቁም እንስሳት ኤክስፖርቱ ተወዳዳሪ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 3. የመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ይበልጥ ማጠናከርና ሽፋኑን ማሳደግ

አሁን ባለው አሰራር በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት የሚጓጓዘው ጭነት መጠን ዝቅተኛ ነው፡፡ ይህንን ሽፋን ለማሳደግ የሚያስችል የኦፕሬተር አቅም የማጎልበት እና አሁን በመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት ያልተሸፈኑ ጭነቶች በዚህ ስርዓት የሚካተቱበት ጥናት በማካሄድ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 4. የወጪ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሸጎ የመላክ አሠራር መዘርጋት

በዓለም አቀፍ ደረጃ እቃን በኮንቴይነር አሽጎ የመላክ አሰራር እያደገ እና ዘመናዊ እየሆነ የመጣ ሲሆን የሀገራችን ጭነት ግን 67% የሚሆነው በጆንያ ተቋጥሮ ጅቡቲ ወደብ ከደረሰ በኋላ በኮንቴይነር ታሽጎ ኤክስፖርት የሚደረግ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ኋላቀር አሰራር ለመለውጥ የሚያስችል ጥናት በማካሄድ የህግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤ ኤክስፖርት እቃን በኮንቴይነር አሽጎ ለመላክ የሚያስችሉ መሰረተ-ልማቶች እና ፋሲሊቲዎች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

## 5. የኢኮኖሚ አዋጭነትን መሠረት ያደረገ ተጨማሪ ወደቦች/የትራንዚት ኮሪደሮች አጠቃቀም ማሳደግ፡፡

የሀገራችን ገቢና ወጪ እቃ ሙሉ ለሙሉ ሊባል በሚችል ደረጃ በተወሰኑ ኮሪደሮች የሚተላለፍ ሲሆን ይህም የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጡን ውስብስብ በማድረግ የትራንዚት ወጪና ጊዜ እንዲጨምር አድርጓል፡፡ በመሆኑም አሁን ያሉ ኮሪደሮችን አጠቃቀም በማሳደግ፤ ተጨማሪ ኮሪደሮችን በመክፈት የተሳለጠ የኮሪደር አጠቃቀም ስርዓት በጋራ ይዘረጋል፡፡

## 6. የተሟላና የተቀናጀ የኤክስፖርት የሎጅስቲክስ አገልግሎት ፓኬጅ አሠራር መዘርጋት፡

የሀገራችንን ኤክስፖርት በጊዜ እና በዋጋ ተወዳዳሪ በማድረግ የኤክስፖርት መጠንን ለማሳደግ እና የንግድ ሚዛንን ለማመጣጠን በኤክስፖርት ላይ የሚታዩ የሎጅስቲክስ አሰራሮችን በመፈተሽ በኤክስፖርት የተሰማሩ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን አሰራር በማሻሻል እና የማበረታቻ ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት ኤክስፖርት ሎጅስቲክስ በፓኬጅ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡

## 7. የባህር ትራንስፖርት አገልግሎትና ዋጋ የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት

የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ዋጋ አሁን ባለው አሰራር በዓለም አቀፍ ገበያ የሚመራ ነው፡፡ የዓለም አቀፍ አሰራር ይህ ሆኖ ሳለ ግን የሀገራችን ደግሞ በሞኖፖሊ የሚሰራ እና በገበያ የማይመራ ነው፡፡ ስለሆነም ዋጋውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ያደረገ አሰራር በጥናት ተመስርቶ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 8. የገቢ ዕቃዎች የትራንዚት ትራንስፖርት የሚመራበት ሥርዓት መዘርጋት

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ እቃዎች የትራንዚት እና የትራንስፖርት ሎጅስቲክስ ሂደትን በተመለከተ ስታንዳርድ በማዘጋጀት ሁሉም አገልግሎት ሰጪዎች ወጥ በሆነ አሰራር አገልግሎት ለመስጠት እንዲችሉ የሚያደረግ የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 9. የኢንዱስትሪያል ፓርኮችን እና የጭነት መነሻና መድረሻ ጣቢያዎችን ማዕከል ያደረገ የተቀናጀ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የትራንዚት ትራንስፖርት አሠራር መዘርጋት

የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ከመደበኛው የተለየ እና ከመነሻ እስከ መድረሻ ወጥ የሆነ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አሰራር በማጥናት የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 10. የሎጅስቲክስ የጭነት ማዕከሎች የጋራ አጠቃቀም አሠራር መዘርጋት

በሀገር ውስጥ በመንግስት የተገነቡ እና ወደፊት የሚገነቡ የጭነት ማዕከላት ውስጥ ሁሉም የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች በጋራ ለመጠቀም የሚያስችላቸው አሰራር በመዘርጋት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 11. በደረቅ ወደቦች የዕቃዎች የቆይታና የውርስ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት

በሀገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች የሚስተናገዱ ጭነቶችን በወደቡ ውስጥ ለማቆየት፤ ለማስተላለፍ እና ባለቤት ሳይቀርብ ሲቀር ደግሞ የሚወገዱበትና የሚወረሱበት በአጠቃላይ በዚህ ሂደት ያሉትን ማነቆዎች በማጥናት የአሰራር ስርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 12. የባህር የየብስና የአየር ትራንስፖርት በማጣመር አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የከንሶሊዴሽን አሠራር መዘርጋት

የወጪና ገቢ እቃዎችን በተለይም የኤክስፖርት ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ እቃዎችን የየብስ እና የአየር ትራንስፖርት በማጣመር ለመጠቀም የሚያስችሉ የኮንሶሊዴሽን ማዕከላትን ምርቱ በሚገኝባቸው አካባቢዎች መገንባት እና የአጠቃቀም የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## ንዑስ ስትራተጂ 1.2 የኢባትሎአድን የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ፣ አሰራርና አደረጃጀትን ትራንስፎርም ማድረግ፣

ይህ ንዑስ ስትራቴጂ በዋናነት የሚያተኩረው ኢባትሎአድ ላይ ሲሆን ድርጅቱም በሀገራችን ሎጅስቲክስ ሥርዓት ከፍተኛ ሚና ያለው የመንግስት ልማት ተቋም ነው፡፡ ተቋሙ ከሉጅስቲክስ አንጻር በማንኛውም የሀገራችን የልማት እንቅስቃሴ ጀርባ ሊገኝ ይገባል፡፡ ስለሆነም ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጂ ከመተግበር አኳያ የኢባትሎአድ በዋናነት ሁለት ሚናዎች ይኖሩታል፡፡ እነርሱም፡-

1ኛ/ ስትራቴጂውን በተግባር ለመተርጎም ግንባር ቀደም የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ተቋም ሆኖ መገኘት፡፡

2ኛ/ በሎጅስቲክስ የአገልግሎት መስክ ከተሰማሩት ተቋማት ጋር በአጋርነት በመስራት የሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን የማብቃትና ዘርፉም ለውድድር ምቹ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽዎ የሚያደርግ ብቁ ተቋም ሆኖ መገኘት ይጠበቅበታል፡፡

በመሆኑም የዚህ ንዑስ ስትራቴጂ ማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Intervention) እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 13. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት የሚጓጓዝ የጭነት ሽፋን እና የአገልግሎት አሰጣጥ ለማሳደግ ሌሎች የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ አካላትን ለመጠቀም የሚያስችል አሠራር መዘርጋት፡፡

የኢባትሎአድ አሁን ባለው አሰራር ሁሉንም አገልግሎቶች በራሱ አቅም የሚሰጥ ሲሆን የትራንስፖርት አገልግሎትን ግን ሌሎች የትራንስፖርት ድርጅቶች ጋር ውል በማግባት "Out source" በማድረግ እያሰራ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ከዚህ በላይ አቅሙን የበለጠ ለማሳደግ እና በመልቲሞዳል ያልተሸፈኑ ጭነቶችን ወደዚህ ስርዓት ለማስገባት እንዲቻል የግል የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን በኮንትራት ውል የሚያሰራበት ስርዓት በመቅረጽ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 14. የኢትዮጵያ ጭነት በሚስተናገድባቸው ወደቦች ቀድሞ በመገኘት ሎጅስቲክስ የማሳለጥ ሀገራዊ ተልዕኮ በብቃት መፈጸም፤

የሀገራችን ገቢና ወጪ እቃዎች በሚስተናገዱባቸው ወደቦች እና ኮሪደሮች የተሟላ የአገልግሎት መስጫ ጽ/ቤት በመክፈት ኦፕሬሽኑ የሀገራችንን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ እንዲሆን ሞዴል ሆኖ እንዲሰራ እና ሌሎች አገልግሎት ሰጪዎች ይህንኑ እንዲከተሉ በኦፕሬሽን ብቃት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

## 15. በመልቲ ሞዳል ትራንስፖርት ሥርዓት ለሚጓጓዙ ጭነቶች ፈጣን አገልግሎት መስጠት

የመልቲሞዳል ትራንስፖርት ስርዓት በሀገራችን አስመጪና ላኪዎች ዘንድ ይበልጥ ተመራጭ እንዲሆን እና በጊዜ እና በወጪ ተወዳዳሪ ለማድረግ ጭነትን ከመርከብ በተራገፈ በአጭር ቀናት ውስጥ ደረቅ ወደብ ለማድረስ የሚያስችል ስታንዳርድ ኦፐሬሽን ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

## 16. በዩኒ ሞዳል የትራንስፖርት ሥርዓት ለሚጓጓዝ ጭነት ፈጣን አገልግሎት መስጠት

በዩኒሞዳል የትራንስፖርት ሥርዓት ለሚጓጓዝ ጭነት የተሟላ የክሊሪንግ ሰነድ ከመረከብ ጀምሮ ጭነቱን በአጭር ቀናት ውስጥ ለማስረከብ የሚያስችል ስታንዳርድ ኦፐሬሽን ይዘረጋል፡፡

## 17. የደረቅ ወደብ ኦፐሬሽን የአገልግሎት አሰጣጥ ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሆነ አሠራር መዘርጋት

አሁን ባለው አሰራር ደረቅ ወደቦች በርካታ የአሠራር ችግሮች ያሉባቸው እና የእቃዎች ደህንነት በበቂ ሁኔታ ለመጠበቅ የማይቻልባቸው ፤ ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ በደንበኞች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው ስርዓቶች ያልተዘረጉባቸው ናቸው፡፡ በደረቅ ወደቦች የዕቃዎች ቆይታም ሆነ የክሊራንስ ጊዜ ረዥም ነው፡፡ የዕቃዎች ክምችትም ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም ደረቅ ወደቦች ወጥ የሆነ ዘመናዊ የተሳለጠና ውጤታማ የደረቅ ወደብ አያያዝ እና አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 18. የሽፒንግ ስትራቴጂ መንደፍና መተግበር

በራስ መርከብ እና በሌሎች መርከቦች በመጠቀም የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት የመስጠት አሠራርን የብሄራዊ፣ አህጉራዊና የዓለም አቀፍ ሁኔታን ያገናዘበ የሽፒንግ ስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 19. ለፕሮጀክት ዕቃዎች ልዩ የካርጐ ሀንድሊንግና የትራንስፖርት አገልግሎት ለመሰጠት የሚያስችል አቅም መፍጠር

ሀገራችን በርካታ ፕሮጀክቶችን በመተግበር ላይ የምትገኝ በመሆኗ እና ለፕሮጀክቶች የሚገቡ እቃዎች ደግሞ ልዩ ባህሪ ያላቸው ከመሆኑ አንጻር የተለየ የሎጅስቲክስ አገልግሎት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ይህንን ለማስተናገድ የሚያስችል ፋሲሊቲ ይሟላል፤ የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ አቅም የማሳደግ ስራ ይከናወናል፡፡

### 20. ጭነት የማቀናጀት አሠራርና ማዕከል (Cross Docking Centers) ማቋቋም

በገቢና በወጪ ንግድ ያለው ክፍተትን ተከትሎ በተለይም በቀላሉ ለሚበላሹ ጭነቶች በኮንቴይነር አቅርቦት እየተከሰተ ያለውን ችግር ለመፍታት የሚያስችል ጭነት የማቀናጀት አሠራርና ማዕከል (Cross Docking Centers) ይቋቋማል፡፡

### 21. የኢባትሎአድ መዋቅራዊ አደረጃጀቱ የተሟላ ቁመና ያለው ተቋም ማድረግ

የኢባትሎአድን ቀደም ሲል በተካሄድ ጥናቶችና በአፈጻጸም የተለዩ ክፍተቶችን ለመሙላት፤ ከላይ የተዘረዘሩትን ስትራቴጂዎች ለመሸከምና በአጠቃላይም የሀገሪቱ የሎጅስቲክስ ሥርዓትን ትራንስፎርም ለማድረግ የተነደፉ ስትራቴጂዎችን በግንባር ቀደምትነት ተሰልፎ ለመፈጸም የሚያስችለው መዋቅራዊ አደረጃጀቱ የተሟላ ቁመና ያለው ተቋም ይሆናል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 1.3 የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችን ማጠናከር

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች ((Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 22. በዘርፉ ጠንካራ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ለመፍጠር የረጅም ጊዜ ኮንትራት አሰራር መዘርጋት

በሎጅስቲክስ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች የሀገራችንን ኢኮኖሚ ከመደገፍ አንጻር ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር እነዚህ አገልግሎቶች በተበጣጠሰ መልኩ በርካታ እጆች የሚገቡባቸው ከሆነ የወጪ መናር እና የትራንዚት ጊዜ መጨመርን ያስከተላሉ፡፡ ስለሆነም ከመነሻ እስከ መድረሻ አገልግሎቶቹን ሊሰጡ የሚችሉ ጠንካራ ኦፐሬተሮችን መፍጠር ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም ጠንካራ የቁጥጥር እና የድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት የአገልግሎት ሰጪዎችን ደረጃ የመመደብ ስራ የሚከናወን ይሆናል፡፡ እንዲሁም ኦፕሬተሮቹ በቂ ሀብት መድበው የሎጅስቲክስ ፋሲሊቲዎችን እንዲያሟሉ ለማድረግ የሚያስችል የረጅም ጊዜ የኮንትራት አሰራር ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 23. በትራንስፖርት አገልግሎት የተሰማሩ ኦፕሬተሮችን ወደ የተሟላ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪነት ማሸጋገር

በአንጻራዊነት የተሻለ አቅም ያላቸውን እና በትራንስፖርት አገልግሎት የተሰማሩ ኩባንያዎችን ወደ የተሟላ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪነት ለማሸጋገር የሚያስችል ኘሮግራም ተነድፎ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 24. በዘርፉ የተሰማሩ የእቃ አስተላላፊነትና የመርከብ ውክልና አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችን ማጠናከር

አሁን ያሉት የእቃ አስተላላፊዎች ከጥቂቶቹ በስተቀር በቂ ሙያ ኖሯቸው ተገቢውን ፋሲሊቲ በማሟላት ለደንበኞች እርካታን የሚፈጥር ስራ የሚያከናወኑ አይደሉም፡፡ አንዳንዶቹ ቅሬታ እና ክስ የሚበዛባቸው፤ ለአጋሮቻቸው ክፍያ በወቅቱ የማይፈጽሙ፤ የስነምግባር ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ዓለም አቀፍ ተሞክሮን መሰረት ያደረገ ስታንዳርድ በማዘጋጀት የማጥራት እና በዘርፉ ሊቀጥሉ የሚችሉትን በመለየት በቂ ድጋፍ በማድረግ የማጠናከር ስርዓት መዘርጋት ነው፡፡ የመርከብ ወኪሎች አሰራርም ቢሆን አንድ የመርከብ ወኪል ሊያከናውን በሚችለው ደረጃ የመወሰን አቅም ያላቸው አይደሉም፡፡ አንዳንዶቹ ወኪሎች በጅቡቲ ወደብ ለሚገኙ ወኪሎች ተቀጽላዎች እንጂ እራሳቸውን የቻሉ ባለመሆናቸው ሎጅስቲክሱን ከማሳለጥ አንጻር ያላቸው ሚና በዚያው ልክ ዝቅተኛ ነው፡፡ ስለሆነም በቀጥታ የመርከብ ኩባንያው ወኪል በመሆን ጠንካራ የመወሰን እና ለሀገራችን ሎጅስቲክስ በጎ ሚና የሚጫወቱ እንዲሆኑ የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

## 25. የጉምሩክ ልዩ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፈቃድ ሥርዓት ለሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች የሚሰጥበት አሠራር መዘርጋት፡፡

ልዩ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ፈቃድ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በኩል በማኑፋክቸሪንግ ፤ በግብርና ምርት እና በማዕድን ዘርፍ ለተሰማሩ አምራቾች፤ላኪዎች እና አስመጪዎች የሚሰጥ ነው፡፡ ስለሆነም የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችም በዋናነት አገልግሎት የሚሰጡት ከላይ ለተጠቀሱት አምራቾች፣ ላኪዎችና እና አስመጪዎች በመሆኑ ለእነሱም የጉምሩክ ልዩ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 26. የድንበር ዘለል የእቃ አስተላላፊነት አገልግሎት ሰጪዎች የቅንጅት አካሄድ የሚመራበት አሠራር ማሻሻል

በሀገራችን የእቃ አስተላላፊነት የስራ ፈቃድ ወስደው በመስራት ላይ የሚገኙ አንቀሳቃሾች በጅቡቲ ወደብ እና በሌሎችም ወደቦች ከሚሰሩ ከኢትዮጵያ ወጪ የሆኑ የእቃ አስተላላፊዎች ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት እና ቅንጅታዊ አሰራር በብዙ ፈተናዎች የታጠረ እና ባህር ወደብ ላይ ያለውን የእቃ አስተላላፊ በአሰራር ሂደት አንቅፋት ቢፈጥርባቸው መብታቸውን ለማስከበር የሚችሉበት፤ እንዲሁም የውጭ የእቃ አስተላላፊዎች በኢትዮጵያዊያን የእቃ አስተላላፊዎች በኩል ውልን ጠብቆ ያለመስራት እና ክፍያ በወቅቱ ያለመክፈል ችግር ሲያጋጥም እየተፈታ ያለበት አሰራር ብዙ ውጤት እያመጣ አይደለም፡፡ ስለሆነም ይህንን አሰራር በመፈተሽ ከባለወደብ ሀገራት ጋር ዘላቂ የሆነ የእቃ አስተላላፊዎች በቅንጅት ወይም በሌላ አደረጃጀት የሚሰሩበት፤ የቁጥጥር እና የክትትል ስርኣት ይዘረጋል፡፡

## 27. የተቀናጀ የሥልጠናና የፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት

የእቃ አስተላላፊዎች እና የጉምሩክ አስተላላፊዎች ስራ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይነት ያለው እና ለአንድ ካርጎ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ አካላት ናቸው፡፡ ሆኖም ለሁለቱም የሚሰጠው የስልጠና እና የብቃት ማረጋገጥ ስርዓት የተናበበ አይደለም፡፡ ስለሆነም ለእቃ አስተላላፊዎችም ሆነ ለጉምሩክ አስተላላፊዎች ወጥ የሆነ የስልጠና እና የብቃት ማረጋገጥ ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 28. የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ የጥራት ቁጥጥር አሠራር መዘርጋት

የሎጅስቲክስ አገልግሎት ጥራት መለኪያዎችን ከዓለም አቀፍ ተሞክሮ በመቀመር የአገልግሎቱን ጥራት ለመለካት፤ለማሻሻል እና ተገቢ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችል የሎጅስቲክስ አገልግሎት የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 29. በሎጅስቲክስ አገልግሎት መስክ የተሰማሩ ኩባንያዎችና የሰው ኃይል አቅም መገንባት

በሀገራችን የሎጅስቲክስ ዘርፍ ውስጥ ያለው የሰው ሀይል አቅም በሚፈለገው ደረጃ እንዳልሆነ እና የሰው ሀይሉን የማብቃት ስርዓቱም በዚያው ልክ በበቂ ስርዓት የተደራጀ እንዳለሆነ ታይቷል፡፡ ስለሆነም የሎጅስቲክስ ዘርፍ

የሰው ሀይል አቅም ግንባታ ስርዓትን በመፈተሽ ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ስርዓት መዘርጋት እና በዘርፉ በቂ የሰው ሃይል መፍጠር ተገቢ ነው፡፡

## 30. የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች የማበረታቻ ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ

በሎጅስቲክስ የአገልግሎት መስክ የተሰማሩ ኦፐሬተሮችን ለማነቃቃትና በዘርፉ የሚሰጡ የአገልግሎት አሰጣጥን ተከታታይነት ባለው መልኩ ለማሻሻል የሚያስችል የማበረታቻ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**ንዑስ ስትራቴጂ 1.4 የትራንስፖርት አቅምን ማሳደግ (Enhance Transport Capacity)**

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች ((Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 31. የምድር ባቡር ትራንስፖርት ከመንገድ ትራንስፖርትና የጭነት ማዕከላት ጋር አቀናጅቶ አገልግሎቱን ማጠናከር

በሀገራችን የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ለማሳደግ የተጀመሩ ፕሮጀክቶች እና ወደ ፊትም የሚከናወኑ ስራዎች እቃን ከማጓጓዝ በተጨማሪ በተርሚናሎች የሚሰጡ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶችን ቀልጣፋ ከማድረግ አንጻር የባቡር ትራንስፖርት እና የጭነት ማዕከላትን፤ እንዲሁም ከመንገድ ትራንስፖርት ጋር በማስተሳሰር ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 32. የሀገሪቱ የገቢና የወጪ ዕቃዎች የትራንዚት እና የጭነት ፍሰትን ማቀናጀት

አሁን ባለው የኢኮኖሚ ደረጃችን የሀገራችን ገቢ ጭነት ከወጪ ጭነት የበለጠ በመሆኑ በትራንስፖርት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያለው እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ይህንን እና መሰል ችግሮችን ከመፋታት አንጻር የጭነት ፍሰትን በማቀናጀት ለገቢ እቃ የተጠቀምንባቸውን ፋሲሊቲዎች ለወጪ እቃም መጠቀም የሚያስችሉ የአሰራር ስርዓቶች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

## 33. የመጫን አቅማቸው ከፍተኛ የሆኑ /ከ70 - 100 ቶን/ ተሽከርካሪዎችን ማስገባት

ይህ የመፍትሄ ሃሳብ በዋናነት በተመረጡ የሀገራችን መንገዶች ላይ የተለያዩ የአሰራር እና የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀት ከፍተኛ መጠን ያለው ጭነት በአንድ ጊዜ ለማጓጓዝ የሚችሉ የጭነት ተሽከርካሪዎችን ለማሰማራት የሚያስችል ጥናት ተካሂዶ ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

## 34. ተሳቢዎችን በጐታች መኪናዎች በመጠቀም ጭነት የማጓጓዝ ሥርዓት መዘርጋት (Tractor Head Exchange System)

የመንገድ አጠቃቀምን፤ የነዳጅ ፍጆታን፤የመጫን እና የማራገፍ ጊዜን እና ሌሎችንም ሀብቶች በቁጠባ ከመጠቀም አንጻር በርከት ያሉ ጎታች መኪኖች በመጠቀም ከፍተኛ መጠን የመጫን አቅም ያላቸው ሸፍን እና ግልጽ ተሳቢዎች ለማሰማራት የሚያስችል ጥናት ተካሂዶ ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

## 35. የሀገራችን የጭነት አጓጓዥ ማኅበራት አደረጃጀት ፈትሾ ማሻሻል

በሀገራችን የጭነት ተሽከርካሪ ባለቤቶች እጅግ በጣም በርካታ ናቸው፡፡ አንድ ተሽከርካሪ ብቻ ያላቸው ባለሀብቶች ብዙ ናቸው፡፡ ይህንን የተበታተነ የተሽከርካሪ ስምሪት በተወሰነ ደረጃ ለማቀናጀት እንዲቻል የትራንስፖርት ማህበራት ተደራጅተው እየሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይሁንና ማህበራቱ ተሽከርካሪዎችን ማዘዝ የማይችሉ ከመሆኑም ባለፈ ለስነምግባር ብልሹነት በማጋለጣቸው የትራንስፖርት ስራ አመራራችንን ውስብስብ አድርጎታል፡፡ ስለሆነም የሀገራችን የጭነት አጓጓዥ ማኅበራት አደረጃጀት ወደ ንግድ ተቋምነት ለማሸጋገር የሚያስችል አሠራር ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 36. የፍሊት ማኔጅመንት አሠራር ተግባራዊ ማድረግ

የተሽከርካሪ አጠቃቀምን ለማሳደግ እና ሀብትን በብቃት ለመጠቀም እንዲቻል የስምሪት ስራ አመራር ስርዓት ''Fleet Management System'' ስራ ላይ ይውላል፡፡

## 37. የሎጅስቲክስ መስመሮችን (Logistics Routes) ማጠናከር

ይህ ሃሳብ ዋና ዋና የሎጅስቲክስ መስመሮችን በመለየት በፋሲሊቲ እና በአሰራር ስርዓት ማጠናከር ነው፡፡

## ስትራቴጂ 2 የሎጅስቲክስ ዘርፍ የፖሊሲና የህግ ማዕቀፍ ማጠናከር

*የስትራቴጂው መግለጫ*

*የሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ብቃት፣ የአገልግሎት ጥራት ደረጃ፣ የተሟላና የተቀናጀ የሎጅስቲክስ አገልግሎቶች ፓኬጅ በመስጠት ረገድ በእጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ናቸው። ይህም የውጭ ንግዳችን በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዳይሆን አድርጐታል። ለዚህ ዋናው መንስኤ ደግሞ በዘርፉ ያለው የውድድር ማዕቀፍ መጥበብ ነው። በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶች አንዳንዶቹ በአንድ መንግሥታዊ ተቋም በሞኖፖል የሚሰሩ ናቸው። አንዳንዶች ለሀገር ውስጥ የግል ኦኘሬተሮች ክፍት ቢሆኑም ለዓለም አቀፍ ኦኘሬተሮች ዝግ ናቸው። ስለሆነም የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ በዘርፉ የሚሰጡ አገልግሎቶችን በተመለከተ ለፖሊሲ ውሣኔ መነሻ ጥናቶች ላይ ተመስርቶ ለመንግስት እየቀረበ ደረጃ በደረጃ ለውድድር ክፍት ማድረግ ነዉ። በዚህም የመንግስትም ሆኑ የግል የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ተዓማኒ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት በመስጠት ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ ከፍ ማድረግ ነው። ይህን ስትራቴጂ ለመተግበር የሚከተሉት ንዑሳን ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል።*

እነርሱም፡-

ንዑስ ስትራቴጂ 2.1፡- የባህር ትራንስፖርት የአገልግሎት መስክ ፖሊሲ ማሻሻል።

ንዑስ ስትራቴጂ 2.2፡- የመልቲ ሞዳል ኦፕሬተርነት የፈቃድ አሰጣጥ ፓሊሲ ማሻሻል።

ንዑስ ስትራቴጂ 2.3፡- የፍሬት ፎርዋርዲንግ እና የመርከብ ውክልና የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ማጠናከርና ማሻሻል።

ንዑስ ስትራቴጂ 2.4፡- የደረቅ ወደብ ልማት እና አገልግሎት ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ማሻሻል።

ንዑስ ስትራቴጂ 2.5፡- የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ፖሊሲ ማጠናከርና ማሻሻል።

ለእያንዳንዱ ንዑሳን ስትራቴጂዎች ማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Interventions) ከታች በየንዑስ ስትራቴጅዎች ስር በቅደም ተከተል (Step by Step) እንደሚተገበሩ ታሳቢ ተደርጎ ተመልክቷል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 2.1 የባህር ትራንስፖርት የአገልግሎት መስክ ፖሊሲ ማሻሻል

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 38. የባህር ትራንስፖርት አገልግሎትን ቀስ በቀስ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት ማድረግ

በመጀመሪያው ምዕራፍ (በ 1 ዓመት ጊዜ ውስጥ) በኢባትሎአድ በሞኖፖል እየተሰጠ ያለው አገልግሎት ለማሻሻል እና የአገልግሎት ጥራቱና ዋጋውን ለመቆጣጠር እንዲቻል ከፍተኛ አስመጪዎች እና ላኪዎች (Major cargo owners) በድርጅቱ የአክስዮን ድርሻ እንዲገቡ በማድረግ ተቋሙ ይጠናከራል እንዲሁም የኢትዮጵያ ገቢ እቃ በኢትዮጵያ መርከብ ብቻ እንዲጓጓዝ በ1990 እና 92 የወጣው የ ‹‹FOB›› አሰራር ይከለሳል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ (ከ1 - 2 ዓመት) የኢባትሎአድ ከውጭ የመርከብ ኩባንያዎች ጋር በፖርትነርሽፕ የሚሰራበትን አሰራር ይዘረጋል፡፡

በሶስተኛው ምዕራፍ (ከ 5 ዓመት በኋላ) የባህር ትራንስፖርት አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ኩባንያዎች ክፍት ይሆናል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 2.2 የመልቲ ሞዳል ኦፐሬተርነት የፈቃድ አሰጣጥ ፖሊሲ ማሻሻል

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 39. በኢባትሎአድ ብቻ እየተሰጠ ያለውን የመልቲሞዳል ትራንስፖርት አገልግሎት ቀስ በቀስ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት ማድረግ፤

በመጀመሪያው ምዕራፍ (ከ1 — 1 1/2 ዓመት)፡- ብቸኛው የመልቲ ሞዳል አከናዋኝ የሆነው የኢባትሎአድ ሌሎች የሎጅስቲክስ አገልግሎት

ሰጪዎች አቅምን ለመጠቀም የሚያስችለው አሠራር ዘርግቶ ተግባራዊ በማድረግ አገልግሎቱን ማሻሻል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ (1 - 2 ½ ዓመት)፡- የሀገር ውስጥ የግል የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎችን ፈቃድ ለመስጠት የሚያስችል ደንብ አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ፡፡

በሶስተኛው ምዕራፍ (ከ 5 ዓመት በኋላ)፡- የመልቲ ሞዳል ኦፕሬተርነት የአገልግሎት ዘርፍ ሙሉ ለሙሉ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት ማድረግ፡፡

**ንዑስ ስትራቴጂ 2.3 የዕቃ አስተላላፊነት የአገልግሎት ዘርፍ ላይ ለመሰማራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ማጠናከርና ማሻሻል**

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች ((Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 40. የእቃ አስተላላፊነት የአገልግሎት ዘርፍን ቀስ በቀስ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት ማድረግ

በመጀመሪያው ምዕራፍ (1 ዓመት) የሀገር ውስጥ የዕቃ አስተላላፊ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች በተመረጡ አገልግሎቶች ከውጭ ኩባንያዎች ጋር በፓርትነር ሽፕ በመስራት አቅማቸው እንዲጠናከር ይደረጋል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ (1 ½ ) የሀገር ውስጥ የዕቃ አስተላላፊ አገልግሎት ሰጪ ኩባንያዎች ከውጭ ሀገር ኩባንያዎች በሁሉም አገልግሎቶች በፖርትነርሺፕ ለመስራት የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል፡፡

በሶስተኛው ምዕራፍ (ከ 2 ዓመት በኋላ) የዕቃ አስተላላፊነት አገልግሎት መስክን ሙሉ ለሙሉ ለዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ክፍት ይሆናል፡፡

**ንዑስ ስትራቴጂ 2.4 የደረቅ ወደብ ልማት እና አገልግሎት ዘርፍ ለመሰማራት የሚያስችል የፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት ማሻሻል**

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 41. የደረቅ ወደብ አገልግሎት ቀስ በቀስ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ኦፕሬተሮች ክፍት ማድረግ፡፡

በመጀመሪያው ምዕራፍ (1 - 2 ዓመት)፡- የደረቅ ወደብ ኦፐሬሽን አገልግሎት በብቸኝነት እየሰጠ ያለው የኢባትሎአድ የደረቅ ወደብ መሠረተ ልማት የመገንባትና የጋራ የአገልግሎት መስጫ ባለቤት በመሆን በደረቅ ወደብ ውስጥ የሚሰጡ ልዩ ልዩ የኦፐሬሽን ተግባራት በግል የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችና የጭነት ባለቤቶች የሚከናወኑበት አሠራር ይዘረጋል፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ (ከ2 ዓመት በኋላ)፡- የደረቅ ወደብ አገልግሎት እና የኮንቴይነር ፍሬት ስቴሽን ፤ የሎጅስቲክስ ፓርኮች ሙሉ ለሙሉ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ኦፕሬተሮች ክፍት ማድረግ፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 2.5 የመንገድ ትራንስፖርት ዘርፍ ፖሊሲ ማሻሻል

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 42. የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ቀስ በቀስ ለዓለም አቀፍ ገበያ ክፍት ማድረግ፤

በመጀመሪያው ምዕራፍ (በ 1 ዓመት ጊዜ) የሀገር ውስጥ የትራንስፖርት ኩባንያዎችን ብቃት በማሻሻል የመወዳደር አቅማቸውን ለማሳደግ የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከጐረቤት ሀገሮች የትራንስፖርት ኩባንያዎች ጋር በሽርክና እንዲሰሩ ክፍት ማድረግ፡፡

በምዕራፍ ሁለት (በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ) የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለጐረቤት ሀገሮች የትራንስፖርት ኩባንያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲሰሩ ክፍት ማድረግ፡፡

በምዕራፍ ሶስት (ከ5 ዓመት በኋላ) የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ለዓለም አቀፍ የትራንስፖርት ኩባንያዎች ገበያ ክፍት ማድረግ፡፡

## ስትራቴጂ 3 የተሳለጠና አስተማማኝ የጉምሩክና የትራንዚት ሥርዓት መዘርጋት

*የስትራቴጂው መግለጫ*

የስትራቴጂው ዋና ዓላማ በዕቃዎች ፍሰትና እንቅስቃሴ ሚና ያላቸው ተቆጣጣሪ ተቋማት አሠራር ቀላል፣ የተቀናጀና የተቀላጠፈ ማድረግ ነው፡፡ ይህን ስትራቴጅ ለማሳካት የሚከተሉት ንዑሳን ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ንዑስ ስትራቴጂ 3.1 | ውጤታማ የጉምሩክና የፋሲሊቴሽን አሠራር መዘርጋት፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 3.2 | ውጤታማ የትራንዚት የወደብ ኦፐሬሽን አሠራር መዘርጋት፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 3.3 | የኮሪደር አጠቃቀምን ማሳደግ፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 3.4 | የወደብ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ |

ለእያንዳንዱ ንዑሳን ስትራቴጂዎች ማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሣቦች (Interventions) ከታች ተመልክቷል፡፡

### ንዑስ ስትራቴጂ 3.1 ውጤታማ የጉምሩክና የፋሲሊቴሽን አሠራር መዘርጋት

### 43. ብሄራዊ የአንድ መስኮት አገልግሎት ማቋቋም

በገቢና ወጪ ዕቃዎች የትራንዚት ሂደትና በአጠቃላይም በውጭ ንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ በርካታ ተዋናዮች አሉ፡፡ የእነዚህ ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪ አካላት /ባንኮች፣ ኢንሹራንስ፣ የመርከብ ኩባንያዎች፣ ፍሬትፎርዋርደሮች/በተበታተነ መልኩ መሆን ሂደቱን የተንዛዛ ጊዜ የሚወስድና ወጪን የሚያንር በመሆኑ እነዚህን በተበታተነ መልኩ የሚሰጡ የሥራ ሂደቶችና በርካታ የሰነድ ቅብብሎሽ በአንድ ማዕከል እንዲሆኑና በ"IT" የተደገፉ በማድረግ የተሳለጠና ዘመናዊ ለማድረግ ብሄራዊ የአንድ መስኮት አገልግሎት (National Single Window) ይቋቋማል፡፡ ለዚህም በኢትዮጵያ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን አስተባባሪነት የተጀመረ ፕሮጀክት ያለ ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርሜሽን

ዓላማን ከማሣካት አንጻር በመቃኘትና የትግበራ ሂደቱም እንዲፋጠን ይደረጋል፡፡

## 44. ቀጠናዊ (Regional) የአንድ መስኮት አገልግሎት ማቋቋም

ሀገራችን ወደብ አልባ በመሆኗ ለውጭ ንግድ የወደብ አገልግሎት የምታገኘው በጐረቤት ሀገሮች ወደቦች ነው፡፡ በመሆኑም በሀገር ውስጥ በሎጅስቲክስ ሂደት ቁልፍ ሚና ያላቸው ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪ አካላትን ብቻ በማቀናጀት ብሄራዊ የአንድ መስኮት አገልግሎት ማቋቋም በራሱ የተሟላ መፍትሄ አይሆንም፡፡ በባህር ወደቦች በተመሳሳይ መልኩ ከሚቋቋሙ የአንድ መስኮት አገልግሎት ማዕከላት ጋር በተቀናጀ መልኩ መሥራትና ትስስር መፍጠር የግድ ይላል፡፡

## 45. የጉምሩክ አሠራር የማሻሻያ ኘሮግራም

ገቢ ዕቃዎችን ከባህር ወደብ ከመርከብ በተራገፈ በጥቂት ቀናት ውስጥ ወደ መድረሻ ጣቢያ ለማጓጓዝና፣ ወጪ ዕቃዎችን ደግሞ ከሀገር ውስጥ መነሻ ቦታ በባህር ወደብ ለመርከብ ጭነት ዝግጁ ለማድረግ እየወሰደ ያለው የጉምሩክና የትራንዚት ሂደት ረጅም ነው፡፡ ይህን ችግር የሚፈታ የጉምሩክ አሠራረ ማሻሻያ ኘሮግራም መንደፍና መተግበር አንድ የመፍትሄ ሃሣብ ነው፡፡

## 46. በሀገሪቱ የውጭ ንግድ መግቢያና መውጫ ድንበሮች/ ኬላዎች ስታንዳርድ የጉምሩክ አሠራር መዘርጋት

የሀገራችን የገቢና የወጪ ዕቃዎች እየተስተናገዱ ያሉባቸው እና በቀጣይም የሚስተናገዱባቸው ኬላዎች በርካታ ናቸው፡፡ ለምሣሌ ጋላፊ፣ ሞያሌ፣ መተማ፣ ሁመራ፤ ደወሌ፣ ቡሬ፣ ዛላንበሳ፣ ራማ ወዘተ. ሲሆኑ፣ በእነዚህ ኬላዎች የሚሰጠው የጉምሩክ አሠራር ወጥ የሆነ አይደለም፡፡ ይህ ደግሞ የጭነት እንቅስቃሴን የሚያስተጓጉልና አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር በመሆኑ በሁሉም የጉምሩክ ኬላዎች ወጥ የሆነ የተቀላጠፈ አሠራር መዘርጋት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 47. በሞጆ ደረቅ ወደብ የተቀናጀና ቀልጣፋ የጉምሩክ አሠራር መዘርጋት

የሞጆ ደረቅ ወደብ ዋነኛውና ትልቁ የሀገራችን የሀገር ውስጥ ደረቅ ወደብ ነው፡፡ ይህ ወደብ በሀገራችን የሎጅስቲክስ አገልግሎት እያጋጠሙ ያሉትን ችግሮች ለመፍታት በሚያስችል መልኩ ወደ ሎጀስቲክስ ማዕከልነት የሚያሸጋግረው ኘሮግራም ተቀርጾ ተግባራዊ እየሆነ ነው፡፡ በዚህ ትልቅ የሎጅስቲክስ ማዕከል ውስጥ በሞዴልነት የሚያገለግል የተሻሻለና ቀልጣፋ አዲስ የጉምሩክ አሠራር ይዘረጋል፡፡ በቀጣይም በሌሎች የጭነት ማዕከሎች በሞዴልነት ተወስዶ ይተገበራል፡፡

## 48. የትራንዚት የፍተሻ ጣቢያዎች መቀነስ እና ጊዜን ማሳጠር

የገቢ ዕቃዎች ከባህር ወደብ እስከ መድረሻ ቦታ፣ የወጪ ዕቃዎች ደግሞ ከመነሻ ቦታ እስከ ወደብ ድረስ ሲጓጓዝ የፍተሻ ጣቢያዎች መብዛት ለተንዛዛ የትራንዚት ሂደት ዳርጓል፡፡ ስለሆነም የፍተሻ ጣቢያዎች ቁጥር ለመቀነስ እና ለፍተሻ የሚወስደውን ጊዜ ለማሳጠር የሚያስችል ኘሮግራም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 49. ነፃ የኮንቴይነር ዝውውር ሥርዓት መዘርጋት

ኮንቴይነር የመርከብ አካል ነው፡፡ የገቢ ዕቃን በመያዝ አብዛኛው ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡት ኮንቴይነሮች የመርከብ ኩባንያዎች ናቸው፡፡ የኮንቴይነሮቹ ባለቤቶች /የመርከብ ኩባንያዎች/ ኮንቴይነሩን ለቀጣይ ጭነት ስለሚያስፈልጋቸው ኮንቴይነሩ እንዲመለስና በሀገር ውስጥ እንዳይቀር ይፈልጋሉ፡፡ በሌላ በኩል ኮንቴይነሩን የወጪ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ በኮንቴይነር አሽጉ ለመላክ ይፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም የኮንቴይነር ነፃ እንቅስቃሴ ማለትም ኮንቴይነሮች ወደ ሀገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ለማስወጣት የሚያስችል ቀላልና ቀልጣፋ አሠራር ይዘረጋል፡፡

## 50. የጋራ የጉምሩክ አገልግሎት ቀጠና ማቋቋም

የዕቃዎች ፍሰት በሰነድና በገንዘብ ፍሰት አሠራር ይወሰናል፡፡ በተለይም የጉምሩክ አሠራር ወሣኝ ነው፡፡ በተለይም የውጭ ንግድ ዕቃዎች የሌሎች ሀገሮች ድንበር (Territory) ተሻግረው የሚገቡና የሚወጡ ሲሆን፣ የየሀገሩ የተለያየ የጉምሩክ ፎርማሊቲና አሠራር ትልቅ እንቅፋት ነው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት የየሀገራቱ የጉምሩክ ተቋማት በጋራ ከመሥራት ጀምሮ የትራንዚት ሂደትን ከማቀላጠፍ እንጻር በረጅም ሂደት የጋራ የጉምሩክ

ቀጠና (Single Customs Territory) በማቋቋም የውጭ ንግድ የዕቃ ፍሰትን የተቀላጠፈ ለማድረግ የሚያስችል ኘሮግራም ይተገበራል፡፡

## 51. የሰነድ መጠን መቀነስ

ከመሠረታዊ የሎጅስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያዎች ውስጥ አንዱ የአገልግሎት አሰጣጥ ውስብስብነት (Complexity) ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ ፎርማሊቲዎችን ለማጠናቀቅ በጉምሩክና በሌሎች ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚጠይቁ የሰነዶች ብዛት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለትራንዚት ሂደት መንዛዛት ስለሚዳርግ የሰነድ ብዛትን መቀነስ አንድ የመፍትሄ ሃሣብ ነው፡፡

## 52. የወደብ አልባ ሀገሮች የቬና ኘሮግራም መተግበር

በዓለም አቀፍ የወደብ አልባ ሀገሮች የትራንዚት ትራንስፖርት ችግሮችን ለመፍታት የሚያግዝ የ"UN" አካል አለ፡፡ ይህ አካል ባሁኑ ወቅት "Veina Programme of Action" አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ሲሆን፣ ሀገራችንም ከወደብ አልባ ሀገሮች ከፍተኛውን የህዝብ ብዛት ያላት ከመሆኗ አንጻር በቂ ተሳትፎ ማድረግና በጋራ የወጡ ችግር ፈቺ ኘሮግራሞችን መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ጉዳዩን የሚከታተል "Focal Point" በመሰየምና የክትትል አሠራር ተዘርግቶ መተግበር ይኖርበታል፡፡

## 53. ጭነትን በከፊል የመልቀቅ አሠራር ሥርዓት መዘርጋት

በደረቅ ወደቦች የጭነት መከማቸት አለ፡፡ የዕቃዎች የቆይታ ጊዜ በጣም ረጅም ነው፡፡ ችግሩን ለመፍታት መወሰድ ካለባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ውስጥ አንዱ አስመጪዎች ካለባቸው የገንዘብ (Capital)፣የመጋዘንና የገበያ እጥረትን ግምት ውስጥ በማስገባት ካላቸው ጭነት ውስጥ ባላቸው ዓቅም መሠረት የተወሰነ ጭነትን የጉምሩክ ስነስርዓት ፈጽመው ለማስወጣት የሚያስችል ዕቃን በከፊል (Partial Shipment) የሚለቀቅበት የጉምሩክ አሠራር ይዘረጋል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 3.2 ውጤታማ የትራንዚት የወደብ ኦፐሬሽን አሠራር መዘርጋት

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው።

### 54. በባህር ወደብ የሞኖፖሊ አሠራር ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት

በባህር ወደቦች የሚሰጡ ስቴቬዶሪንግ፣ የሾር ሀንድሊንግና ተዛማጅ የተርሚናል አገልግሎቶች ለአንድ ተቋም በብቸኝነት የሚሰጥ ከሆነ ከአገልግሎት ጥራት፣ ከዋጋና መሰል መለኪያዎች አኳያ ሊገኝ የሚችል ጥቅምን ያሳጣል። በወድድር ሊገኝ የሚችል ብዙ ሀገራዊ ጠቀሜታን ለማስጠበቅ በባህር ወደቦች የተርሚናል ኦፕሬተሮች በውድድር የሚሰሩበት አሠራር እንዲኖር ከባለ ወደብ ሀገሮች ጋር በጥናት ላይ የተመሠረተ ድርድርና ስምምነት መፈጸም ይኖርበታል። በልላ በኩል ለውድድር ክፍት ያልሆኑ የአገልግሎት መስኮች የቁጥጥር ሥራ (Regulation) መዘርጋት አስፈላጊ ነው።

### 55. በባህር ወደቦች የአንድ መስኮት አገልግሎት እንዲቋቋም ማድረግ

በባህር ወደብ የትራንዚት ዕቃዎችን የወደብና የጉምሩክ ፎርማሊቲዎችን አጠናቆ ለማጓጓዝ የበርካታ ተቆጣጣሪና አገልግሎት ሰጪዎች /ጉምሩክ፣ የወደብ ባለሥልጣን፣ የመርከብ ወኪል…ወዘተ/ ድርሻ አለ። ይህ በተበታተነ መልኩ ሲሆን፣ ደግሞ ይበልጥ ጊዜ ወሳጅና ወጪን የሚያንር ነው። ይህን ችግር ለመፍታት የጅቡቲ ወደብ ኮሙኒቲ በማቋቋም የተፋጠነና ወጥ የሆነ የአንድ መስኮት አገልግሎት ማዕከል መስጠት አስፈላጊ ነው።

## ንዑስ ስትራቴጂ 3.3 የኮሪደር አጠቃቀምን ማሳደግ

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው።

## 56. በባህር ወደቦችና የትራንዚት ኮሪደሮች የአፈጻጸም መለኪያ ማዳበርና የክትትል ሥርዓት መዘርጋት

የባህር ወደቦችም ሆኑ ኮሪደሮች የአፈጻጸም ቁልፍ መለኪያዎች ያሉት ሲሆን፣ በነዚህ ቁልፍ መለኪያዎች መሠረት በየጊዜው ተከታታይነት ባለው መንገድ አፈጻጸሙን የመለካት፣ በክፍተት የሚታዩትን ችግሮች የሚፈታ ኘሮግራም በማዘጋጀት ለመተግበር የወደቦችና የኮሪደሮች የአፈጻጸም የክትትል ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 57. የጋራ የድንበር ቁጥጥር (One Stop Boarder Post) ማቋቋም

ለጭነት የትራንዚት ጊዜ መራዘም፣ የውጪ ንግድ የሚያንገዙ ተሽከርካሪዎች እና ባቡር በየቦታው የመቆምና ተያያዥ ችግሮች በባለወደብ ሀገሮችም ሆነ በኢትዮጵያ በኩል የጉምሩክና መሰል የቁጥጥር ሥራን ለመሥራት በርካታ የፍተሻ ጣቢያዎች አሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በትራንዚት ሂደቱ ማነቆዎች ናቸው፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት አንድ የጋራ የፍተሻ ጣቢያ (One Stop Boarder Post) አቋቁሞ መተግበር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 58. የመንገድ የክብደት ህግ ማጣጣም

በኢትዮጵያና በባለወደብ ሀገሮች ያለው የመንገድ የክብደት ህግ (Axle Load Limitation) የተጣጣመ ካልሆነ በትራንዚት ትራንስፖርቱና በተለይም በተሽከርካሪዎች የጉዞ እንቅስቃሴና በጭነት ፍሰት ላይ ችግር ያጋጥማል፡፡ ይህን ችግር ለመፍታት የመንገድ የክብደት ህግ እንዲጣጣም ከጎረቤት ሀገሮች ጋር በመነጋገርና የጋራ ስምምነት ላይ የተመሠረተ ወጥ ህግ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 59. የትራንዚት ኮሪደር ማኔጅመንት ባለሥልጣን ማቋቋም

የድንበር ዘለል የትራንዚት ትራንስፖርት አሠራር የተሳለጠ ለማድረግ በኢትዮጵያና በባለወደብ ሀገሮች የሚገኙ የሚመለከታቸው አካላት ተቀናጅተው ሲሰሩ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በትራንዚት ትራንስፖርት ሂደቱና በአጠቃላይ በኮሪደሮች የሚሰጠው አገልግሎት የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመፍታትና ተከታታይነት ያለው የማሻሻያ ኘሮግራሞች በጋራ እያቀዱ፣ በጋራ እየተገበሩ፣ በጋራ እየገመገሙ ለመሄድ የሚያስችል ከኢትዮጵያና ከባለወደብ ሀገሮች የተውጣጣ የኮሪደር ማኔጅመንት ባለሥልጣን

ይቋቋማል። ይህም በኮሪደሮች የሚሰጠውን አገልግሎት ፈጣንና የተሳለጠ ለማድረግ ወሣኝ ነው።

| ንዑስ ስትራቴጂ 3.4 የወደብ አጠቃቀምን ማሳደግ |
| --- |
| የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው። |

## 60. የባህር ወደብ በጋራ ማልማት

የወደብ አገልግሎት በብቸኛ የወደብ አልሚዎች ከተያዘ ዘርፈ-ብዙ ጉዳት አለው። የሀገራችን የውጭ ንግድ በሚስተናገድበት የባህር ወደብ በመገኘት ብሄራዊ ጠቀሜታን ለማስጠበቅ፡ በባህር ወደቦች በየጊዜው ያለምንም ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የታሪፍና የአሠራር ለውጥ የማድረግ አሠራርን ለማስቀረት እንደሀገር በባህር ወደቦች በጋራ የማልማት ስራ ላይ የተሟላ ተሳትፎ ይደረጋል።

## 61. ቀጠናዊ "Regional" የባህር ወደብ የሎጅስቲክስ ማዕከል እንዲኖር መሥራት

የትራንስፖርት ወጪ በተለይም የባህር ትራንስፖርት ወጪን ለመቀነስ አንዱና ወሣኝ ሁኔታ ከፍተኛ የጭነት መጠን (Economy of Scale) እንዲኖር ማድረግ ነው። ከፍተኛ የመጫን አቅም ያላቸው መርከቦች የሚያስከፍሉት የትራንስፖርት ዋጋ በአንጻራዊ ዝቅተኛ ነው። እንደነዚህ ዓይነት መርከቦች ለመጠቀም ደግሞ ጭነትን የማሰባሰብና መርከቦቹን ለማስተናገድ ዓቅምና ብቃት ያለው ትልቅ ወደብ መገንባትን ይጠይቃሉ። ይህም ከአካባቢ ሀገሮች ለጋራ ጥቅም በጋራና በትብብር በመሥራት ቀጠናዊ "Regional" የባህር ወደብ መገንባት በጣም ጠቃሚ ነው።

## 62. በባህር ወደብ ለረጅም ጊዜ የሚከማቹ እና ባለቤት የሌላቸውን እቃዎችን ለማንሳት ያሚስችል አሰራር መዘርጋት

ሀገራችን በምትጠቀምባቸው ወደቦች በተለይም በጅቡቲ ወደብ አስመጪዎች በተለያየ ምክንያት በወቅቱ የማያነሷቸው እቃዎች በርካታ ናቸው። ስለሆነም እነዚህ እቃዎች ለማስተዳደር የሚያስችል የአሰራር ስርዓት እና ተቋም ይደራጃል።

## ስትራቴጂ 4 አስተማማኝ የንግድና የፋይናንስ ሥርዓት በመዘርጋት በሎጅስቲክስ የማሳለጥ ሚናውን ማጐልበት

*የስትራቴጂው መግለጫ*

የንግድና የፋይናንስ ሥርዓቱ የሉጅስቲክስ ጊዜና ወጪን ለመቀነስና የሉጅስቲክስ ሥርዓቱን ትራንስፎርም ለማድረግ በሚያግዝ ደረጃ ማሻሻል የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ ነው፡፡ ስለሆነም ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ንዑሳን ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ንዑስ ስትራቴጂ 4.1 | ቀልጣፋና ውጤታማ የንግድ ፋይናንስ አሠራር መዘርጋት፤ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 4.2 | የምርት ትስስርን መሰረት ያደረገ (Production Network) የሎጅስቲክስ አገልግሎት መዘርጋት፤ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 4.3 | ዘመናዊ የገቢ ንግድ የስርጭት ትስስር መዘርጋት (Distribution Network) |

### ንዑስ ስትራቴጂ 4.1 ቀልጣፋና ውጤታማ የንግድ ፋይናንስ አሠራር መዘርጋት

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 63. የባንክ ትራንዛክሽን ክፍያን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራር መዘርጋት

በሀገራችን የሎጅስቲክስ ወጪ የሚያንሩ ከቅልጥፍና ማነስ (inefficiency) እና የአገልግሎት ሰጪዎች የክፍያ መጠን ከፍተኛ ከመሆን ጋር የተያያዙ በርካታ ሁኔታዎች አሉ፡፡ ለባንክ ፈቃድና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚጠየቀው ተመንም ከፍተኛ በመሆኑ በተለይም በአስመጪዎች ዘንድ የወጪ ጫና የፈጠረ መሆኑ ታይቷል፡፡ ይህ ተመን የሎጅስቲክስ ወጪን በማናር ረገድ የሚያስከትለው ተጽዕኖን ለማስቀረት በብሄራዊ ባንክ በኩል ተመኑን ለመቆጣጠር የሚያስችል አሠራር ይዘረጋል፡፡

## 64. የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት የሚስተናገድበት አሠራር ማሻሻል

የሀገራችን የገቢ ዕቃዎችን ትዕዛዝ ከመስጠት ጀምሮ እስከመረከብ ያለው ጊዜ (Lead Time) በጣም ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ትልቁ ድርሻ አስመጪዎች የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የሚወስደው ጊዜ ነው፡፡ ከአስመጪዎች ከተሰበሰበው መረጃ ለመገንዘብ የተቻለው የውጭ ምንዛሪ እጥረቱ የፈጠረው አስመጪዎችን በእኩል ያለማስተናገድ ችግር አለ፡፡ ይህም በሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ በመሆኑ ይህ አሠራር እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

## 65. ከወደቦች ጭነት በወቅቱ የማያነሱ አሰመጪዎች የተጠያቂነት አሠራር መዘርጋት

የሀገራችን የገቢ ዕቃዎች የወደቦች ላይ ቆይታ በጣም ረጅም ነው፡፡ በዚህ ረገድ የአስመጪዎች ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ጭነታቸውን በወቅቱ (Reasonable time) የማያነሱ አስመጪዎች ተጠያቂ የሚያደርግ አሠራር መዘርጋት አንዱ ተግባር ነው፡፡

## 66. ከጐረቤት ሀገሮች የሚደረግ የንግድ ልውውጥ ማሳደግ

የሀገሪቱ የሎጅስቲክስ ወጪ ከሀገሪቱ ጥቅል ምርትም (GDP) ሆነ ከዕቃው ዋጋ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ሁኔታዎች አንዱ የሀገራችን የንግድ ልውውጥ ከሩቅ ምሥራቅ በመሆኑ የባህር ማጓጓዣ ወጪው ከፍተኛ መሆን ነው፡፡ ሌሎች ሀገሮች የንግድ ልውውጣቸውን ከአካባቢው ሀገሮች በማድረግ የሎጅስቲክስ ወጪአቸውን ለመቀነስ ችለዋል፡፡ የሀገራችን የንግድ ልውውጥም በተጠና አካሄድ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከጐረቤት ሀገሮች ያለንን የንግድ ልውውጥ በማሳደግ ሀገራዊ የሎጅስቲክስ ወጪን መቀነስ አንዱ መፈጸም ያለበት ተግባር ነው፡፡

## 67. አስመጪዎችና ላኪዎችን የሚያግዝ አዲስ የፋይናንስ የድጋፍ አሠራር መዘርጋት

የውጭ ንግድ ዕቃዎች በተለይም የገቢ እቃዎች የወደብ ላይ ቆይታ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ከአስመጪዎች የገንዘብ ዓቅም/እጥረት ጋር ይያያዛል፡፡ ጭነቱን በወቅቱ ከወደብ ለማንሳት ለባንክ የሚከፈል፣ ለገቢዎችና ጉምሩክ የሚከፈል ታክስ፣ ቀረጥና ሌሎች የገንዘብ ዓቅምን የሚፈታተኑ ክፍያዎች ያስፈልጋሉ፡፡ ስለሆነም ለአስመጪዎች የተለያዩ የፋይናንስ ድጋፍ ለምሣሌ

"Import Financing" አሠራር በመዘርጋት የንግድ ሂደቱ እንዲሳለጥ ማድረግ አንዱ መፈጸም ያለበት ተግባር ነው፡፡

## 68. ለባህር ወደብ አገልግሎት ቀላልና ውጠታማ የክፍያ ሥርዓት መዘርጋት

በባህር ወደቦች ለሚሰጡ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች የሚከፈለው በውጭ ምንዛሪ ሆኖ አገልግሎት ከተሰጠ በኋላ ነው፡፡ አሁን ባለው አሠራር በኢትዮጵያውያን የእቃ አስተላላፊዎች እና በጅቡቲ ትራንዚተሮች መካከል ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል፡፡ አንዳንዴም ክፍያ ከመዘግየቱ የተነሳ ዕቃዎችን በመያዣነት በወደብ ላይ እንዲቆዩ ይደረጋሉ፡፡ በአጠቃላይ አሁን ያለው አሠራር ያሉበትን ክፍተቶች የሚቀርፍ አዲስ የክፍያ ሥርዓት ይዘረጋል፡፡

## 69. ነፃ የንግድ ቀጠና ማቋቋም

በሀገራችን ያለው የውጭ ምንዛሪ ለመቆጣጠር የወጡ አሠራሮችና የፋይናንስ ዘርፍ ፖሊሲን በማገናዘብ የሀገራችን የገቢ ዕቃዎች ትዕዛዝ ከመስጠት ጀምሮ እስከመረከብ ያለው ጊዜ "Lead Time" ለመቀነስ፣ በማኑፋክቸሪንግ የተሰማሩ ኢንቨስተሮችን ችግር ለመፍታት፣ የንግድ ሂደቱን ለማሳለጥና የሎጅስቲክስ ጊዜና ወጪ ለመቀነስ እንዲያስችል በተመረጡ ቦታዎች ነፃ የንግድ ቀጠና (Free Trade Zone) ይቋቋማል፡፡

**ንዑስ ስትራቴጂ 4.2 የምርት ትስስርን መሰረት ያደረገ (Production Network) የሎጅስቲክስ አገልግሎት መዘርጋት፤**

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች ((Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 70. የፕሮዳክሽንና የሎጅስቲክስ አቅርቦት ማስተር ኘላን ማዘጋጀት

ለሀገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት የአግሮ ኘሮሰሲንግና ቀላል የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ትልቅ ሚና እንዳላቸው ይታመናል፡፡ ይህን የኢኮኖሚ ዘርፍ ለመደገፍና በዓለም የተወዳዳሪነት ብቃቱን ለማሳደግ አስተማማኝ የሎጅስቲክስ አቅርቦት ወሣኝ ነው፡፡ ለዚህም የሀገሪቱን የኘሮዳክሽን ማዕከላትና ቦታዎችን ግምት ውስጥ ያስገባ ሀገራዊ ማስተር ኘላን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 71. የኮንሰሊደሽን ሥርዓት መዘርጋት

የሀገራችን የዕቃዎቹ ወይም የጭነቶቹ ልዩ ባህሪን ያገናዘበ የኮንሰሊደሽን ሥርዓት ይዘረጋል።

## 72. በቀላሉ ለሚበላሹ ዕቃዎች ዘመናዊና ውጤታማ የሎጅስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት

በቀላሉ የሚበላሹ ዕቃዎች እንደ ጭነቶቹ ባህሪይ የተለየ የማጓጓዣ ዘዴና ልዩ ፋሲሊቲ እንደሚያስፈልግ ይታወቃል። የአገልግሎት ሰጪዎችም የጭነት ዓይነቶች ልምድ፣ ልዩ ሥልጠናና ዕውቀት ያስፈልጋቸዋል። እንደነዚህ ዓይነት ፋሲሊቲና የማስተናገድ ዓቅምን ያገናዘበ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ይዘረጋል።

## 73. ዘመናዊ የላብራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ መዘርጋት

ለውጭ ንግድ ዕቃዎች የተሳለጠ የትራንዚት አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ አስተማማኝ ቀልጣፋና ዘመናዊ የላብራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ መዘርጋት ነው። ስለሆነም ለሀገራችን ወጪና ገቢ እቃዎች የሚሰጠው የላብራቶሪ አገልግሎት ቀናትን የሚወስድ እና ዘመናዊ ባለመሆኑ በሎጅስቲክስ ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል። በመሆኑም ዘመናዊ የላብራቶሪ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት ይዘረጋል።

**ንዑስ ስትራቴጂ 4.3 ዘመናዊ የገቢ ንግድ የስርጭት ትስስር (Distribution Network) መዘርጋት**

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው።

## 74. ዘመናዊ የገቢ ንግድ አሠራር ማስተር ኘላን ይተገበራል

ለሀገራችን የገቢ ንግድ የተሳለጠ አገልግሎት ለመስጠት ዘመናዊ የንግድ ስርጭትና ትስስር መዘርጋት ወሣኝ ሲሆን፣ ለዚህም የስርጭት ኔትወርክ ማስተር ኘላን ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል።

## 75. ከተሞች የሎጅስቲክስ አሠራር መዘርጋት

የከተሞች ዕድገት፣ የትራፊክ መጨናነቅና ይህን ተከትለው የሚመጡ ችግሮችን ለመፍታት ለከተሞች የጭነት ሥርጭት ማዕከላት ማቋቋም፣ የትራንስፖርት ኔትዎርክ መዘርጋትና የከተማ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ማፍራትን ይጠይቃል፡፡ ይህ በሥርዓት ለመምራት የከተሞች የሎጅስቲክስ አሠሪር ይዘረጋል፡፡

## 76. የአየር ብክለትን ለመቀነስ የሚያስችል የሎጅስቲክስ አሠራር መዘርጋት

በሀገር ውስጥ በሚገነቡ የሎጅስቲክስ ማዕከላት እና የደረቅ ወደቦች የአካባቢ እና የአየር ብክለትን በሚከላከል እና የአረንጓዴ ልማት ስትራቴጅን ለመፈጸም በሚያስችል መልኩ እንዲከናወኑ ጠንካራ የቁጥጥር እና የክትትል ስርዓት ይዘረጋል፡፡

# ስትራቴጂ - 5 የሎጅስቲክስ መሠረተ - ልማት መገንባት

*የስትራቴጂው መግለጫ*

የስትራቴጂው ዋና ዓላማ በሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ቁልፍ ሚና ያለው የሎጅስቲክስ መሠረተ-ልማት አቅርቦት ማሻሻል ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካትም የሚከተሉት ንዑሳን ስትራቴጂዎች ተነድፈዋል፡፡ እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ንዑስ ስትራቴጂ 5.1 | የሎጅስቲክስ ማዕከላትና ፋሲሊቲዎችን መገንባት፣ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 5.2 | የትራንስፖርት መሠረተ - ልማት መገንባት |
| ንዑስ ስትራቴጂ 5.3 | የሎጅስቲክስ ሥርዓት ለማሻሻል የሚያስችል የ"IT" ግንባታ ማከናወን |

## ንዑስ ስትራቴጂ 5.1 የሎጅስቲክስ ማዕከላትና ፋሲሊቲዎችን መገንባት

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

## 77. የሀገሪቱ የሎጅስቲክስ (የጭነት ማዕከላት) ማስተር ኘላን ማዘጋጀት፡፡

የሀገራችን የጭነት ማጓጓዝ እና ለተጠቃሚዎች በማድረስ ሂደት የሎጅስቲክስ ማዕከላት ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በአሁኑ ወቅት የጭነት መኪኖችን እና መርከብን እንደመጋዘን በመጠቀም ለረጅም ጊዜ ጭነት ሳይራገፍ የሚቆይበት ዋናው ምክንያት በሀገር ውስጥ የጭነት ማዕከላት፤ የሎጅስቲክስ ፓርኮች እና መሰል ተርሚናሎች በተጠና መልኩ በበቂ ያለመኖር ነው፡፡ ስለሆነም በሀገር ውስጥ የጭነት ማዕከላትን ለመገንባት ወጥ የሆነ እና የቀጣይ የእድገት አቅጣጫን ታሳቢ ያደረገ ሀገር አቀፍ ማስተር ፕላን ይዘጋጃል፡፡

## 78. የሞጆ ደረቅ ወደብን ወደ የሎጅስቲክስ ማዕከልነት (Logistics hub) ማሳደግ፤

የሞጆ ደረቅ ወደብ አሁን ካለው ከጉምሩክ ስነስርዓት የማስፈጸም አገልግሎት መስጠት በተጨማሪ ሌሎች እሴት የሚጨምሩ የኤክስፖርት ፕሮሰሲንግ፤ ፓኪንግ፤ የመገጣጠም እና ሌሎች የሎጅስቲክስ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችል የሎጅስቲክስ ማዕከል (Logistics hub) ሆኖ ይገነባል፡፡ እንዲሁም በሞጆ ደረቅ ወደብ የባቡርና የመንገድ ትራንስፖርትን በማስተሳሰር፤ ለገቢና ለወጪ ዕቃዎች የተሟላ አገልግሎት በመስጠት በአጠቃላይ በሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ውስጥ ቁልፍ ሚና እንዲኖረውና ለሌሎችም የደረቅ ወደቦችም አሠራሩን ለመዘርጋት ሞዴል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 79. ዋና ዋና የምርት ማዕከላትን ከሎጅስቲክስ ማዕከላት ጋር የሚገናኙበት ኔትዎርክ መገንባት፡፡

በሀገሪቱ ሁሉም አካባቢዎች የሚመረቱ የግብርና፤የማኑፋክቸሪንግ እና የማዕድን ምርቶችን በወቅቱ እና በተመጣጣኝ ወጪ ለተጠቃሚ ለማድረስ እንዲቻል የምርት ማዕከላቱን ከሎጅስቲክስ አገልግሎት መስጫ ማዕከላት ጋር የሚያስተሳስር ኔትወርክ ይዘረጋል፡፡

## 80. ለሚበላሹ ጭነቶች የቀዝቃዛ መጋዘኖችና ተያያዥ ፋሲሊቲዎችን መገንባት

ሀገራችን ፍራፍሬ፤አበባ፤ስጋ እና ሌሎችም በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ

ምርቶችን የማምረት አቅም እንዳላት ይታወቃል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ምርቶች ለገበያ በማቅረብ ሂደት ሎጅስቲክስ ቁልፍ ሚና አለው፡፡ ይህን ከግምት በማስገባት በሀገር ውስጥ የሚገነቡ የሊጅስቲክስ ማዕከላት በቀላሉ ሊበላሹ ለሚችሉ ምርቶችም ተገቢው ፋሲሊቲ ተሟልቶ እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አሁን ባለው ሁኔታ ምርቶች ባሉበት አካባቢ አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስችል  የቀዝቃዛ ምርቶች የሎጅስቲክስ ፋሲሊቲ እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

### 81. የአየር ጭነት ማዕከላት ከሌሎች የትራንስፖርት ዘዴዎችና የሎጅስቲክስ ማዕከላት ጋር በማቀናጀት የግንባታ ተግባር ማከናወን

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ ቀዳሚ አገልግሎት ሰጪ እና በብዙ አፍሪካዊያን ዘንድ ተመራጭ ነው፡፡ በመሆኑም ይህንን ብቃት በማሳደግ በሀገር ውስጥ የካርጎ ሎጅስቲክስ ማዕከላትን በመገንባት ከኢትዮጵያ አልፎ ለሌሎች ሀገራትም በማዕከልነት ሊያገለግል ይችላል፡፡ ስለሆነም የአየር ጭነት የሎጅስቲክስ ማዕከላት ከሌሎች የትራንስፖርትና የሎጅስቲክስ ማዕከላት ጋር በማቀናጀት ግንባታ ይከናወናል፡፡

## ንዑስ ስትራቴጂ 5.2 የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት መገንባት

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 82. የትራንስፖርት መሠረተ-ልማት ማስተር ኘላን ማዘጋጀት፡፡

የትራንስፖርት መሰረተ - ልማትን በዘላቂነት ለመገንባት እና ለማሳደግ እንዲቻል ሀገራዊ የሆነ የትራንስፖርት መሰረተ - ልማት ማስተር ፕላን ተዘጋጅቶ ስራ ላይ ይውላል፡፡

### 83. የትራንዚት ኮሪደሮች፣ መንገዶች የማስፋትና የማሻሻል ግንባታ እና የተሟላ ፋሲሊቲና መሣሪያዎችን የማሟላት ተግባር ማካሄድ

ይህ የመፍትሄ ሃሳብ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ የሚፈጸም ሲሆን ከመካከለኛ ጊዜ አኳያ አሁን የምንጠቀምባቸውን ከወደብ ጋር የሚገኛኙ ኮሪደሮችን ደረጃ የማሳደግ ስራ ሲሆን ከረጅም ጊዜ አኳያ በትራንስፖርት መሰረተ-ልማት ማስተር ፕላን መሰረት የሚፈጸም  ነው፡፡

## 84. የነዳጅና መሰል ፈሳሽ ጭነቶች የዴፖና የማጓጓዣ መስመር ግንባታ ማካሄድ

ሀገራችን ነዳጅ ከውጪ በከፍተኛ መጠን የምታስገባ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለውን ነዳጅ የማጓጓዝ፣ የማሰራጭት እና በሀገር ውስጥ የነዳጅ ዲፖ ማዕከላትን የመገንባት ስራ በተመለከተ በቀጣይ በሚዘጋጅ ሀገራዊ ማስተር ፕላን መሰረት እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡

| ንዑስ ስትራቴጂ 5.3 የሎጅስቲክስ ሥርዓት ለማሻሻል የሚያስችል የ"IT" ግንባታ ማከናወን |
|---|
| የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡ |

## 85. የጭነት መረጃ ልውውጥ "Freight Information Exchange System" ስርዓት መዘርጋት

ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባም ሆነ ወደ ውጪ የሚላክ ጭነት በደረሰበት ቦታ ሁሉ ለማወቅ የሚያስችል አሁናዊ መረጃ "Real Time Data" አቅርቦት ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 86. የሎጅስቲክስ ወጪን እና ጊዜን ለመቆጠብ የሚያስችል የግብይት ስርዓት ተግባራዊ ማድረግ

አሁን በዓለም ላይ ያለው የሸቀጦች የግብይት ስርዓት በኤሌክትሮኒክስ የተደገፈ እና የሎጅስቲክስ ሂደትን በእጅጉ የቀነሰ ሆኗል፡፡ ስለሆነም የኤሌክትሮኒክ ንግድ "E-Commerce" በተደራጀ መልኩ በሀገራችን ተግበራዊ እንዲሆን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 87. ዘመናዊ የተርሚናል እና የኮሪደር ማኔጅመንት ስርዓት መዘርጋት

የተሟላና የተቀናጀ የተርሚናል የኦፐሬሽን ሥርዓት በሀገር ውስጥ ደረቅ ወደቦች በጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የ CCTV, GPS, Electronic Cargo Tracking እና መሰል ዘመናዊ የተሽከርካሪ ስምሪትና የጭነት መቆጣጠሪያ ቴክኖሎጅዎች በሁሉም ኮሪደሮች ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

## ስትራቴጂ - 6 የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተቋማዊ አቅምና የዘርፉ የሰው ኃይል መገንባት እና ውጤታማ አደረጃጀት መፍጠር

*የስትራቴጂው መግለጫ*

የዚህ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ የዘርፉን የሰው ኃይል ብቃትና ክህሎት በማሳደግና የአገልግሎት ጥራቱን በማሻሻል ዘርፉ በዕውቀት እንዲመራ ማድረግ ነው፡፡ እንደዚሁም በዘርፉ ጠንካራ ቅንጅት ለመፍጠር ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት ንዑሳን ስትራቴጂዎች ተነድፏል፡፡

እነርሱም፡-

| | |
|---|---|
| ንዑስ ስትራቴጂ 6.1 | የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተቋማዊ አቅም ማሳደግ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 6.2 | የሎጅስቲክስ ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ማካሄድ |
| ንዑስ ስትራቴጂ 6.3 | ሎጅስቲክስን በተቀናጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል ውጤታማ አደረጃጀት መፍጠር |

### ንዑስ ስትራተጂ 6.1 የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ተቋማዊ አቅም መፍጠር

የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 88. በሎጅስቲክስ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶችና ኦፐሬተሮችን ለመምራት የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር

በሀገራችን በሎጅስቲክስ ዘርፍ የሚሰጡ አገልግሎቶች አሠራሮችና ኦፐሬተሮችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመምራትና ለመቆጣጠር የሚያስችል አደረጃጀት መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህም በሀገራችን የተዘረጋው/የሚዘረጋው የሎጅስቲክስ ሥርዓት ውጤታማነቱን ባረጋገጠ መልኩ ለመምራት እንዲቻል ሎጅስቲክስን የማቀናጀት እና የመቆጣጠር ስልጣን የተሰጣቸው ተቋማት ተልዕኮ እና አደረጃጀት ተፈትሾ ዓለም አቀፍ የሎጅስቲክስ የአመራር ስርዓትን መሰረት ያደረገ አደረጃጀት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ ተቋማቱም የኦፐሬተሮችን ብቃት የማረጋገጥና ክፍተቶችም ካሉ የማረም ብቃታቸው በየጊዜው እንዲሻሻል ብሄራዊ የሎጅስቲክስ የኦዲት አሠራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 89. የሎጅስቲክስ ዘርፍን በዕውቀት ለመምራት የሚያስችል ተቋማዊ ዓቅም መገንባት

በኢትዮጵያ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ውስጥ ቁልፍ ሚና ያላቸው ተቋማት ዘርፉን በዕውቀት ለመምራት እንዲችሉ ያለባቸው ክፍተቶችን በዳሰሳ በመለየት ተከታታይነት ያለው ሥልጠና ለመስጠት እንዲቻል በየተቋማቱ የሎጅስቲክስ ተጠሪ አካል "Focal Point" እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡ ይህ ተጠሪ አካል ከሚቋቋመው ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካውንስልና የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ ጋር የተናበበ አሰራር እነዲኖረው ስርዓት ይዘረጋል፡፡

| ንዑስ ስትራቴጂ 6.2 የሎጅሰቲክስ ዘርፍ የሰው ኃይል ልማት ማካሄድ |
|---|
| የዚህ ንዑስ ስትራቴጅ የማስፈጸሚያ ስልቶች (Intervention) የሚከተሉት ናቸው፡፡ |

## 90. የሎጅስቲክስ የልህቀት ማዕከል ማቋቋም

የሎጅስቲክስ ሥልጠና የሚሰጥ፣ የሎጅስቲክስ ባለሙያዎችን የብቃት መለኪያ የሚያዘጋጅ፣ የሎጅስቲክስ የዕውቀት ባንክ የሚሆኑ የሎጅስቲክስ የልህቀት ማዕከሎች ይቋቋማሉ፡፡

## 91. የምሥክር ወረቀት መርሀ-ግብርና ዕውቅና የሚሰጥበት ስልት መቀየስ

በሎጅስቲክስ ዘርፍ የተሰማሩ ባለሙያዎችና ድርጅቶች የዕውቅናና የብቃት ምስክር ወረቀቶች የሚሰጡ ለምሣሌ ለጉምሩክ አስተላለፊዎች የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፣ ለእቃ አስተላላፊዎችና የመርከብ ወኪሎች የማሪታይም ጉዳይ ባለሥልጣን፣ የንግድ ፈቃድ ደግሞ የንግድ ሚ/ር የሚሰጡዋቸው ሲሆኑ፣ በዋናነት ወጥና የተቀናጀ አይደለም፡፡ የሚሰጡት ሥልጠናዎችም የተሟሉ አይደሉም፡፡ የሥልጠና ዕድሉም በጣም ጠባብ በመሆኑ በአጭር ስልጠና ብቃት የሚሰጣቸው ባለሙያዎች በጣም ውሱን በመሆናቸው ለእጥረት ዳርጓል፡፡ የዕውቀትና የክህሎት ክፍተቱም በዘርፉ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል፡፡ ስለሆነም እነዚህና ተያያዥ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል በሀገር ደረጃ ወጥ የሆነ የሥልጠና መርሀ-ግብር ዕውቅና የሚሰጥበት አሠራር ስርዓት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 92. የሎጅስቲክስ የመረጃ ማዕከል (Logistics Information Hub) መፍጠር

የሀገሪቱ የሎጅስቲክስ ሥርዓት ያለበትን ደረጃ ለመገንዘብ፣ አፈጻጸሙን ለመለካት፣ በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለማካሄድ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ አያያዝ ችግር አለ። ስለሆነም የሎጅስቲክስ መረጃ በሥርዓት የሚሰባሰብበት፣ የሚጠናቀርበት እና በቀጣይ የሀገር ጥቅም ለማስጠበቅ በሚደረጉ የፖሊሲና የጥናት ስራዎች መነሻ የሚሆን መረጃ ለማደራጀት እንዲቻል ብሄራዊ የሎጅስቲክስ የመረጃ ማዕከል ይቋቋማል።

## 93. የሎጅስቲክስ አገልግሎት አሰጣጥ ምርጥ ተሞክሮ ወይም ልምድ (practice) መንደፍ

ለጭነት አስተላላፊዎች፣ ለትራንስፖርት ማኅበራት፣ ለሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች ዓለምአቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ግልጽነት፣ ቅልጥፍናና ጥራት ላይ የተመሠረተ የአገልግሎት አሰጣጥ ልምድ (practice) ለመቅሰም እና ለመተግበር የሚስችል አሰራር ይዘረጋል።

## ንዑስ ስትራቴጂ - 6.3 ሎጅስቲክስን በተቀናጀ አግባብ ለመምራት የሚያስችል ውጤታማ አደረጃጀት መፍጠር

### የንዑስ ስትራቴጂው መግለጫ

የሎጅስቲክስ ሥርዓት ከመነሻ እስከ መድረሻ ባለው ሂደት ሶስት ፍሰቶችን (Flows) ማለትም፡- የዕቃ ፍሰትን፣ የፋይናንስ ፍሰትንና የመረጃ ፍሰትን አቀናጅቶ፣ አስተሳስሮ የማቀድ፣ የመምራትና የመቆጣጠር አሠራር ነው። የሎጅስቲክስ ሂደት የተለያዩ ባለድርሻ አካላትንና ተቋማትን የሚያሳትፍ ሥርዓት ነው። ስለሆነም እነዚህ አካላትን በተቀናጀ መልኩ በሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ውስጥ በጋራ የመስራት፣ የሎጅስቲክስ ዓላማን ለማሳካት በሁሉም ዘርፍ ትስስር የመፍጠር ጉዳይ በጣም አስፈላጊ ነው። በመሆኑም የዚህ ንዑስ ስትራቴጂ ዋና ዓላማ የሀገራችን የሎጅስቲክስ የቅንጅት ክፍተት ቁልፍ ችግርን ለመፍታት የሚያስችልና ዘርፉን በበላይነት የሚመራ የተቀናጀ አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ ነው። የስትራቴጂውን ዓላማ ለማሳካት የሚከተሉት የማስፈጸሚያ የመፍትሄ ሃሳቦች (Interventions) ከታች ተመልክቸዋል።

እነርሱም፡-

## 94. ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካውንስል ማቋቋም

የሀገራችን የሎጅስቲክስ ሥርዓት ትራንስፎርም ለማድረግና እንደሀገር በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪነታችን ለማረጋገጥ ብሎም በአስተማማኝ ደረጃ ለማስቀጠል በሎጅስቲክስ ዘርፍ ቁልፍ ሚና ያላቸው ተቋማት መቀናጀት ብቻ ሳይሆን ሎጅስቲክስ ነክ የሆኑ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች የሚመሩ በተለያየ ደረጃ የተዋቀሩ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎችን በበላይነት የመምራት፣ በጋራ ማቀድ፣ በጋራ መገምገም፣ የሎጅስቲክስ ሥርዓቱን ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስችሉ ሥራዎችን እንደየድርሻቸው ቆርሰው በመውሰድ መተግበርን ይጠይቃል፡፡ ከዚህም ባለፈ ይህን ትልቅ ኃላፊነት ለማቀናጀት ከፍተኛ ውሣኔ የሚሹ ጉዳዮችን በወቅቱ ለመወሰንና ለማስፈጸም የከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች አመራር (High Level Leadership) ወሣኝ ነው፡፡ ለዚህም የሎጅስቲክስ ሥርዓታችን ትራንስፎርም ለማድረግ ትልቁ ዓምድ (pillar) በብሄራዊ ደረጃ በሎጅስቲክስ ሥርዓት ቁልፍ ሚና ያላቸው የሚኒስቴር መ/ቤቶችና ተቋማትን ያካተተ በከፍተኛ ኃላፊ የሚመራ፣ ተጠያቂነትና ኃላፊነት ያለው ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካውንስል በህግ ይቋቋማል፡፡

## 95. የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ ማቋቋም

የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ በብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካዉንስል የሚወስኑ ጥናቶች፣ የፖሊሲ ሃሣቦች፣ ሪፖርቶች፣ ኘሮግራሞችና መሰል ሥርዓቱን ትራንስፎርም ለማድረግ ወሣኝ የሆኑ ኘሮፖዛሎችን የሚያቀርብ ነው፡፡ ካውንስሉም ሆነ መንግስት የሎጅስቲክስ ዘርፉን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ የሚሰጡ ውሣኔዎች በተሳሳተ መረጃ እንዳይሆን በትክክለኛ መረጃና በቂ ትንታኔ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ኃላፊነት አለበት፡፡ በሎጅስቲክስ ስትራቴጂው ውስጥ ያሉት የመፍትሄ ሃሳቦችን (Interventions) ወደ ኘሮግራም የመለወጥ፣ የትግበራ መርሀ-ግብር አዘጋጅቶ ትግበራውን በተሟላ መልኩ መከታተልና በዘርፉ የሚገኙት ተቆጣጣሪ እና አገልግሎት ሰጪ አካላትን በማቀናጀት የስትራተጂውን ትግበራ የተሟላ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህ ቢሮ በሎጅስቲክስ/ሰኘላይ ቼይን ዘርፍ ከፍተኛ ትምህርት ያላቸው (Academia) ከኢንዱስትሪው በቂ ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች ያካተተ እንዲሆን ተደርጎ ይደራጃል፡፡

## 96. የሎጅስቲክስ ካውንስል በክልል መስተዳድሮች ደረጃ ማቋቋም

የብሄራዊ የሎጅስቲክስ የቅንጅት ካውንስል ማቋቋምን ተከትሎ በክልል መስተዳድሮችም ከዚህ ከዋናው ካውንስል ተናቦና ተቀናጅቶ የሚሠራ የሚመለከታቸው ተቋማትን ያካተተ ካውንስል ይቋቋማል፡፡

## 97. የከተሞች የሎጅስቲክስ ካውንስል ማቋቋም

የከተሞች በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ ዕድገት፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ የአየር ብክለትና መሠል ጉዳዮችን ከግምት በማስገባት የከተማ የሎጅስቲክስ ባህሪይን ያገናዘበ ሥራ ለመሥራት የከተሞች የሎጅስቲክስ ካውንስል (Urban Logistics Council) ይቋቋማል።

## 98. የሎጅስቲክስ ኮሙኒቲ ማቋቋም

የሎጅስቲክስ ስርዓቱን ይበልጥ በተቀናጀ መልኩ ለመምራት በግል ዘርፍ የተሰማሩ አካላትን ማሳተፍ ወሣኝ ነው። ለዚህም የሎጅስቲክስ ኮሚዩኒቲ ይቋቋማል። በኮሚዩኒቲው ውስጥ የጭነቱ ባለቤት፤የተቆጣጣሪ ተቋማት፤ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎች እና የዩኒቨርሲቲ ምሁራን የሚካተቱበት ይሆናል። ኮሚዩኒቲው የበለጠ በዕውቀት የተደራጀ ሀሳብ ለማቅረብ እንዲችል ከሎጅስቲክስ ባለሙያዎች ማህበር ጋር በቅንጅት እንዲሰራ ይደረጋል። ሌሎቹ በሙሉ በጭነት ባለቤቱ ዙሪያ የሚሰለፉ ሆነው የጭነት ባለቤቱ ግን ዋናው አምድ ይሆናል። የሎጅስቲክስ ሥርዓቱ ትራንስፎርም ሆነ ማለት በዋናነት የመጀመሪያው ተጠቃሚ የጭነት ባለቤት (Cargo Owner) ነው። ስለሆነም የሎጅስቲክስ ኮሚዩኒቲው ለሎጅስቲክስ ካውንስሉ የሚቀርቡ እና ውሳኔ የሚስፈልጋቸውን ጉዳዮች በመለየት ረገድ ከሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ እና ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካውንስል ጋር በመቀናጀት የሚሰራ ይሆናል።

# ክፍል አራት:

## የስትራቴጂውን በመፈጸም ረገድ ከመንግስት የሚጠበቁ እርምጃዎች፣ ባለድርሻ አካላት ሚና የክትትልና ግምገማ ስርዓት

### 4.1 ከመንግስት የሚጠበቁ እርምጃዎች

የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ስትራቴጂው የሀገራችንን የሎጅስቲክስ ማነቆዎች በመፍታት ሎጅስቲክሱ ኢኮኖሚውን መደገፍ ከሚችልበት ደረጃ ያደርሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለሆነም ስትራቴጅው ከጸደቀ በኋላ ለአፈጻጸሙ አስፈላጊውን መዋዕለ ነዋይ በመመደብ ስትራቴጅውን ሊሸከም የሚችል አደረጃጀት መፈጠር ይኖርበታል፡፡ በተለይም ሎጅስቲክስ በከፍተኛ አመራሩ ቀጥተኛ ተሳትፎ የማቀናጀቱን ስራ አቻ ለሆኑ ተቋማት ብቻ መተው ውጤቱ የተጠበቀውን ያህል አይሆንም፡፡ ስለሆነም ይህንን ችግር ለመፍታት የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ካውንስልን በህግ በማደራጀት የስትራቴጅውን አፈጻጸም ከስትራቴጅው የሚመነጩ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮገራሞችን በቀጥታ እየተከታተለ እንዲመራ ማድረግ ይጠበቃል፡፡

ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ስትራቴጅ ከፍተኛ የመንግስት ሃላፊዎችን ያካተተ አደረጃጀት እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ ስለሆነም ይህ አደረጃጀት በየቀኑ እየተገናኘ ስለሎጅስቲክስ ብቻ እየመከረ ሊውል ስለማይችል ሊወሰኑ የሚገባቸውን ተግባራት በየዕለቱ እየተከታተለ እና ለውሳኔ በሚያመች መልኩ የሚያቀርብ የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ መቋቋም ይኖርበታል፡፡ የቢሮው መደበኛ ስራ ስትራቴጅውን ወደ ፕሮጀክትና ፕሮግራም የመለወጥና የፕሮጀክት ጽ/ቤቶችን የማቋቋም እና የመደገፍ አፈጻጸማቸውን የመለካት ሚና ይኖረዋል፡፡

### 4.2 የባለድርሻ አካላት ሚና

ይህን ስትራቴጅ ከመፈጸም አኳያ በርካታ ባለድርሻ አካላት ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የዋና ዋናዎቹ ሚና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

## የገንዘብ ሚኒስቴር

የገንዘብ ሚኒስቴር ይህንን ስትራቴጅ በማስፈጸም ረገድ በዋናነት ለሚዘጋጁ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች ሀብት የመመደብ ሲሆን የተመደበው ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን የመከታተል እና የማሻሻያ አርምጃዎችን የመውሰድ እንዲሁም የጉምሩክ አሰራር ስርዓቶችን በማሻሻል ረገድ ቁልፍ ሚና አለው፡፡

## የንግድ እና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና በስሩ ያሉ ተቋማት

የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን የንግድ ፈቃድ የመስጠት እና በወሰዱት ፈቃድ ልክ አገልግሎት መስጠታቸውን የመቆጣጠር፤ የመንግስት ደረቅ ብትን ጭነት አስመጪ ድርጅቶችን የግዢ እና የስርጭት ስርዓት ለማሻሻል አንዲሁም ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ እቃዎች የሚደረገውን የጥራት ፍተሻ እና የላብራቶሪ አሰራር ዘመናዊ ለማድረግ በሚቀረጹ ፕሮግራሞች ላይ በባለቤትነት የመስራት ሚና ይኖረዋል፡፡

የኤክስፖርት ሎጅስቲክሱን በማሻሻል የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የኤክስፖርት ተወዳዳሪነት ለማሳደግ የሚቀረጹ ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ከብሄራዊ ሎጅስቲክስ ካውንስል በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት የማስፈጸም ሃላፊነት አለበት፡፡

## የገቢዎች ሚኒስቴር

የጉምሩክ አሰራር የማሻሻል፤የድንበር አገልግሎት አሰጣጥ የማዘመን፤ የቴክኖሎጅ አጠቃቀምን የማሳደግ እና ከጉምሩክ ጋር በተያያዘ በሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ የሚቀረጹ ፕሮግራምና ፕሮጀክቶች ያስፈጽማል፡፡

## በትራንስፖርት ሚኒስቴር ስር ያሉ ተቋማት

በመሰረተ-ልማት ግንባታ በተለይም በመንገድ ልማት፤ በተርሚናል እና ወደብ ግንባታ፤የጭነት ትራንስፖርት ማኔጅመንት ማዘመን፤ የአየር ጭነት ሎጅስቲክስ ማዕከል በመገንባት፤ የሎጅስቲክስ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶችን ብቃት በማረጋገጥ እና አደረጃጀታቸውን ለማሻሻል የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞችን የማስፈጸም ሃላፊነት ይኖራቸዋል፡፡

## የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን

በኤክስፖርት ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ ለተሰማሩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ልዩ የሎጅስቲክስ አገልግሎት እንዲያገኙ የሚቀረጹ ፕሮጀክቶች እና ፕሮግራሞች የሚያስፈጽም ይሆናል፡፡

## የትምህርት ሚኒስቴር

በሎጅስቲክስ ዘርፍ ያለውን የእውቀት እና የክህሎት ክፍተት ለመድፈን ዘላቂ የሆነ የዩኒቨርስቲ እና ኢንዱስትሪ ትስስርን በማጠናከር በቂ የሎጅስቲክስ ባለሙያ ለማፍራት የሚነደፉ ፕሮጀክቶችን ያስፈጽማል፡፡

## የመንግስት የልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ

በሎጅስቲክስ ዘርፍ የተሰማሩ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን በአደረጃጀት፣በአሰራር እና በሰው ኃይል ትራንስፎርም ለማድረግ የሚቀረጹ ፕሮጀክቶችን እና ፕሮግራሞችን በበላይነት ያስፈጽማል፡፡

## የግብርና ሚኒስቴር

የግብርና ምርቶች ኤክስፖርትን ለማሳደግ፣የእንስሳት ሀብት ኤክስፖርት ሎጅስቲክስ ለማሻሻል፣የግብርና ግብዓት ግዢ እና የሎጅስቲክስ ሂደት ዘመናዊ ለማድረግ የሚቀረጹ ፕሮግራሞችን በግንባር ቀደምነት ያስፈጽማል፡፡

## የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

ሀገራችን አስተማማኝ የባህር ወደብ አገልግሎት እንድታገኝ፣ በኮሪደር እና በወደብ ልማት ከውጪ ሀገር ኩባንያዎች እና ከባለወደብ ሀገራት ጋር በጋራ ለማልማት የሚደረጉ ድርድሮችን እና ይህንን ለማስፈጸም የሚቀረጹ ፕሮግራሞች በማስፈጸም ረገድ ቁልፍ ሚና ይኖረዋል፡፡

## ብሔራዊ ባንክ

በውጭ ንግድ ለተሰማሩ አንቀሳቃሾች የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስ አቅርቦት ችግር የመፍታት፣ የውጭ ምንዛሬ አሰጣጥ ችግር ለመቅረፍ እና አጠቃላይ የአሰራር ስርዓት ለማሻሻል የተቀመጡ ስትራቴጅዎችን ያስፈጽማል፡፡

## የኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት

ድርጅቱን በሁለንተናዊ መልኩ ትራንስፎርም ለማድረግ የተቀመጡ ስትራቴጅዎችን በካውንስሉ በሚቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ይፈጽማል፡፡

## ዓለም አቀፍ ደጋፊ ተቋማት እና ሀገራት

የሎጅስቲክስ ልማትን በመደገፍ ረገድ በርካታ ሀገራት እና ዓለም አቀፍ ተቋማት ያሉ ሲሆን ከሀገራችን ጋር ካላቸው ግንኙነት አንጻር ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሀገራትና ተቋማት በፋይናንስ፤ በስልጠና እና በምክር (Consulting Service) ስትራቴጂዉን ከማስፈጸም አንጻር ድጋፍ ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

እነሱም፡-

- የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (United Nation Development Programme /UNDP)
- የተባበሩት መንግስታት የንግድ እና ልማት ኮንፈረንስ (United Nation Conference on Trade and Development / UNCTAD)
- የቻይና መንግስት (The Government of Peopls Republic of China)
- የሩሲያ መንግስት (The Government of The Russian Soveit Fedrative Socialist Republic)
- የህንድ መንግስት (The Government of India)
- የጃፓን መንግስት (The Government of Japan)
- የደቡብ ኮሪያ መንግስት (The Government of South Korea)
- የአውሮፓ ህብረት (Eropean Union)
- የአፈሪካ አቅም ግንባታ ፋውንዴሽን (African Capacity-Building Foundation /ACBF)
- የአፈሪካ ልማት ፋውንዴሽን (African Development Foundation /ADF)

- የፈረንሳይ ልማት ኤጀንሲ (Agence Francaise De Developpment /AFD)
- የኤሺያ ልማት ባንክ (Asian Development Bank /ADB)
- የአውስትራሊያ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (Australian Agency for International Development /AusAID)
- የዓለም ባንክ (The World Bank Group)
- የካናዳ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ (Canadian International Development Agency /CIDA)
- ከታዳጊ ሀገራት ጋር የምርምር አጋርነት ኮሚሽን (Commission for Research Partnership with Developing Countries /KFPE)
- የኢንተርፕራይዞች ልማት ለጋሾች ኮሚቴ (The Donor Committee for Enterprise Development /CDASED)
- የዓለም አቀፍ ልማት ዲፓርትመንት (Department for International Development /DFID)
- Deutsche Gesellschaft Fur Technische Zusammenarbeit (GTZ)
- Deutscher Akademischer Austausch Dienst (DAAD)
- Environmental Development Action in the Third World (ENDA)
- Food and Agriculture Organization of the United Nations (FAO)
- የዓለም ምግብ ፕሮግራም (UN World Food Programme / WFP)
- Inter-Academy Panel on International Issues (IAP)
- International Atomic Energy Agency (IAEA)
- International Centre for Agricultural Research in the Dry Areas (ICARDA)
- International Crops Research Institute for the Semi-Arid Tropics (ICRISAT)

- International Development Research Centre (IDRC)
- International Foundation for Science (IFS)
- International Fund for Agricultural Development (IFAD)
- International Institute for Sustainable Development (IISD)
- Islamic Development Bank (IDB)
- Japan International Cooperation Agency (JICA)
- Norwegian Agency for Development Cooperation (NORAD)
- OPEC Fund for International Development (OPEC FUND)
- Organization for Economic Cooperation and Development (OECD)
- RAND Corporation (RAND)
- Swedish International Development Cooperation Agency (SIDA)
- Swiss Agency for Development and Cooperation (SDC)
- Trade Mark East Africa (TMEA)
- Ford Foundation
- Rockefeller Foundation
- Commercial Logistics Providers (DHL, FEDEX, UPS, 2/3/4PL providers, etc.)

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ሌሎችም በዚህ ያልተጠቀሱ ተቋማትን በማፈላለግ ድጋፍ እንዲያደርጉ አቅዶ መስራት ተገቢ ይሆናል።

## 4.3 የስትራቴጅው አፈጻጸም ክትትል እና ግምገማ አቅጣጫ

ስትራቴጅው ተግባራዊ ሆኖ የታለመለትን ሀገራዊ ፋይዳ ማሳካት እንዲችል በየደረጃው የአፈጻጸም ክትትል እና የግምገማ ሪፖርቶች እየተዘጋጁ የሚቀርቡ ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር የብሄራዊ ሎጅስቲክስ ካውንስሉ በበላይነት ወደፊት በሚወሰን የጊዜ ገደብ እየተገናኘ አቅጣጫዎችን የሚሰጥ ይሆናል፡፡ የሎጅስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮው ደግሞ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረዥም ጊዜ የትግበራ እቅዶችን በማዘጋጀት ተቋማትን ይደገፋል፣ የአፈጻጸም ሪፖርት በማዘጋጀትም ለካውንስሉ ያቀርባል፡፡ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በተቋማቸው ከስትራቴጅው የሚደርሳቸውን ተግባር በመወሰድ እና የራሳቸውን አደረጃጀት በመፍጠር አፈጻጸሙን እንደሚከታተሉ ይጠበቃል፡፡ የአጠቃላይ ስትራቴጅው አፈጻጸም በተወሰነ ጊዜ በባለሙያዎች ዝርዝር ኦዲት ተደርጎ ለቀጣይ እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ ለካውንስሉ የሚያቀርቡበት አሰራርም ተግባራዊ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ ብሄራዊ የሎጅስቲክስ ካወንስሉም ለሚኒስተሮች ም/ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የአፈጻጸም ሪፖርት የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ አጠቃላይ የክትትል እና ግምገማ ሂደቱን በተመለከተ ዝርዝር አሠራር ተዘጋጅቶ የሚመራ ይሆናል፡፡